# በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው

በ

ሞገስ ሚካኤል

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር

ሰኔ 2002 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው


በ

ሞገስ ሚካኤል

አማካሪ

ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር)


በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር



ሰኔ 2002 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

YONAS ADMASSU ______________________ ______________________

አማካሪ ፊርማ

[illegible] ______________________ ______________________

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

______________________ ______________________

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

ከሁሉም በላይ የጥናት ጽሑፌን ረቂቅ በማረምና በማስተካከል ያላሰለሰ ጥረት ላደረጉ አማካሪዬና አስተማሪዬ ዶክተር ዮናስ አድማሱ የከበረና እጅግ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ቀጥሎ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በጀት መድቦ ይህንን ጥናት እንድሰራ ስለረዳኝ አመሰግናለሁ። የቀብር ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ መረጃ ለሰጡኝና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ተቋማትና ግለሰቦች ሁሉ የትብብር ደብዳቤ በመጻፍ የረዱኝን የላይ አርማጭሆ ወረዳ አስተዳደር ዋና ጽህፈት ቤት ምክትል ሃላፊ የሆኑትን አቶ ደምሴ በየነን፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱን እንድቀርፅ የፈቀዱልኝንና ያስፈቀዱልኝን ቄስ አዲሱ ቀጸላን፣ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝን የወረዳው ማህበረሰብ አባላትንም ሁሉ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

ወንድሜ እንዳልካቸው ተሰራ (ቢቦዬ) ለትምህርቴ መቃናት ከልጅነት እስካሁን አስፈላጊውን ድጋፍ አከናውነሃልና አመሰግንሃለሁ። የሃሳብ ድጋፍ የሰጣችሁኝ ጓደኞቼ የኔሁን ብርሌ፣ ሣምራዊት ዘውዱ፣ ሰይድ ይማም፣ መዓዛሽወርቅ እርገጥ፣ አመሰግናችኋለሁ።

በመጨረሻም ጥናቱን በኮምፒውተር የጻፍሽልኝ ኤደን ሃብቴ አመሰግንሻለሁ።

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና ....................................................................... I

አጠቃሎ ..................................................................... iv

መቅድም ..................................................................... v

1. መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ .............................................................. 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................ 2

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች ..................................................... 3

1.4 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ............................................ 3

1.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ........................................ 4

1.6 የአጠናን ዘዴ ............................................................ 6

1.7 የናሙና አወሳሰድ ....................................................... 6

1.8 የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ ............................................... 6

1.9 የጥናቱ ወሰን ............................................................ 7

1.10 የጥናቱ አደረጃጀት ..................................................... 7

1.11 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ....................... 7

2. ክለሳ ድርሳን

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ................................................ 10

2.1.1 የለቅሶ ስርዓትንና ሙሾን ያጠኑ ..................................... 10

2.1.2 የለቅሶ ሥርዓትን፣ ሙሾን፣ ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ .................. 15

2.1.3 የለቅሶ ሥርዓትን ብቻ ያጠኑ ......................................... 18

2.1.4 ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ ............................................ 18

2.2 የንድፈ ሀሳብ (Theories) ቅኝት ........................................ 22

2.2.1 የቀብር ሥነ ሥርዓት ................................................. 22

2.2.2 ቀረርቶ .................................................................. 23

2.2.3 ፉከራ .................................................................... 24

2.2.4 ክዋኔ (Performance) ................................................. 29

2.2.4.1 የመከወኛ ምክንያት (Occasion) ...................................... 30

2.2.4.2 ከዋኝ (Performer) ....................................................................31
2.2.4.3 ታዳሚ (Audience) ....................................................................32
2.2.4.4 አውድ (Context) ....................................................................33
2.2.4.4.1 ተጨባጭ አውድ (physical context) ....................................33
2.2.4.4.2 ማህበራዊ አውድ (Social Context) ....................................34
2.2.4.5 ድርሰት (Composition) ....................................................................35
2.2.4.6 የክዋኔ ጠቋሚዎች (Performance markers and Frames) .........36
2.2.4.7 የመከወኛ ቁሶች ....................................................................37
3. ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢ ዳራ ....................................................................39
4. በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፤ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ
ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው ....................................................................44
4.1 የቅድመ ሞት ዝግጅት ....................................................................44
4.1.1 የኑዛዜ ሥርዓት አፈፃፀም ....................................................................45
4.1.2 ለዋናው ለቅሶና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች ....................46
4.2 ጊዜ ሞት ....................................................................48
4.2.1 በምሽት የሚካሄዱ ሥነ ሥርዓቶች ....................................................................48
4.2.2 በንጋት የሚካሄዱ ሥነ ሥርዓቶች ....................................................................54
4.2.2.1 ግንዘት ....................................................................57
4.2.3 በአስከሬን ጉዞ ወቅት የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች ....................................60
4.3 ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች ....................................................................77
5. ማጠቃለያና ይሁንታ
5.1 ማጠቃለያ ....................................................................86
5.2 ይሁንታ ....................................................................87
ዋቢ ጽሑፎች ....................................................................89
አባሪዎች
አባሪ አንድ፡- የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች ስብስብ ....................................................................1
አባሪ ሁለት፡- የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል ....................................................................21
አባሪ ሦስት፡- ኢንተርቪው ለተደረጉ አካላት የቀረቡ መንደርደሪያ ጥያቄዎች ....................24

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በላይ አርማጭሆ ወረዳ በሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓትና በሥነ ሥርዓቱ ላይ በሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ጥናቱ በወረዳው የሚደረገውን የጀግና የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚደረገውን የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ በቪዲዮ በመቅረፅ፣ በቴፕ በመቅዳት፣ ፎቶግራፍ በማንሳት፣እና በጽሑፍ በማዘጋጀት፣ እንዲቀረስ ማድረግ፣ የሚለውን ነጥብ ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ገላጭ የምርምር ዘዴንም ተግባራዊ አድርጓል፡፡

ጥናቱ የመስክ ምርምርን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በመስክ ስራ የቪዲዮ፣ የቴፕና የፎቶግራፍ ቀረፃዎች፣እና ስለ ቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በቂ እውቀት አላቸ ው ከተባሉ ካህ ናት፣ አዛውንቶች፣ ፖሊሶች፣ ፎካሪዎችና ሌሎችም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ኢንተርቪዎች፣ ተከናውነዋል፡፡

በዚህም መሠረት በወረዳው፣ ከየቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በተለይም፣ ከግንዘት፣ ከፍታት፣ ከአቀባበር አቅጣጫ፣ ወዘተ.፣ ጋር ተያይዘው፣ በካህናትና በሌላው ማህበረሰብ የሚፈፀሙ እርስ በርስ የሚጣረሱ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ሥነ ሥርዓቶች እንዳሉ በጥናቱ ታውቋል፡፡ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔን በተመለከተም፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከኢኮኖሚና ከልማድ፣ የመነጩ የአመለካከት ልዩነቶች እንዳሉ በጥናቱ ታውቋል፡፡ ይኸውም በወረዳው በሚደረግ የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ከቀረርቶውና ከፉከራው ጋር ብዙ ጥይት የመተኮስ ልማድ በመኖሩ፣ ድርጊቱን የፈጸሙ ሰዎች በየመንግስት አካላት "ሰላምና ፀጥታ አደፍራሽ" ተብለው በመወንጀል፣ ጠመንጃቸውን እንዲነጠቁ፣ በእስርና በገንዘብ እንዲቀጡ፣ እያደረገ ነው፡፡ ካህናትም፣ «ገዳይ፣ ዘራፍ እያሉ ሟችን እያሞገሱና እያወደሱ፣ በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ማቅራራትና መፎከር የሟች ነፍስ ሲኦል ትገባ ዘንድ የምስክርነት ቃል መስጠት ነው» በማለት ድርጊቱን ያወግዛሉ፡፡ የሚተኮሰው ጥይት ዋጋም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ የሥነ ሥርዓቱ ነባር ይዘት እየተለወጠ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም በማህበረሰቡ ዘንድ በቀደምቶቹ ትውልዶችና በአሁኑ ትውልድ መካከል ከሚፎከርላቸው ሰዎች ማንነት ጋር የተያያዘ የልማድ ለውጥ አለ፡፡ በቀደምቶቹ ትውልዶች በቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት የሚፎከርላቸው አርበኞችና አዳኞች ብቻ ነበሩ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለጠንካራ ገበሬዎችም መፎከር ተለምዷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ አዳኝ ተብለው የሚፎከርላቸውም እንደ ቀደምቶቹ አዳኞች ዝሆን፣ ጐሽ፣ ቀጭኔ፣ አንበሳና ሌሎችንም ትልልቅና አደገኛ የዱር እንስሳት የገደሉ ብቻ ሳይሆኑ ለምግብነት የሚውሉ የዱር እንስሳትን አድነው የገደሉም ናቸው፡፡

# መቅድም

በዚህ ጥናት በቀብር ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ወቅት የሚታዩትን አንዳንድ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድርጊቶች በአግባቡ ለመግለፅ ሲባል ከተጠቀምኩባቸው የአገላለፅ ዘዴዎች በስተቀር፣ የማህበረሰቡ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥነ ሥርዓቱ ላይ የሚገጠሙት የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች ምንም አይነት ማሻሻያና ለውጥ ሳይደረግባቸው የተገለፁ ናቸው።

በጥናቱ የመጨረሻ ክፍል በአባሪነት የተያያዙት የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞችም የተሰበሰቡት በቀብር ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ወቅት ነው። በመሆኑም በግጥሞቹ ውስጥ በአካባቢው ዘዬ የተገለፁ ቃላት፣ የቦታ፣ የሰው፣ የእንስሳት፣ ስሞች ይገኙባቸዋል። ለዚሁ መፍትሄ ይሆን ዘንድ በአካባቢው ዘዬ የተገለፁ ቃላት፣ የእንስሳት ስሞችና የቦታ ስሞች ያሉባቸውን ስንኞች ቃላቱ ስር በማስመር፣ በየስንኞቹ ጐን በቅንፍ ውስጥ አቻ ትርጉማቸውን በመግለፅ፣ የሰው ስሞችን ደግሞ ስማቸው የተጠቀሰበትን ቦታ ክፍት (___) በማድረግ ተጠቅሜያለሁ። የሰው ስሞችን ክፍት (___) በማድረግ የተጠቀምኩበት ምክንያት ብዙ ጊዜ በግጥሞች ውስጥ የሚጠቀሱት ስሞች በህይወት የሌሉ ሰዎች ስሞች በመሆናቸውና ስማቸውን መጥቀስ ተገቢ ስላልመሠለኝ ነው።

የምንጭ አጠቃቀስን በተመለከተም በትምህርት ደረጃቸው ቢ.ኤ እና ከዚያ በታች የሆኑትን (ለምሳሌ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችን ስቃኝ) "አንተ፣ አንቺ" እያልኩ ተጠቅሜያለሁ። በትምህርት ደረጃቸው ኤም.ኤ እና ከዚያ በላይ የሆኑትን፣ ታላላቅ ፀሃፍትን (ለምሳሌ፣ እንደ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ እንደ ደስታ ተክለ ወልድ ያሉትን) እና የውጭ ፀሃፍትን ደግሞ "አንቱ" እያልኩ ተጠቅሜያለሁ። እነዚህን ሰዎች "አንቱ" እያልኩ የተጠቀምኩበት ምክንያት ለሙያው እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረጋቸው ነው። በተጨማሪም የውጭ አገር ፀሃፍትን በስማቸው ብቻ ፆታቸውን መለየት አስቸጋሪ ስለሆነብኝና "አንቱ" የሚለው ቃል ሁለቱንም ፆታዎች የሚገልፅ በመሆኑ ቃሉን ተጠቅሜያለሁ።

ዓመተ ምህረት አጠቃቀስን በተመለከተ ደግሞ የሃገር ውስጥ ሰዎች ስሞችን ተከትሎ የሚመጣው ዓመተ ምህረት በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር የተገለፀ ሲሆን የውጭ አገር

ሰዎች ስሞችን ተከትሎ የሚመጣው ዓመተ ምህረት ደግሞ እንዳለ በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር የተገለፀ ነው።

የስያሜ ቃላትን በተመለከተም አንዳንዴ የሚወክሉት ጉዳይ ተመሳሳይ ሆኖ የተለያየ ስያሜ የተሰጣቸው ቃላት ያጋጥማሉ። ለምሳሌ፣ "audience" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በተለያዩ የውጭ ፀሃፍት "listener, participant, observer, viewer, spectator, public" ተብሎ ተገልፆ እናገኛለን (ቫንሲና፣ 1985፡34፤ ፊነጋን፣ 1977፡89፤ በውማን፣ 1977፡13፤ ማርታና ማርቲን፣ 2005፡128)።

ይህንኑ ቃል "ተደራሲ፣ ተሳታፊ፣ ተመልካች፣ አድማጭ" እያሉ የአማርኛ ትርጉም የሰጡትም አሉ። "ተደራሲ" ከሚለው ቃል በስተቀር ሌሎቹ የሥነቃል ክዋኔን ለመግለፅ የተሻሉ ይመስላሉ። ምክንያቱም "ተደራሲ" የሚለው ቃል ሥነቃልን ሳይሆን የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ተፅፈው የሚቀርቡለትን አካል ለመግለፅ የሚያደላ ይመስለኛል። ቃላቱ የሚወክሏቸው ሃሳቦች የተሳሰሩና የክዋኔውን አውድ ተመስርተው የሚለዋወጡ ቢሆኑም፣ በዚህ ጥናት "ታዳሚ" እያልኩ የገለፅኩት ተሳታፊ፣ ተመልካች፣ አድማጭ፣ የሚሉትን ቃላት ሊወክል የሚችል ነው።

# 1. መግቢያ

ለቅሶ ምክንያቱ ብዙ ነው። ብቸኝነት፣ ናፍቆትና ትዝታ፣ ጥቃት፣ የመንፈስ ፅናት ማጣት፣ አንዳንዴም ደስታ ሲበዛ ያስለቅሳል (ይለቀሳል)። ከነዚህ ሁሉ የተለየው ግን በሞት ጊዜ የሚለቀሰው ለቅሶ ነው። ሞት በማንኛውም ማህበረሰብ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚከሰት፣ በሰው ልጅ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ልዩ ስፍራ ያለው፣ የተፈጥሮ ግዴታ ነው። የደስታ ጊዜያት በእስክስታ፣ በጭፈራ፣ በዳንኪራ፣ በሳቅና በፈገግታ እንደሚታጀቡ ሁሉ የሞት ጊዜ ደግሞ በለቅሶ፣ በጩኸት፣ በዋይታና በሰቆቃ ታጅቦ እንደየማህበረሰቡ ወግና ልማድ ሲለያይ የሚችል የቀብር ሥነ ሥርዓት ክንውን ይፈፀማል። ይህ ልማድም ፎክሎር ትኩረት ሰጥቶ ከሚያጠናቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ የሆነው የቀብር ሥነ ሥርዓት እና ክዋኔ ከአራቱ የፎክሎር የጥናት መስኮች ጋር ቁርኝት ያለው ነው።

ይኸውም የቀብር ሥነ ሥርዓት ከፎክሎር የጥናት መስኮች ውስጥ ከሃገረሰባዊ ልማድ (Social folk custom) የሚፈረጅ ሲሆን ስርዓቱ ሲከወን አብረው የሚታዩት እንደ ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ሙሾና ረገዳ የመሳሰሉት ደግሞ ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Performing folk arts) በሚባለው የፎክሎር የጥናት ዘርፍ የሚመደቡ ናቸው።

እንደየባህሉ ደንብ የሚለያዩ ቢሆኑም፣ የቀብሩን ሥነ ሥርዓት ለማድመቅና ለማልቀሻ የሚወጡት የሟቹ አልባሳት፣ ዋንጫ፣ ጋሻ፣ ጦር፣ ጎራዴ፣ ጠመንጃ፣ የፈረስ ወይም የበቅሎ ጌጦች፣ ወዘተ. ደግሞ ከቁሳዊ ባህል (Material culture) የሚፈረጁ ናቸው። የሙሾ፣ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች ደግሞ በስነቃል (Oral folklore) ስር የሚመደቡ ናቸው።[1]

በሌላ በኩል ስነቃሎች፣ ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባትም ሆኑ ሃገረሰባዊ ልማዶች እንዲሁም ቁሳዊ ባህሎች ህልውናቸው ተጠብቆ፣ ከትውልድ ትውልድ መተላለፍ የሚችሉት ክዋኔ (Performance) ሲኖር ነው። ይህንን አስመልክተው ፈቃደ፤

---

[1] የፎክሎር የጥናት መስኮች አራት መሆናቸውን ከሪቻርድ ዶርሰን "Folklore and Folklife" መፅሐፍ 1972÷2-4፤ አቻ የአማርኛ ትርጉማቸውን ደግሞ ከፈቃደ አዘዘ "የስነቃል መምሪያ" 1991÷10 የወሰድኩት ነው።

> የአፋዊ ኪነተቃል ህልውናው ክዋኔ ነው። ከደራሲውና ከተደራሲያኑ አንደበት በመውረድ፣ በመነገር፣ በመዘመር። በመተረቱ፣ በመዘፈኑና በመደርደሩ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል። አፋዊ ኪነተ ቃል በህዝቡ መሐል ካልተከወነ ወይም በሚከወንበት መንገድ ካልተቀረሠ ሞተ እንደማለት (1984 ÷ 3-5)

በማለት ክዋኔ ለሥነቃል ህልውና መሠረት እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህ ጥናትም የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓትንና በሥነ ሥርዓቱ ላይ የሚደረገውን ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔውን በጥምረት የሚያሳይ ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ ሰው ሲሞት በተለያየ መንገድ እየተለቀሰ የቀብር ስርዓትን መፈፀም የተለመደና የሚመሳሰል ጉዳይ ሊሆን ይችላል። በለቅሶ እያጀበ የቀብር ሥነ ሥርዓትን መፈፀም ያመሳስለው እንጂ እንደየማህበረሰቡ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ. ደግሞ ልዩነት ይኖራል።

ልዩነቱ በእድሜ (ህፃን፣ ወጣት፣ አዋቂ፣ ሽማግሌ በመሆን)፣ በፆታ፣ በማህበራዊ ደረጃ (ድሃ፣ ባለፀጋ፣ ጀግና... በመሆን)፣ የተማረ፣ ያልተማረ በመሆንና በሌሎች ምክንያቶች የሚመጣ ሊሆን ይችላል።

ይህ ጥናት በተደረገበት ማህበረሰብ ዘንድም እነዚህ ልዩነቶች ጎልተው ይታያሉ። በዚህ ማህበረሰብ የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ሌላው የማህበረሰብ አባል ሲሞት እንደሚደረገው ሙሾ እየወረደ፣ ለቀስተኛው ደረቱን እየደቃ፣ ፊቱን እየቧጨረ፣ ፀጉሩን እየነጨ፣ ሳይሆን የመረረና የከረረ ሀዘን ሳይኖርበት፣ በሙሾው ፋንታ ፉከራና ቀረርቶ እየተደረገ፣ በዋይ ዋይ ፋንታ እልል እየተባለና ጥይት በብዛት እየተተኮሰ የሚከናወን ነው። ይኸው ልዩነትም ነው ትኩረቴን የሳበው።

ይኸ ጉዳይ ለጥናት የተመረጠው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

1. ይህን የጥናት ስራዬን ከመጀመሬ በፊት በአካባቢው በተለያየ ጊዜ በሞቱ ጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ በመገኘቴና ይህ ተሳትፎዬ በዚህ አካባቢ በሚደረግ የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ያተኮረ ርእስ እንድመርጥ ስላነሳሳኝ፣
2. በአካባቢው የቀብር ሥነ ሥርዓት በተለይም ፉከራና ቀረርቶን እንዲሁም ክዋኔን ማዕከል ያደረገ ምርምር ባለመደረጉ፣

3. በአካባቢው ይህ ሥነ ሥርዓት በተለይም ቀረርቶውና ፉከራው በሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ተፅእኖዎች ምክንያት ነባር ይዘቱ እየተለወጠ በመሆኑ፣

እኔም የዚህን እየተለወጠ ያለ የቀብር ሥነ ሥርዓት ምንም እንኳ ነባር ይዘቱ እየተለወጠ ያለ ቢሆንም፣ አሁን ያለውን ይዘቱን በቪዲዮና በቴፕ በመቅረፅ፣ ፎቶግራፍ በማንሳት እንዲታወቅና እንዲቀረስ የማድረግ ፍላጐት ስላደረብኝ፣

4. ተወልጄ ያደግኩት እዚያው በመሆኑና ሥነ ሥርዓቱን የማውቅ በመሆኔ፣

አንድ አጥኚ በሚያውቀው ማህበረሰብ ዘንድ ጥናቱን ቢያደርግ የተሻለ መሆኑን ፈቃደ፣ «አንድ የራሱን ባህል የሚያጠና ግለሰብ መረጃ አቀባይ እንደልብ የማግኘት፣ በአካባቢው በነፃነት የመንቀሳቀስ፣ በባህሉ የሚከለከሉና የሚፈቀዱ ጉዳዮችን የማወቅ... እድል ይኖረዋል» (1991 ÷ 118) ይላሉ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረገውን የጀግና የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚደረገውን የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ በቪዲዮ በመቅረፅ፣ በቴፕ በመቅዳት፣ ፎቶግራፍ በማንሳት፣ እና ጥናቱንም በጽሑፍ በማዘጋጀት፣ እንዲቀረስ ማድረግ ነው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀምን ዓለማዊና መንፈሳዊ ገፅታ ማሳየት፣ ይኸውም በጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ወቅት የሚደረጉ ማህበረ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክንውኖች እንዴት፣ ለምን፣ በማን፣ መቼና የት፣ ወዘተ. እንደሚደረጉ በዝርዝር ማሳየት፣

2. በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ የሚደረጉ ክንውኖች አሁንና ድሮ ምን እንደሚመስሉ በማነፃፀር ልዩነታቸውን እና ተመሳስሏቸውን ለማሳየት መጣር (ንፅፅሩ ድሮ እንዴት ይከናወኑ እንደነበር የእድሜ ባለፀጎችን በመጠየቅ፣ አሁን ከሚታየው ጋር በማነፃፀር የሚጠና ይሆናል)፡፡

3. ስለጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ክዋኔ የማህበረሰቡ አመለካከት ምንድን ነው?

(ስለዚህ የቀብር ሥነ ሥርዓት ክዋኔ በተለይም ስለቀረርቶውና ስለፉከራው ካህናት፣ ታዳሚዎች፣ አቅራሪዎችና ፎካሪዎች፣ ምን ይላሉ?)

## 1.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች

ስለየመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ፈቃደ፤

> የመስክ ምርምር በሦስት ልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄድ ይችላል፡፡ እነዚህ ሶስት መንገዶች ምልከታ (Observation) ኢንተርቪው (Interview) እና መጠይቅ (Questionnaire) ናቸው፡፡ የመስክ ምርምር በብዙ ሙያተኞች ዘንድ አስፈላጊና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ (1991 ÷ 90)

ይላሉ፡፡

የምስልና የድምፅ መቅረጫ መሳሪያዎችን በተመለከተም፣ መረጃዎችን በቴፕ፣ በቪዲዮና በፎቶ ካሜራዎች በመታገዝ መሰብሰብ በፅሁፍ ለመግለፅ አስቸጋሪ የሚሆኑትን ነገሮች ለመቅረፅ እንደሚያስችል (ጆርስ እና ጆንስ÷ 1995÷16) ያስረዳሉ፡፡

እኔም ወደ መስክ በወጣሁበት ጊዜ ከመጠይቅ (Questionnaire) በስተቀር ከላይ የተጠቀሱትን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተጠቅሜያለሁ፡፡

የመስክ ስራ፡- የዚህ ጥናት መረጃ ከየካቲት 22 እስከ መጋቢት 23/2002 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ የተሰበሰበ ነው፡፡ በመጀመሪያ ጥናቱ ወደሚያተኩርበት ወረዳ ከመጓዜ በፊት ለቀረፃና ለፎቶግራፍ ማንሻ የሚሆኑኝን መሳሪያዎች በማዘጋጀት፣ ልምድ ካላቸው ሰዎች እርዳታ በመጠየቅ አጠቃቀማቸውን ለመድኩ፡፡ ከዚያ የካቲት 22/2002 ዓ.ም ከወረዳው ደረስኩ፡፡ እንደደረስኩም፣ ወደ ወረዳው አስተዳደር ዋና ጽህፈት ቤት በማምራት ጉዳዬን ካስረዳሁ በኋላ፣ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የትብብር ደብዳቤ እንዲፃፍልኝ አደረግኩ፡፡

በመጀመሪያው ሳምንት የመስክ ቆይታዬ በወረዳው የተለያዩ ቀበሌዎች በመዘዋወር፣ መረጃ አቀባዮችን በማነጋገር፣ ወደ ወረዳው የሄድኩበትን ዓላማ እያስረዳሁ ፈቃደኝነታቸውን ሲገልጹልኝ ለኢንተርቪው ቀጠሮ እየያዝኩ፣ ቀረርቶና ፉከራ የሚደረግለት ሰው ሲሞት ቶሎ እንዲነግሩኝ እያሳሰብኩ አሳለፍኩ፡፡

በሁለተኛው ሳምንት የካቲት 29/2002 ዓ.ም አንድ በጠና ታመው የነበረ ዘማች መሞታቸው ተነገረኝና ወደ ስፍራው ሄጄ የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ክዋኔ፣ ከሥርዓተ ግንዘት

እስከ ቀብር ሥነ ሥርዓት ፍፃሜው ድረስ ያለውን ሂደት በቪዲዮና በቴፕ በመቅረፅ፣ ፎቶግራፍ በማንሳት መረጃዎችን መሠብሠብ ቻልኩ።

ኢንተርቪው፡- ስለ ቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም፣ ስለ ቀረርቶና ስለፉከራ በቂ እውቀትና ልምድ አላቸው ከተባሉ 15 ቁልፍ መረጃ አቀባዮችና 23 ንኡሳን መረጃ አቀባዮች ጋር ኢንተርቪው አድርጌያለሁ። ኢንተርቪዉ ያዘጋጀኋቸውን ጥያቄዎች እያነሳሁ መረጃ አቀባዮች እንዲመልሱልኝ በማድረግ መደበኛ (structured interviewን) እና አንዳንዴም ለውይይት ይበጃሉ የምላቸውን አዳዲስ ነጥቦች በማንሳት መደበኛ ያልሆነ (non structured interviewን) በመጠቀም የተካሄደ ነው። ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን የመረጥኩትም ስለ ሥነ ሥርዓቱ አፈፃፀም በቂ እውቀትና ልምድ አላቸው ተብሎ ከአካባቢው ሰዎች በተሰጠኝ ጥቆማ መሠረት እና በአገላለፅ ችሎታቸውም የራሴን ግምገማ በማድረግ ነው።

ኢንተርቪው ያደረኳቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች ካህናት፣ አርሶ አደር የእድሜ ባለፀጎች፣ ፖሊሶች፣ መምህራንና ተማሪዎች፣ ነጋዴዎችና ከሙያቸው ጐን በፎካሪነታቸው በወረዳው የሚታወቁ ሠዎች ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ በጥር ወር የመጀመሪያውን ሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተና በምፈተንበት ወቅት፣ ቀረርቶና ፉከራ ሊደረግላቸው የሚችል አንድ አዛውንት በጠና መታመማቸው ተነገረኝ። እኔም ፈተና አቋርጬ መሄድ የማልችልበት ወቅት ስለነበረ፣ እዚያው የሚኖር ወንድሜ የሟች ቤተሰቦችን ፈቃድ ጠይቆ፣ ፈቃደኛ መሆናቸውን እንደገለፀልኝ፣ጎንደር ለሚገኝ የካሜራ ባለሙያ 1250 ብር ከፍየ ከወንድሜ ጋር በማገናኘት፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ያለው ሂደት እንዲቀረፅልኝ አድርጌያለሁ።

በተጨማሪም በ1996 ዓ.ም የሞቱ የአንድ አርበኛ አጐቴ የቀብር ሥነ ሥርዓት እና የደመር ለቅሶ ሥነ ሥርዓት ውጭ አገር የሚኖሩ ልጆቻቸው በቪዲዮ እንዲቀረፅ ማድረጋቸውን አውቅ ስለነበር፣ ቤተሰብን አስፈቅጄ ወደ ሲዲ በማስገልበጥ ለዚህ ጥናት እንደማጠናከሪያነት ተጠቅሜበታለሁ።

በጥቅሉ በዚህ ጥናት የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀምን የሚያሳዩ (አንድ እኔ የቀረፅኩት፣ አንድ ወንድሜ ያስረቀረፀልኝ፣ አንድ ከዘመድ ያገኘሁት) ሶስት የቪዲዮ

ካሴቶችን፣ ከመረጃ አቀባዮች ጋር የተደረገው ኢንተርቪው የተቀረፀባቸው እያንዳንዳቸው 90 ደቂቃ መቅዳት የሚችሉ አስራ አንድ ካሴቶችን፣ 145 ፎቶግራፎችን ተጠቅሜያለሁ።

## 1.6 የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት መሠረት ያደረገው የአጠናን ዘዴ ገላጭ ዘዴን (Descriptive Method)ን ነው። ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ዘዴው፣ የአንድን ክስተት ወቅታዊ ሁኔታ በግልፅ በማሳየት ላይ ስለሚያተኩር እና ክስተቱን ባለበት ተፈጥሯዊ መቼት ስለሚመረምር፣ እንዲሁም በተፈጥሯዊ መቼት በተገኙት መረጃዎች ላይ ተነስቶ ትንታኔዎችን ለመስጠት ስለሚረዳ ነው። በመሆኑም የቀብር ሥነ ሥርዓት ተፈጥሯዊ መቼት ላይ ተገኝቼ መረጃዎችን በመሠብሰብ፣ በመመደብና በመተንተን ላይ ትኩረቴን ስላደረግሁ ይህንን የጥናት ዘዴ ተጠቅሜያለሁ።

## 1.7 የናሙና አወሳሰድ

በዚህ ጥናት ታላሚ ንሞናን (purposive sampling ን) በመጠቀም ስለ ቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በቂ እውቀትና ልምድ አላቸው የተባሉ ሃይማኖታዊ ሰዎችን፣ አዛውንቶችን፣ ፎካሪዎችንና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሌሎችንም አካላት በመምረጥ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ።

## 1.8 የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ውጤት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። ከነዚህም መካከል:-

1. የወረዳው ህዝብ ከዚህ ጥናት ተጠቃሚ ይሆናል። ምክንያቱም በሌላው ሰው ባህሉ እንዲታወቅ ያግዘዋልና ነው።
2. ከዋኞች ተጠቃሚ ናቸው። በጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ እየተገኙ የጀግኖችን የቀብር ሥነ ሥርዓት በፉከራና በቀረርቶ የሚያደምቁ ቁልፍ ከዋኞችን በስራቸው እንዲተጉ ያበረታታል።

3. የወረዳው እና የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ይኸውም የነዚህ ቢሮዎች የስራ ኃላፊነት በአካባቢያቸው የሚከናወኑ ባህል ነክ ጉዳዮችን መሰብሰብ፣ ማጥናትና በስርዓት መሰነድ በመሆኑ፡፡

## 1.9 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በላይ አርማጭሆ ወረዳ በሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ በሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው ላይ ትኩረት ሰጥቶ የተካሄደ ነው፡፡

## 1.10 የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ፣ የአጠናን ዘዴ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች በሥሩ ተካተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ተደርጓል፡፡ በምዕራፍ ሶስት ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራ ተገልጿል፡፡ በምዕራፍ አራት በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረገው የቀብር ሥነ ሥርዓትና በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ ፉከራ እና ክዋኔው ተተንትኗል፡፡ በምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና ይሁንታ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም አባሪዎች ተያይዘዋል፡፡

## 1.11 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይህን ጥናት በማካሂድበት ወቅት በጣም የከፋ ችግር አላጋጠመኝም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የታሰበውን የጥናት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥረት በማደርግበት ወቅት የተከሰቱ መጠነኛ ችግሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ከገጠሙኝ ችግሮች መካከል፣

1. ጥናቱ የሚካሄድበትን አካባቢ ዳራ ለመግለፅ የሚያስችል የመረጃ እጦት ትልቁና ዋነኛው ችግር ነበር፡፡ ይህም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የወረዳው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለምሳሌ፣ የወረዳው የማስታወቂያና የመረጃ ቢሮ፣ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የወረዳው አስተዳደር ዋና ጽህፈት ቤት፣ ወዘተ. ከጥናቱ ጋር የተያያዘ ስለወረዳው ምንም መረጃ የሌላቸው መሆናቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ከወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽህፈት ቤት ቢሮና ከወረዳው ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ቢሮ ውስን መረጃዎች የተገኙ ቢሆንም፣ ከየመስሪያ ቤቶቹ የተገኙት መረጃዎች የተለያዩ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ የወረዳውን የህዝብ ብዛት በተመለከተ ከወረዳው ግብርናና ገጠር

ልማት ጽህፈት ቤት ቢሮ የተገኘው መረጃ 181,101 እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ከወረዳው ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ቢሮ የተገኘው መረጃ ደግሞ 166,103 እንደሆነ ይገልፃል፡፡ በሌላ በኩል የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ቢሮ እ.ኤ.አ የ2007 የህዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት ሪፖርት ደግሞ የወረዳውን የህዝብ ብዛት 157,797 እንደሆነ ገልጿል፡፡

ለነዚህ ችግሮች የተወሰዱት የመፍትሄ እርምጃዎች፣ ወደ ዞኑ የአቅም ግንባታ ዋና ጽህፈት ቤት (ጐንደር) በመሄድ መረጃ በመጠየቅ ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ከህዝብ ብዛት ጋር ተያይዞ ለተፈጠረው ችግር ደግሞ ማዕከሉ ጉዳዩ የሚመለከተው በመሆኑና ከወረዳው ቢሮዎች በተሻለ መረጃው በጥናት የተረጋገጠ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ቢሮ ሪፖርት ውጤትን መውሰድ ነው፡፡

2. የማህበረሰቡ አባላት ስለ ሥነ ሥርዓቱ በሚጠየቁበት ወቅት ተገቢ መልስ በመስጠት የተባበሩኝ ቢኖሩም፣ በአንፃሩ ደግሞ አንዳንዶች ለእንዲህ አይነቱ ተግባር ትኩረት የማይሰጡ ሆነውብኝ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ የኢንተርቪው ቀጠሮ ቀን ለመወሰን ስንነጋር፣ "ነገ እንገናኝ ዛሬ አይመቸኝም" የሚል መልስ ሲሰጡ፣ "ነገ ስንት ሰዓት? የት ድረስ ልምጣ?" ስላቸው፣ "ነገ እሚሆነው ምኑ ታውቆ፤ እስቲ ዛሬን ቸር እንደር" በማለት ይመልሱልኝ የነበሩ ብዙ ናቸው፡፡

ይህን ችግር ለመቀነስ የወሰድኩት የመፍትሄ እርምጃ ሰዎች የሚሰባሰቡባቸውን ቀናት እየጠበቅሁ፣ የሚሰባሰቡባቸው ቦታዎች ድረስ በመሄድ የምፈልጋቸውን ሰዎች ማግኘት ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ የሰንበት፣ የስላሴ፣ የሚካኤል፣ ወዘተ. ማህበር ለመጠጣት ቤታቸው ወይም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሲሰባሰቡ፣ እንዲሁም ጠላ ቤቶች እና ፀበል መጠመቂያ ቦታዎች በመሄድ መረጃ አቀባዮችን ማግኘት ችያለሁ፡፡ በአንፃሩ ማህበር የሚጠጡበትን ቀን ጠብቄ ቦታው ድረስ በመሄድ የምፈልጋቸውን ሰዎች አግኝቼ መረጃ መሰብሰብ እንደጀመርኩ ብዙዎቹ ጠጥተው እየሰከሩ በተገቢው መንገድ፣ ተገቢ መልስ የማይሰጡኝም ነበሩ፡፡

3. "የቅድመ ሞት ዝግጅት" በሚለው የዚህ ጥናት ንዑስ ርእስ ሥር የተገለፁትን ድርጊቶች ሲከወኑ ለማየትና በቪዲዮ ለመቅረፅ፣ ፎቶም ለማንሳት አጋጣሚ አለማግኘት ሌላው ችግር ነበር፡፡ ለዚህ ችግር የተወሰደው የመፍትሄ እርምጃ፣ ስለ

ሥነ ሥርዓቱ ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ አስመልክቶ የተለያዩ የማህበረሰቡ አባላትን በመጠየቅና ራሴ የማውቀውንም በማከል ክፍተቱን መሙላት ነው፡፡

4. የቀብር ሥነ ሥርዓቱን፣ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔን በምቀርፅበት ወቅትም ቀረፃው በከዋኖች ላይ የፈጠራቸው አንዳንድ ተፅእኖዎች ነበሩ፡፡ ለመቀረፅና ፎቶግራፍም ለመነሳት ሲሉ ፎክረው የማያውቁት ሁሉ ለመፎከር ይጥሩ ነበር፡፡ አንዳንድ እውቅ ፎካሪዎችም ቀረፃው ባሳደረባቸው ተፅእኖ ምክንያት በባህርይው የማይደጋገም አንድን ስንኝ ሶስት አራት ጊዜ ይደጋግሙት ነበር፡፡ ለዚህ ችግር የተወሰደው የመፍትሄ እርምጃ፣ ከአጠገባቸው መራቅና በ"Zoom" በማቅረብ ቀረፃ ማካሄድ ነበር፡፡

5. የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ክዋኔ በቪዲዮ መቅረፅም ሆነ ፎቶግራፍ ማንሳት ሃዘንተኞችን እንደመናቅና በሃዘናቸውም እንደመደሰት ስለሚቆጠር እንዳልቀርፅ በሟች ቤተሰቦች ተከልክየ ነበር። ይሁን እንጅ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ቁስ ቆመው ከለመኑ የማይደረጉ ነገሮች ሁሉ እንዲደረጉ ማህበረሰቡ እንደሚፈቅድ አውቅ ስለነበር የሟቹ የነፍስ አባት እንዲለምኑልኝ በማድረግ የሥነ ሥርዓቱን ክዋኔ መቅረፅ ችያለሁ፡፡

ሌላው የመስክ ገጠመኝ ምንም እንኳ በአካባቢው ተወልጄ ያደግሁ ቢሆን፣ አንዳንድ የማህበረሰቡ ልማዶችን በመዘንጋት የተፈጠረ ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ በተለይም በገጠር ቀበሌዎች ዘንድ የሚተዋወቁም ይሁኑ የማይተዋወቁ ሰዎች በመንገድ ላይ ሲገናኙ ሰላምታ የመለዋወጥ ልማድ አላቸው፡፡ እኔም የዘነጋሁት ይህንኑ ነበር፡፡ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም አንድ ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አሉ ወደተባለበት የሰንበቴ ማህበር መረጃ ለመሰብሰብ ስሄድ በመንገድ ላይ አንድ መንገደኛ አገኙኝና "ደህና ዋልክ?" አሉኝ፡፡ እኔም "ደህና ነኝ፤ እንደምን ዋሉ?" በማለት ሰላምታ ሰጠኋቸው፡፡ ትንሽ እንደተጓዙ ለኔ በሚሰማኝ አኳኋን፣

ደህና ዋልክ ብለው ደህና ነኝ አለኝ
የእግዜሩ ሰላምታም ሊቀር ነው መሠለኝ

በማለት ገጠሙ፡፡ ለካ "ደህና ዋልክ?" ሲሉኝ፣ "እግዚአብሔር ይመስገን" ብዬ መመለስ ነበረብኝ፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በላይ አርማጭሆ ወረዳ በሚከናወን የቀብር ሥነ ሥርዓትና በሥርዓቱ ላይ በሚደረግ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው ላይ የተደረገ ጥናት አልተገኘም፡፡ ነገር ግን በመነሻነት ያገለገሉኝ አስራ አምስት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች(ሁሉም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ተማሪዎች የተሰሩ ናቸው) እና ሦስት ለተለያዩ ሴሚናሮች የቀረቡ በድምሩ አስራ ስምንት ተዛማጅ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ ሶስቱ ለሴሚናር የቀረቡት ጥናቶች በነጋ ተሠማ፣ በፋሲካ በለጠ፣ በአስመላሽ ወ/ማርያምና በጽጌረዳ ተክሌ የቀረቡ ናቸው፡፡

ሁሉንም ጥናቶች በመጀመሪያ በሚያነሱት ርዕሠ ጉዳይ ተመሳሳይነት መሠረት ለጥናቱ አመቺ በሆነ መንገድ ለመመደብ ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት የለቅሶ ስርዓትንና ሙሾን ያጠኑ፤ የለቅሶ ስርዓትን፣ ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ፤ የለቅሶ ስርዓትን ብቻ ያጠኑ፤ ቀረርቶንና ፉከራን ብቻ ያጠኑ ብሎ በመመደብ፣ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በተመሳሳይ ዘመን ከተጠኑ ጥናቶች በስተቀር አቀራረባቸው እንደየተጠኑበት ዘመን ቅደም ተከተል ነው፡፡

#### 2.1.1 የለቅሶ ስርዓትንና ሙሾን ያጠኑ

ሐረገወይን ድፋባቸው (1974)፣ "የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ ጥናቷ "የህብረተሰቡን የለቅሶ ሁኔታ ለማሳወቅና ለታሪክ ማስረጃነት እንዲጠቅም ለማድረግ" የሚሉ ነጥቦችን ዓላማ አድርጕ ተነስቷል፡፡ ሶስት ምዕራፎችም አሉት፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ ብሔረሰቡ ተገልጾበታል፤ የሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በስርዓቱ ላይ ወንዶችና ሴቶች ያላቸውን ሚና በመግለጽ፣ የቀብር ሥርዓቱ እንደሚቹ ትውልድ፤ ጾታና ሙያ እንዲሁም ዕድሜ እንደሚለያይ ተጠቁሞበታል፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍም የሙሾ ግጥሞች ይዘት ተተንትኖበታል፡፡ የሙሾ ግጥሞች የተተነተኑበት መንገድ (በፆታ፣ በእድሜ፣ በሙያ የመመደብ ዘዴ) ለሌሎች አጥኚዎች በመነሻነት ሊያገለግል የሚችል ነው፡፡

የጥናቷ ርዕስ ጉዳይ ባይሆንም በዚህ ጥናት የተገለጸው የቀብር ሥርዓት ለየትኛው የማህበረሰቡ ክፍል የሚደረግ እንደሆነ፣ የቀብር ሥርዓቱ እንደሚቹ ሙያ የሚለያይ መሆኑ ቢገለጽም በብሔረሰቡ የቀብር ስርዓት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሙያዎች የትኞቹ እንደሆኑ የተገለጸ ነገር የለም።

ድጋፌ ፈይሳ (1975)፣ "የሲዳማ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል። ድጋፌ በስራው አንድ አረጋዊ (ጨሜሳ) ሲሞት የሚደረገውን የቀብር ሥርዓት አፈፃፀም ቅድመ ቀብር፣ ቀብር፣ እና ድህረ ቀብር ብሎ በመከፋፈል አሳይቷል። የሙሾ ግጥሞችን ይዘት እና ቅርጽም ተንትኗል። ድጋፌ የሙሾ ግጥሞችን ከአድሜ ባለጸጋዎች በሚሰበስብበት ወቅት ፊውዳሊዝምንና በወቅቱ የነበሩ ጭቃ ሹሞችን የሚያወድሱ የሙሾ ግጥሞችን "ስርዓቱ በወደቀበት ዘመን መናገር ያስቀጣል" በማለት ቆርጠው ለማውጣት ይሞክሩ እንደነበር ጠቁሟል። በተጨማሪም በብሔረሰቡ ልማድ መሠረት በሰላም ጊዜ ሙሾ መናገር ሟርት ነው ተብሎ እንደሚታመን የሠጠው ፍንጭ፣ በሌሎች ማህበረሰቦች ላይ ጥናት ለማድረግ ለሚያስቡ ሰዎች ለችግሩ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚረዳ ነው። ድጋፌ በጥናቱ ያሳየው በማህበረሰቡ ለአንድ አረጋዊ የሚደረገውን የቀብር ሥርዓት አፈፃፀም ብቻ ነው።የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ለማሳየት የአንድ አረጋዊ የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀምን ለምን እንደመረጠ የገለጸው ነገር የለም። ለአንድ አረጋዊ የሚደረገው የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ብቻም የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርዓት በሙሉ ሊወክል ይችላል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው።

አስመላሽ ወ/ማርያምና ጸጌረዳ ተክሌ (1980)፣ "በትግርኛ የለቅሶ አጋጣሚ የሚተላለፉ መልዕክቶች" በሚል ርዕስ፣ ሁለቱ ባንድነት በየኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓመታዊ ሴሚናር ጥናት አቅርበዋል።

አጥኚዎቹ በዚህ ስራ «... የለቅሶ አጋጣሚ» በማለት ማሳየት የፈለጉት የሙሾ ግጥሞች የመከወኛ ምክንያት የለቅሶ ስርዓቶች በተለይም የቀብር ሥርዓት፣ ሟችን ለማስታወስ የሚደረጉ ስርዓቶች (አርባና ሙት ዓመት) መሆናቸውን ነው።

በለቅሶ ምክንያት አልቃሾች የሚያነሱዋቸው ግጥሞች ሟችን በተመለከተ ብቻ የሚገጠሙ አለመሆናቸውን፣ የህብረተሠቡ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንደሚያንጸባርቁ አንዳንድ የሙሾ ግጥሞችን በምሳሌነት በመጥቀስ አመልክተዋል።

መዓዛ ተስፋይ (1982)፣ "በዓጋመ አውራጃ የቀብር ሥርዓት አፈፃፀምና የለቅሶ ግጥሞች የይዘት ትንተና" የሚል ጥናት አካሂዳለች። ስራዋ በቀብር ሥርዓት አፈፃፀም ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን "የሁለተኛ የቀብር ሥነ ሥርዓት" አፈፃፀምንም ያሳያል። ይህ "ሁለተኛ የቀብር ሥነ ሥርዓት" ተብሎ የተገለፀው ጉዳይ በሌሎች የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዘንድ፣ በተለይም በአማራ ክልል በአንዳንድ አካባቢዎች ከሚደረገው "የደመር ለቅሶ ስርዓት" ጋር የሚመሳሰል ነው።

በዚህ ጥናት በአብዛኛው የሙሾ ግጥሞች የሚደረደሩት (በአርባና በሙት ዓመት ከሚደረደሩት በተሻለ) በነዚህ ስርዓቶች (በቀብርና በሁለተኛ ቀብር) ላይ እንደሆነ በመጥቀስ የግጥሞቹን ይዘት ተንትና አሳይታለች። በመጨረሻም የሙሾ ግጥም ስብስብ ከነአማርኛ ፍቺው በአባሪነት አያይዛለች።

በዚህ አውራጃ የሚደረገው የቀብር ስርዓት አፈፃፀም በእድሜ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ. ተለይቶ በግልፅ ስላልተቀመጠ የአውራጃውን የቀብር ሥነ ሥርዓት በደንብ ለመረዳት የሚያስችል አይመስለኝም።

ጥላሁን ኢቢዶ (1982)፣ "የጌዴኦ ኅብረተሰብ የልቅሶ ሥርዓት" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል። አጥኚው በጥናቱ በህብረተሰቡ ለቅሶ ስርዓት ውስጥ "ጉልህ ድርሻ አለው" ስላለው የጌዴኦ የገዳ ስርዓት ማብራሪያ ሰጥቷል። ይህንን የገዳ ስርዓት መሠረት በማድረግ የለቅሶ ስርዓቱን በእድሜ ለህፃን፣ ለወጣት፣ ለጐልማሳ፣ ለአረጋዊ የሚደረግ፣ በፆታ ደግሞ ለወንዶችና ለሴቶች የሚደረግ በማለት ለያይቶ ፅፏል። የሙሾ ግጥሞችንም ተንትኗል።

በዚህ ጥናት አጥኚው የማህበረሰቡን የእድሜ ደረጃዎችም ሆነ የፆታ አይነቶች በማህበረሰቡ ቋንቋ የገለፃቸው በመሆኑ (በተለይ በጥናቱ የርዕስ ማውጫ ክፍል) ጥናቱን በቀላሉ ለመከተል ያስቸግራል። ምንም እንኳ፣ በጥናቱ መጨረሻ ክፍል የቃላት መፍቻ ያዘጋጀ ቢሆንም፣ በርዕስ ማውጫ ክፍሉም አቻ ትርጉማቸውን ቢያስቀምጥ ችግሩን ያቀለው ነበር።

አየለ መሎሬ (1986)፣ "የሀዲያ ህብረተሠብ የለቅሶ ሥርዓት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል። የህብረተሠቡን የለቅሶ ስርዓት ሂደት "ቅድመ ቀብር» እና "ቀብር" በማለት ከለየ በኋላ፣ በየሂደቶች "ከልደት እስከ ሙሽርና ለደረሡ»፣ «ለአዛውንት" በማለት መድቦ የህብረተሠቡን የለቅሶ ሥርዓት አሳይቷል። አየለ "ቅድመ ቀብር" በማለት የገለፃቸው ተግባራት ማንኛውም ሠው ከመሞቱ በፊት (በሽታው ጸንቶ እንደማይድን ሲገመት ለማለት

ነው) ህብረተሠቡ የሚያደርጋቸውን ቅድመ ዝግጅቶች ነው። ከነዚህም ቅድመ ዝግጅቶች መካከል ለቀብር ቀን የሚሆን የምግብ እና የመጠጥ ዝግጅት ይጠቀሳል።

እዚህ ላይ "ቅድመ ቀብር" የሚለውን ሀሳብ በተገቢው መንገድ የተጠቀመበት አይመስለኝም። ቀብር ማለት ግለሠቡ ከሞተ በኋላ ያለውን ሥርዓት የሚገልጽ እንጂ ከዚያ በፊት (ሳይሞት) ያለውን ስርዓት ሁሉ የሚገልጽ አይደለም። በተጨማሪም በዚህ ቅድመ ቀብር ሥርዓት ወቅት እንደሚለቀስ ስላላመለከተ ቅድመ ቀብር ዝግጅቱ የለቅሶው አንድ ገጽታ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም።

ወርቁ ማንደፍሮ (1987)፣ "በሊቦከምከም ወረዳ የለቅሶ ሥነ ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች" በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄደ ሲሆን ጥናቱ በአካባቢው አንድ ሰው ከሞተበት ጊዜ አንስቶ እስኪ ቀብር ድረስ ያለውን አጠቃላይ ክንውንና የተወሠኑ የሙሾ ግጥሞችን ተንትኗል። በትንታኔው መሠረት የሙሾ ግጥሞችን ለወጣት፣ ለሽማግሌ፣ ለእናት፣ ለእህት፣ ለወንድም፣ የሚደረደሩ በማለት መድቧል። ጥናቱ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዩን ማህበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ብቻ የሚወክል እንደሆነ መግለጹ ከዚህ በላይም ይሁን ቀጥሎ ከምናያቸው ጥናቶች የተለየ ጥንካሬው ነው።

የሙሾ ግጥሞችንም በይዘት ከፋፍሎ ማስቀመጡ ሌላው ጠንካራ ገጽታው ቢሆንም፣ ደካማ ጐንም አለው። ይኸውም አጥኚው ራሱን በአብዛኛው እንደዋና የመረጃ ምንጭነት በመጥቀስ ያቀረበበት መንገድ ነው። በጥናት ጊዜ ራስን እንደዋና የመረጃ ምንጭነት መጠቀም የሚቻል ቢሆንም፣ አብዝቶ መጠቀም ግን የጥናቱን ሚዛናዊነት ሊያዛባ እንደሚችል ምሁራን ያሳስባሉ (ለምሳሌ፣ ፈቃደ አዘዘ፣ 1999፣6)።

እስካሁን ባየናቸው ተዛማጅ ጥናቶች (ቀጥሎ የምናያቸውን እስከ 1990ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ገደማ ያሉትንም ይጨምራል) ውስጥ የሚታይ አንድ የጋራ ባህርይ አለ። ይህም ጥናቶቹ ስለዓላማቸው፣ ስለዘዴያቸው፣ ስለዳራቸው፣ ስለወሠናቸው፣ ወዘተ. የገለጹበት ራሱን የቻለ ምእራፍ የሌላቸው መሆኑ ነው። አንድ ጥናት እነዚህን ነጥቦች በግልጽ ካላሳየ ደግሞ ይዞት የተነሳውን ዓላማ፣ በመረጠው የጥናት ዘዴ ከግቡ ያድርስ አያድርስ ለመገምገም እንቅፋት ይሆናል። እኔም ጥናቶቹን ስቃኝ የገጠመኝ ችግር ይኸው ነበር።

ወርቃየሁ አረጋ (1995)፣ "የአዊ ህብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርዓት) እና የአውኚ ዚንዚምኚ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች።

ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱን ዘዴ፣ የጥናቱን ወሠንና የጥናቱን አስፈላጊነት አስተዋውቃለች። በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ተዛማጅ ጽሑፎችን ቃኝታለች። በሶስተኛው ምዕራፍ የህብረተሰቡን የለቅሶ ስርዓት አሳይታለች። በአራተኛው ምዕራፍ ደግሞ የሙሾ ግጥሞችን በመተንተን ግጥሞችን ለወንዶች (አባት፣ ወንድም፣ ልጅ) ሲሞት የሚገጠሙ፣ ለሴቶች (እናት፣ እህት) ስትሞት የሚገጠሙ በማለት መድባለች። በመጨረሻም የሙሾ ግጥሞች ስብስብ ከነአቻ ትርጉማቸው አባሪ አድርጋለች። ይህ ጥናት ዓላማ ካደረጋቸው ጉዳዮች አንዱ "የማህበረሰቡን የለቅሶ ሥርዓት ለማሳየት" የሚል ነው። ይሁን እንጂ ጥናቱ ሙሾ ከሚደረግበት አጋጣሚ የቀብር ስርዓትን እንደመነሻ አድርጐ፣ ሥርዓቱን "ከቀብር በፊት"፣ "የቀብር ሥነ ሥርዓት" እና "ከቀብር በኋላ" በማለት አትቷል። ይህ ዓይነት የቀብር ሥነ ሥርዓት ለየትኛው የህብረተሠቡ አካል የሚፈጸም እንደሆነም የተባለ ነገር የለም። በመሆኑም የጥናቱን ዓላማ ከግብ አላደረሰም።

ዘላለም ኢዮብ (1995)፣ "በጐፋ ብሔረሠብ ባህላዊ ለቅሶ (ዬሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነግጥማዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል። ጥናቱ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ዓላማዎች፣ የጥናቱን ወሠን፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ ወዘተ. አስተዋውቋል። በሁለተኛው ምዕራፍ ተዛማጅ ጽሑፎችን ቃኝቷል። በሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የብሔረሰቡን ማህበረባህላዊና ልማዳዊ ገጽታዎች አንስቷል። በአራተኛው ምዕራፍ ለብሔረሰቡ አባላት የሚደረገውን የለቅሶ ሥነ ሥርዓት ለህፃን፣ ለወጣት፣ ለጐልማሳ፣ ለአዛውንት፣ የሚደረግ የአለቃቀስ ሥነ ሥርዓት በማለት በእድሜ ከፋፍሎ አሳይቷል። ዘላለም በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ህፃናትና አዛውንቶች ሲሞቱ ብዙ እንደማይለቀስ፣ ወጣቶችና ጐልማሶች ሲሞቱ ደግሞ በጣም እንደሚለቀስ፣ በሙሾ ግጥሞች ውስጥ የሚንጸባረቁ ዘይቤዎች "አነፃፃሪና ለዋጭ" ዘይቤዎች መሆናቸውን በመግለጽ ጥናቱን ደምድሟል። ዘላለም የብሔረሰቡን የለቅሶ ልማድ ሲገልጽ፣ የለቅሶው አደረጃጀት መሃል ላይ ከወገብ በላይ ርቃናቸውን ሆነው ከበሮ (ዳርቤ) የሚመቱ ሁለት ሰዎችን ተከትሎ ክብ በመስራት እንደሚለቀስ፣ አንበሳ፣ ነብር ለገደሉ የማህበረሰቡ አባላት ጦርና ጋሻ ተይዞ እንደሚለቀስላቸውና የሙሾ ግጥሞችን የሚደረድሩላቸው ወንዶች ጓደኞቻቸው እንደሆኑ ገልጿል። ወንዶች ጓደኞቻቸው ለምን እንደሚደረድሩ እና እንዴት አድርገው እንደሆነ፣ የቁሶች አገልግሎት ምን እንደሆነ ግን የተናገረው ነገር የለም። ይህ ካልሆነ ደግሞ ጥናቱ የተሟላ አይሆንም። ምክንያቱም የጥናቱ ርእስ «...ክዋኔ» ይላልና።

ፈለገ ህይወት ዘገዬ (1997)፣ "በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ሥነ ሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና" የሚል ጥናት አድርጋለች። ይህ ጥናት "የባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ አጭር ዳራ" ብላ ከገለጸችው ሃሳብ ውጭ በዓላማውና በአጠቃላይ ይዘቱ ከላይ ከተጠቀሰው የወርቃየሁ ጥናት ጋር በእጅጉ የሚቀራረብ ነው። በተለይ በጥናቱ ሁለተኛ ምዕራፍ "የባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነ ስርዓት አፈፃፀም" በማለት የገለጸችው ሀሳብ፣ ወርቃየሁ በጥናቷ ሶስተኛ ምዕራፍ "የአዊ ህብረተሠብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርዓት)" በማለት የገለጸችው ሃሳብ ቃል በቃል የተደገመበት ነው። ወርቃየሁ ጥናቷን ያካሄደችው በ1995 ዓ.ም ሲሆን ፈለገ ህይወት ደግሞ በ1997 ዓ.ም ነው። ይህ ደግሞ የኋለኛዋ አጥኚ ከቀዳሚዋ አጥኚ "ሃሳብ የሰረቀች" መሆኗን ይጠቁማል።

ሽመልስ አክሊሉ (1997)፣ "የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓትና የግጥሞች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል። የሽመልስ ጥናት ሶስት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ወዘተ. የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ምዕራፍ ተዛማጅ ጽሑፎች የተቃኙበት ነው። ሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የማህበረሰቡን የለቅሶ ሥነ ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞችን ተንትኖ ያመለከተበት ነው። ሽመልስ ያተኮረው በማህበረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ላይ ሳይሆን በሙሾ ግጥሞች ትንተና ላይ ነው። የጥናቱ አጠቃላይ የገጽ ብዛት ሰላሳ ሁለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሙሾ ትንተናው አስራ ሰባት ገጽ ነው።

### 2.1.2 የለቅሶ ሥርዓትን፣ ሙሾን፣ ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ

ንጉሴ አክሊሉ (1974)፣ "ለጀግኖች ለቅሶ የሚደረደሩ ግጥሞች (ምንጃርና ሸንኮራ አካባቢ)" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል።

ይህ ጥናት ስድስት ምዕራፎች አሉት። በመጀመሪያው ምዕራፍ የስነቃልን አመጣጥ፣ ምንነትና ጥቅም ይገልፃል። በሁለተኛው ምዕራፍ በስነቃሎች ስብሰባ ወቅት ከአቀባዮች የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ለጀግኖች የሚዜሙ ግጥሞች (ሙሾዎች፣ ቀረርቶዎችና ፉከራዎች) በወንዶች ብቻ የሚዜሙ መሆናቸውን ይጠቁማል።

በሶስተኛው ምዕራፍ የሙሾዎችን የግጥም አወራረድ "ከተለያዩ አዝማቾች አኳያ" በማለት አቅርቧል። "አዝማች" ምን ማለት እንደሆነ የተገለጸ ነገር ባይኖርም አጥኚው የሙሾ ግጥሞችን አወራረድ ተከትሎ ስብስቡን ለመመደብ የተጠቀመበት ስልት እንደሆነና ስልቱ ሙሾ አውራጁ የሙሾ ግጥሙን ሲደረድር ተቀባዮቹ ያንኑ ግጥም ቃል በቃል በመድገም

(በመቀባበል) የለቅሶ ስርዓቱን የሚያስኬዱበት ስልት እንደሆነ፣ በየምድቡ ስር ካሠፈራቸው የሙሾ ግጥሞች በመነሳት መገመት ይቻላል። ይሁን እንጂ አጥኚው ይህንን የአመዳደብ ስልት ለምን እንደተጠቀመ ያስቀመጠው ምክንያት የለም። ምክንያቱን ባለማስቀመጡም ጥናቱን ለመከተል ያስቸግራል።

በአራተኛው ምዕራፍ ለጀግኖች የሚገጠሙ ግጥሞችን በመውሠድ፣ ለሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ከሚገጠሙት ግጥሞች የሚለዩበትን መንገድ (ያነጻጸራቸው ለሴባ፣ ለሰነፍ፣ ወዘተ. ከሚገጠሙት ግጥሞች ጋር ነው) ሲገልጽ፣ በአምስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ለጀግኖች የሚገጠሙትን ግጥሞች ይዘት ተንትኗል። በስድስተኛው ምዕራፍም የግጥሞችን ቅርጽና ዘይቤያዊ አጠቃቀም አሳይቷል። በመጨረሻም የግጥም ስብስቦች በአባሪነት ቀርበዋል። አጥኚው ጥናቱን ባደረገበት ማህበረሰብ ዘንድ ጀግና የሚባሉት የማህበረሰብ አባላት ዘማቾችና አዳኞች ብቻ መሆናቸውን አመልክቷል።

በነዚህ ሰዎች የለቅሶ ስርዓት ወቅት የሙሾም ሆነ የፉከራና የቀረርቶ ግጥሞችን የሚደረድሩ ሰዎች ማንነት በገጠርና በከተማ የሚለያይ ሆኖ እንዳገኘው ጠቁሟል። ይኸውም ጥናቱን ባካሄደባቸው ገጠራማ አካባቢዎች እነዚህ ግጥሞች የሚደረደሩት በወንዶች በተለይ በሚቴ ጓደኞች መሆኑን፣ በከተማ አካባቢዎች ግን በሴቶችም ሲደረደሩ ማየቱን ገልጿል። ግጥሞች በሁለት ፆታዎች ሲደረደሩ የተፈጠረውን ክፍተት ግን አልገለጸም። በተጨማሪም አጥኚው መረጃውን የሰበሰበው ከምንጃርና ሸንኮራ ወረዳዎች፣ ከሙክዬ፣ ከቦስት፣ እንዲሁም ከናዝሬት መሆኑን በጥናቱ አመልክቷል። "ምንጃርና ሸንኮራ አካባቢ" ብሎ ተነስቶ ናዝሬት (አዳማ) ለምን እንደሄደ የተገለጸ ምክንያት የለም። ይህ ደግሞ ጥናቱ በርዕሱ ከተገለጸው አካባቢ የወጣ አድርጎታል።

ጌጡ ታደሠ (1986)፣ "ክዋኔ በጐንደር ከተማ ለቅሶ ስነ ስርዓት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል።

ጌጡ በጥናቱ በጐንደር ከተማ የሚደረጉትን የለቅሶ ሥርዓት ዓይነቶች የዕለት ለቅሶ (የቀብር ለቅሶ ማለቱ ነው)፣ የመርዶ ለቅሶ፣ የደመር ለቅሶ፣ በማለት መድቦ ክዋኔያቸውን አመልክቷል። እነዚህን የለቅሶ ሥነ ሥርዓት ዓይነቶች ለባላባትና ለባለፀጋ ሰው፣ ለደሃ ሰው፣ ለጀግና ወይም ለታዋቂ ሰው (በአንድ ዐረፍተ ነገር ብቻ ጀግና የሚባሉት ሰዎች ዘማቾችና በአደባባይ ችሎት ተሟግተው የረቱ መሆናቸውን ገልጿል)፣ ለመንፈሳዊ ሰው፣

የሚደረግ በማለት ከማህበራዊ ደረጃ አንፃር ለይቶ፣ ክዋኔያቸውን አመልክቷል። ለነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚደረገውን የቀብር ሥነ ሥርዓትም አስከሬን ከቤት ሳይወጣ፣ በጉዞ ፍታት ወቅት፣ በአፀደ ቤተ ክርስቲያንና በግብዓተ መሬት ወቅት በማለት የሚደረገውን ሥርዓት ገልጿል። በመጨረሻም በጐንደር ከተማ የለቅሶ ክዋኔ እንደሚቱና እንደወገኖቹ ማንነት እንደሚለያይ፣ ማለትም ባላባትና ባለፀጋ፣ ጀግናና ታዋቂ ሰው ሲሞት በርካታ ለቀስተኛ እንደሚገኝ፣ ሟቹን የሚያወድሱ የሙሾ፣ የቀረርቶና የፉከራ፣ ግጥሞች እንደሚገጠሙ፣ እርግዶም እንደሚደረግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ድርጊቶች ድሃ ሰው ሲሞቱ እንደማይደረጉ ገልጿል። በተጨማሪም ቀረርቶና ፉከራ በተለይም እርግዶ (በምን ምክንያት እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ አልተገለጸም) እየቀሩ በመምጣት ላይ እንደሆኑ በመግለጽ ጥናቱን ደምድሟል።

አጥኚው በከተማዋ የሚታዩትን ሁሉንም የለቅሶ ሥርዓቶች ለማሳየት ያደረገው ጥረት በጣም የሚደነቅ ነው። ይሁን እንጂ ርዕሱ ሠፊ ከመሆኑ የተነሳ ለእያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል የሚደረገው የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ በአግባቡ አልተገለጸም። የጥናቱ ርዕስ "ክዋኔ በጐንደር ከተማ ለቅሶ ስነ ስርዓት" የሚል ሆኖ በጥናቱ ውስጥ የተገለጸው የለቅሶ ስርዓት ግን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዩ ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ብቻ ነው። በመሆኑም የጥናቱን ወሠን በግልጽ ስላላስቀመጠ፣ የከተማዋ ነዋሪ በሙሉ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ነውን? ወይም ይህ የለቅሶ ስርዓት ለሁሉም የከተማ ነዋሪዎች የሚደረግ ነውን? የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልስ የሚሠጥ አይደለም።

ጥናቱ ያተኮረው በከተማዋ ለእያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል (የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነው) ሲሞት የሚደረግለትን ሥርዓት መግለጽ ላይ እንጂ እያንዳንዱ ድርጊት ለምን እንደሚደረግ አይነግረንም። ይህ ደግሞ የክዋኔውን ምልዓት ያጎድለዋል የሚል እምነት አለኝ። አንዳንድ አስረጂዎችን ከጥናቱ ውስጥ ልጥቀስ።

ገጽ 17 ላይ "የለቅሶ ክዋኔ አስከሬን ከቤት ሳይወጣ" በሚለው ንኡስ ርዕስ ስር "አስከሬን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የለቅሶ ክዋኔው ከቤት ውጭ ሰፋ ባለ ገላጣ ቦታ ላይ ይጀመራል። የተዘበራረቀው ለቅሶ ወደ ተቀናጀና ሥርዓት ወዳለው ለቅሶ ይቀየራል" የሚል ገለፃ አለ። ለቅሶውን ምኑ ነው የሚያቀናጀው? ከቤት ውጭስ ይለቀሳል፤ ከቤት ውስጥስ ምን ይደረጋል? የነገረን ነገር የለም። ለምሳሌ ያህል ይህን አነሳሁ እንጂ በጥናቱ ውስጥ ያሉት ስርዓቶች በሙሉ የተገለጹት በዚህ መንገድ ነው።

### 2.1.3 የለቅሶ ሥርዓትን ብቻ ያጠኑ

ነጋ ተሠማ (1953)፤ "The Death Customs in the Province of Tigre" በሚል ርዕስ "Ethnological Society Bulletin" በተባለ መጽሔት ጥናት አቅርቧል። ጥናቱ በትግራይ ክልል የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል ያሳያል። ጥናቱ በየትኛው ዞን፣ በየትኛው ወረዳ፣ ለየትኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት እንደሆነ ባይገልጽም፣ አንድ ሰው ከሞተበት እስከ ግብዓተ መሬቱ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ክንውን የሚያሳይ ነው። ርዕሱ ሰፊ በመሆኑ የተገለጸው የለቅሶ ሥርዓት የሁሉንም የትግራይ ማህበረሰብ ይገልፃል ብሎ መገመት ያስቸግራል።

በዚሁ መጽሔት በተመሳሳይ ዓመተ ምህረት "The Death Customs Among the Amharas of wa" በሚል ርዕስ፣ ፋሲካ በለጠ ጥናት አቅርቧል።

ይህ ጥናት የለቅሶ ሥርዓት፣ ከኑዛዜ ሥርዓት ጀምሮ፣ የመርዶው ሁኔታ፣ ለሟች የሚደረገው የፍታት ዓይነት፣ ወዘተ. በአጭሩ የተገለጸበት ነው። የጥናቱ ርዕስ "የሸዋ አማራዎች የለቅሶ ልማዶች" የሚል ቢሆንም፣ በየትኛው ወረዳ (የሸዋ ክፍል)፣ ለየትኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚከናወን እንደሆነ በግልጽ አልተቀመጠም።

### 2.1.4 ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ

ያቆብ ገብረኪዳን (1979)፣ "የጐንደር ቀረርቶና ፉከራ ይዘትና ክፍለ ሃገራዊ አሻራ" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል። አጥኚው ስሙን የፃፈው "ያቆብ" ብሎ ነው።

ጥናቱ መሠረት ያደረገው ክዋኔን አይደለም፤ ከጐንደር ከተማና ከአጐራባች ወረዳዎች የተሠበሠቡ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞችን ይዘት መመርመርን እንጂ። የግጥም ስብስቦችንም ጀግንነት፤ ሙያ፣ ፍራትና ስንፍና፣ ምሬትና ተቃውሞ፣ የወንድም አስፈላጊነት፣ ታሪክ የተገለጸባቸው በማለት በይዘታቸው ለያይቶ መድቧል። ከተለያዩ አካባቢዎች (ጐንደርና ጐንደር ዙሪያ) የተሠበሠቡ ዘጠኝ መቶ አስራ አራት (914) የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞችን በአባሪነት አያይዟል።ይህንን ያህል ግጥም ማሰባሰቡ አጥኚውን የሚያስመሰግን ታላቅ ስራ ነው።

ወርቁ ደቻሳ (1978)፣ "በወለጋ ክፍለ ሃገር፣ በሆሮ ጉድሩ አውራጃ የኦሮሞ ብሔረሠብ ቀረረቶ ግጥሞች ትንተና" የሚል ጥናት አካሂዷል።

ወርቁ በጥናቱ ቀረርቶን የደገኞችና የቆለኞች ቀረርቶ በማለት መድቧል። ለምደባው ያቀረበው ምክንያት ከደንና ከየዱር እንስሳት መኖር አለመኖር ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ቆለኞች በአካባቢያቸው ብዙ ደኖ ችና የዱር እንስሳት በመኖራቸው ምክንያት የአዳኝ ቀረርቶዎችን እንደሚያቅራሩ፤ በአንፃሩ ደገኞች ይህ ዕድል ስለሌላቸው በደቦ ስራ ወቅት እንደሚያቅራሩ ገልጿል።

ይህ አጥኚ በአፍሪካ ስነቃሎች ላይ ምርምር ያደረጉ፣ ሩት ፊነጋን የተባሉ ምሁርን አስተያየት "ጌረርሳ በጦርነት ጊዜ ብቻ ስሜትን ለመግለጽ የሚከናወን አድርገው ማቅረባቸው ልክ አይደለም" በማለት ነቅፏል። ለአስረጅነትም በአደን ጊዜ፣ በደቦ ጊዜ፣ በችግር ጊዜ፣ የሚዜሙ ቀረርቶዎችን በማቅረብ ግጥማዊ ቅርፃቸውን ጭምር (ከሀረጋት፣ ከቀለማት፣ ከቤት አመታት አንፃር) ተንትኖ አሳይቷል።

በዚህ አስተያየት ላይ ቅሬታ የለኝም። ቅሬታዬ የፊነጋንን ሀሳብ አስመልክቶ በሰነዘረው አስተያየት ላይ ነው። ፊነጋን "ጌረርሳ በጦርነት ጊዜ ብቻ የሚዜም ነው" አላሉም፤ "ጌረርሳ ወደ ጦርነትና ወደ አደን ሲኬድ፤ ከጦርነትና ከአደን መልስ የሚዜም ነው" አሉ እንጂ (ፊነጋን፤ 1970፣210)።

በየነ ለገሠ (1992)፣ "በምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ አርጆ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሠብ "ጌረርሳ" (ቀረርቶ) ዓይነቶችና አጫጭር ትንታኔ" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል።

በየነ ቀረርቶን በሶስት ጐራ መድቦ አጥንቷል። ይኸውም በዓይነት የልጆች (የልጆች ያላቸው እረኞች አዳኝ ሆነው ለመታወቅ ምኞታቸውን የሚገልጹባቸው ቀረርቶዎችን ነው)፣ የአዋቂዎች፣ ተብለው እንደሚመደቡ አመልክቷል። በይዘት ደግሞ ብሶትን፣ ደስታን፣ ሀዘንን፣ የሚገልጹ መሆናቸውን፣ በሚደረደሩበት ጊዜም ወደዘመቻና ወደ አደን ሲኬድ፣ ከዘመቻና ከአደን መልስ የሚደረደሩ፣ በማለት መድቧል። በየነ በዚህ ጥናት "ደገኞች በደቦ ስራ ብቻ ያቅራራሉ" የሚለውን የወርቁን ሃሳብ በመንቀፍ፣ ደገኞች በአደን ጊዜ (ወደ ቆላው ሲወርዱ)፣ በዓመት በዓል፣ ለብቻቸው ሲያርሱ፣ ሲያጭዱና ሲወቁ እንደሚያቅራሩ የሚገልጹ ግጥሞችን በአስረጅነት አቅርቧል።

በመጨረሻም የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በክልሉ እየተስፋፋ በመሆኑና የሃይማኖቱ ሰዎች በስመ "ዘፈን" ስነቃሎች (ቀረርቶን ጨምሮ) እንዳይዜሙና እንዲዘነጉ እያደረጉ በመሆናቸው፣ እነዚህ የህዝብ ሃብቶች ሳይጠፉ በየጊዜው እየተሠበሠቡ ቢጠኑ፣ በመማሪያ

መፃህፍት ዝግጅት ወቅት ቢካተቱ፣ ደራሲያን በድርሠቶቻቸው ቢጠቀሙባቸው፣ የመዝፈኑ ልማድ ሲቀር ቃልግጥሞቹም አብረው እንዳይቀሩ ሊያደርግ እንደሚችል ጠቁሟል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ቅኝት በተደረገባቸው ጥናቶች ውስጥ ጉልተው የሚታዩ ክፍተቶች የሚከተሉት ናቸው። ከነዚህም መካከል የየማህበረሰቡን የለቅሶ ሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች (የለቅሶ ግጥሞች የሚሏቸው ሙሾዎች፣ ቀረርቶዎችና ፉከራዎች ናቸው) ባጠኑ አጥኚዎች ዘንድ የርዕስ ስፋትና በዚሁ ምክንያት የተዛባ ድምዳሜ ላይ የመድረስ ችግር የመጀመሪያው ነው።

ይህም "የ--- ማህበረሰብ የለቅሶ ሥነ ሥርዓት" ብለው ይነሱና ትኩረታቸውን የቀብር ሥርዓት ላይ (ለዚያውም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዩ ማህበረሰብ ላይ) ብቻ አድርገው "ያጠናነው ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ይህ ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል።

አጥኚዎቹ በጥናታቸው ማሳየት የፈለጉት የማህበረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ሆኖ ሳለ፣ ምንም ምክንያት ሳያቀርቡ፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት የማህበረሰቡን የለቅሶ ሥርዓት ሊያሳይ እንደሚችል አድርገው አቅርበዋል። ለምሳሌ፣ ንጉሴ አክሊሉ፣ ነጋ ተሠማ፣ ፋሲካ በለጠ፣ ወርቃየሁ አረጋ፣ ፈለገ ህይወት ዘገዬ።

ይህ ደግሞ ምንም እንኳ ማህበረሰቡ እንደሚከተለው ሃይማኖት፣ ወግና ልማድ የሚለያይ ቢሆንም፣ የለቅሶ ሥርዓት ዓይነቱ ብዙ ነው። የለቅሶ ስርዓት የቀብር ለቅሶን፣ የመርዶ ለቅሶን፣ የደመር (የአጉበር) ለቅሶን፣ የአርባና የሙት ዓመት (የተዝካር) ለቅሶን የሚያካትት ነው። በመሆኑም የቀብር ሥርዓት ከለቅሶ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ እንጂ፣ የለቅሶ ስርዓቶችን በሙሉ ሊወክል የሚችል ሥርዓት አይደለም።

ሌላው ድክመት የሃይማኖት ድንበር ሳይለዩ ስለየማህበረሰቡ የለቅሶ ሥርዓት የሰነዘሩት አስተያየት ነው። ይህም አጥኚዎች ጥናት ባደረጉበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ በሙሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ይመስል "የ--- ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት" በማለት ተነስተው በጥናታቸው የጠቆሙት በየኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዩ ማህበረሰብ ዘንድ የሚደረገውን የለቅሶ ሥርዓት ብቻ ነው።

ይህ አገላለጽ ከወርቁ ማንደፍሮ በስተቀር (የጥናቱ ወሠን የእስልምና ሃይማኖት ተከታይን እንደማይመለከት ገልጿል) በድጋፌ፣ በንጉሴ፣ በአየለ፣ በሐረገወይን፣ በፋሲካ፣ በነጋ፣ በወርቃየሁ፣ በዘላለም፣ በጥላሁን፣ በፈለገ ህይወት፣ ጥናቶች የሚታይ ችግር ነው።

ሌላው ድክመት እያንዳንዱ ሥርዓት እንዴት እንደሚከወን እንጂ ድርጊቱ ለምን እንደሚደረግ አለመገለጹ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ ሁሉም አጥኚዎች የለቅሶ ሥርዓትን ሲገልጹ አንዳንድ ቁሶችና እንስሳት (የሟች አልባሳት፣ ጦር፣ ጋሻ፣ ጐራዴ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ወዘተ.) ለመለቀሻነት እንደሚወጡ ቢገልጹም፣ አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ አልተናገሩም፡፡

በመሆኑም ክዋኔ ሲጠና እያንዳንዱ ድርጊት ለምን እንደሚደረግና የቁሶች አገልግሎትም በአግባቡ ካልተገለጸ ጥናቱን ያልተሟላ ያደርገዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በቀረርቶና በፉከራ ላይ ጥናት ያካሄዱ አጥኚዎችም ግጥሞችን ሰብስበው፣ በአግባቡ መርምረው፣ በይዘት ከፋፍለው በማደራጀት፣ በጽሑፍ በማስፈር እንዲቀረሱ ማድረጋቸው አጥኚዎችን የሚያስመሠግናቸው ጉዳይ ቢሆንም፣ በወቅቱ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ በማን፣ ወዘተ. ይከወኑ እንደነበር አለመግለፃቸው ደግሞ የስብስቦችን ምልዓት የሚያጐድለው ይመስለኛል፡፡

ጥናቱ ከሌሎች ጥናቶች ጋር ያለው ዝምድናና ልዩነት

ከላይ የተዘረዘሩት ቀደምት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበት ነጥብ፣

1. ለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኩሩት ጥናቶች፣ ለቅሶን እንደ አንድ ማህበራዊ ጉዳይ አንስተው የየማህበረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ለማሳየት በመሞከራቸው፣

2. ምንም እንኳ የሚጠናው ማህበረሰብ ቋንቋ፣ ባህልና ክዋኔ የተለያየ ቢሆንም፣ በአንዳንዶቹ ጥናቶች የተገለጹ ስርዓቶች ከዚሁ ጥናት ጋር የተወሰነ ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆናቸው፣ ለምሳሌ፣ በጌጡ ታደሠ፣ በድጋፌ ፈይሳ፣ በወርቃየሁ አረጋ፣ በፈለገ ህይወት ዘገዬ፣ በአየለ መሎሬ፣ በፋሲካ በለጠ፣ በነጋ ተሠማ፣ ጥናቶች ውስጥ የተገለጹት የኑዛዜ ስርዓት፣ ለመለቀሻ የሚሆኑ አንዳንድ ቁሳቁሶችና የእንስሳት ስም፣ ወዘተ. መመሳሰል፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ነጥቦች ተመሳሳይነት ይኑራቸው እንጂ ልዩነታቸውም ሰፊ ነው፡፡ ይኸውም ይህ ጥናት ከለቅሶ ሥርዓቶች ውስጥ በጀግኖች የቀብር ሥርዓት ላይ ብቻ የሚያተኩር በመሆኑ “የለቅሶ ስርዓት” እየተባሉ ከቀረቡ ጥናቶች ይለያል፡፡ በለቅሶ ስርዓት ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ስንመረምር ያመዘኑት በለቅሶው ሥነ ሥርዓት ገለፃ ላይ ሳይሆን

የለቅሶ ስርዓቱን በመጠኑ ከገለጹ በኋላ በዋነኝነት በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት በሚገጠሙ የሙሾ፣ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች የቅርጽ፣ የባህርይና የዘይቤ አጠቃቀም ላይ ነው።

በተጨማሪም ከዚህ በላይ በተቃኙ አንዳንድ ጥናቶች ውስጥ በቀብር ስርዓት ወቅት የሚፎከርላቸው ጀግኖች ሙያቸው ተገልጿል። ለምሳሌ፣ በንጉሴ አክሊሉ፣ በወርቁ ማንደፍሮ፣ በወርቁ ደቻሳ፣ በበየነ ለገሰ፣ ጥናቶች ውስጥ በቀብር ስርዓት ወቅት የሚፎከርላቸው አዳኞችና ዘማቾች ብቻ መሆናቸው ተገልጿል። በጌጡ ታደሰ ጥናት ውስጥ ደግሞ ለዘማቾችና በአደባባይ ችሎት ተሟግተው ለረቱ ሰዎች እንደሚፎከር ተገልጿል። ይህ ለዘማቾች፣ ለአዳኞችና ለተሟጋቾች የመፎከር ጉዳይ የየማህበረሰቡ የቆየ ልማድ ቢሆንም፣ እኔ በማጠናው ማህበረሰብ ዘንድ ግን፣ እነዚህ የተባሉት እንዳሉ ሆኖ (ለተሟጋቾች የተባለውን አይጨምርም)፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለገበሬዎች (ለጠንካራ አራሾችና ለከብት አርቢዎች) ጭምር ይፎከራል። ይህ ደግሞ ጥናቱን ከሌሎች ጥናቶች የተለየ የሚያደርግ ነጥብ ነው።

በሚጠናው ማህበረሠብ ባህል፣ ቋንቋና መገኛም ፍጹም የተለየ ነው።

## 2.2 የንድፈ ሀሳብ (Theories) ቅኝት

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ከቀብር ሥነ ሥርዓት፣ ከቀረርቶ፣ ከፉከራ እና ከዋኔ፣ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ንድፈ ሀሳቦች ይቃኛሉ።

### 2.2.1 የቀብር ሥነ ሥርዓት

ቀብር፣ አንድ ሰው ነፍሱ ከስጋው ስትለይ ወዳጅ ዘመድ በተለያየ መንገድ መርዶ እየተነገረው፣ ተሰብስቦ እያለቀሰ (በአንዳንድ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ምክንያቶች ላያለቅስም ይችላል)፣ የአስከሬኑን ግብዓተ መሬት የሚፈፅምበት ሥነ ሥርዓት ነው።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ቀብር ለሚለው ቃል የሰጡት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ፣ "ቀበር፤ ቀበራ፤ አቀባበር፤ ግንዘት፤ አገናነዝ፤ የሬሳ ህግ፤ ሽቱ መቅባት፣ ማጠን፤ ማጤስ፤ መፍታት፣ ማልቀስ፤ ርግዶ ሙሾ፤ የመሰለው ኹሉ" (ኪዳነ ወልድ፤ 1948፣781) የሚል ነው።

የኪዳነ ወልድ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንደሚያመለክተው፣ ቀብር ሃይማኖታዊ እና ልማዳዊ ሥነ ሥርዓቶች የሚከናወኑበት ነው። ከሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓቶች መካከል የአገናነዝ

ስርዓት፣ አስከሬን መጥፎ ሽታ እንዳይፈጥር የሚደረገው ጥንቃቄ (በከፊል ልማዳዊ የሆኑት እንዳሉ ሆነው፣ ሽቱ መቀባት፣ ማጠን፣ ማጤስ)፣ በሟች ቤት፣ በጉዞ ወቅትና በግብዓተ መሬት አፈፃፀም ወቅት ለሟች የሚደረገው ፀሎት፣ አስከሬን ሲቀበር የሚይዘው አቅጣጫ (አቀባበር)፣ ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ ከልማዳዊ ሥነ ሥርዓቶች ውስጥም ለሟች የሚደረግለት ለቅሶ፣ ርግዶና ሙሾ ይጠቀሳሉ፡፡ የግለሰቡ ሞት ለወዳጅ ዘመድ የሚረዳበት መንገድ፣ የሚደረገው ቀረርቶና ፉከራ ሁሉ በዚህ ስር ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው፡፡

ክዋኔያቸውን ስናይ፣ የነዚህ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ሥነ ሥርዓቶች ክንውን (በእያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት ሰዎች የሚያከናውኑት ጉዳይ የተለያየ መሆን እንዳለ ሆኖ) ቡድናዊ ነው፡፡ ይህ ቡድናዊነትና አጋጣሚ ደግሞ ለቡድኑ አባላት የሚሠጠው ፋይዳ አለ፡፡ ይኸውም አጋጣሚው ለቡድኑ አባላት ስሜትን መተንፈሻ ቀዳዳ የሚፈጥር መሆኑ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ በኑሮ ውጣ ውረድ ያዘነ፣ የተከዘ፣ ሁሉ ያለቅሳል፤ ብሶቱን የሚገልጹ ሙሾዎችን ያወርዳል፤ እሱነቱንና ወዳጆቹን የሚያወድሱ፣ ቀረርቶዎችንና ፉከራዎችን ይደረድራል፡፡ በማልቀሱ፣ ሙሾዎችን በማውረዱ፣ ቀረርቶዎችና ፉከራዎችን በመደርደሩ፣ ጊዜያዊ ፋታ ያገኛል፡፡ ጊዜያዊ ፋታ የሚያገኘው ግጥሞች በመገጠማቸው አይደለም፤ በግጥሞች አማካይነት ሆዱ ባብቶ በማልቀሱ፤ ወይም ወዳጁንና ራሱን በማወደሱ እንጂ፡፡

ይህን መሠል ፋይዳ ከሚሰጡት የሥነ ሥርዓቱ ገጽታዎች መካከል ሙሾዎች ይጠቀሳሉ፡፡

ሙሾዎች በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ በማንኛውም ለቅሶ ሥነ ሥርዓት የሚደረደሩ ቢሆንም፣ በጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ግን ከሙሾዎች ይልቅ ሰፊውን ጊዜ የሚይዙት ቀረርቶዎችና ፉከራዎች ናቸው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት “ለጀግና አይለቀስም፤ የጀግና ሌላው ሠርጉ ቀብሩ ነው” የሚል አመለካከት በማህበረሰቡ ዘንድ በመኖሩ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን “የጀግና ሌላ ሠርግ” የሚያደምቁት ቀረርቶዎችና ፉከራዎች በመሆናቸው፣ ስለነዚህ ነጥቦች አንዳንድ ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዮችን ማንሳት የተሻለ ይሆናል፡፡

### 2.2.2 ቀረርቶ

ቀረርቶ አንድ ማህበረሰብ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ፍቅሩን፣ ጥላቻውን፣ ተስፋውንና ምኞቱን ከሚገልጽባቸው የስነቃል ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ፀሐፊዎች ቀረርቶ በጦርነት ጊዜ

አልያም በልዩ ልዩ ጨዋታዎች (በሰርግ፣ በክብረ በዓላት)፣ በመሸታ ቤቶች፣ ወታደር በጌታው ፊት፣ የከፋው ሰው በየጋራውና ተራራው የሚዘፍነው ዜማ ለበስ ግጥም እንደሆነ፣ በባሕርይው ጀግናን የሚያወድስ፣ ወኔ የሚቀሰቅስና ፊሪ የሚገስጽ እንደሆነ፣ይገልጻሉ(ደስታ ተክለ ወልድ፣1962፣1117፤ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፣1951፣299፤ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣1961፣39፤ ዓለማየሁ ሞገስ፣1973፣13፣)።

የመከወኛ ምክንያቱ ከላይ እንደተመለከተው የከፋው በየጋራው፣ በጦር ሜዳ፣ በጨዋታ፣ ወዘተ. ተብሎ የተገለፀው ብቻ አይደለም። በተለያዩ የለቅሶ ስርዓቶች፣ በተለይ ደግሞ በቀብር ስርዓት ላይ የሟችን ስም እየጠሩ፣ ዘሩን እየቆጠሩ፣ ጀብዱን እየዘረዘሩ፣ ስርዓቱን ያደምቁበታል።

## 2.2.3 ፉከራ

የቃሉን መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስንመለከት ደስታ ተክለ ወልድ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ። "ፈከረ (ግዕዝ)፣ ፎከረ (አማርኛ) ሞያውን ገብዱን ገለጠ፣ ቆጠረ፣ አስረዳ፣ ደነፋ፣ አካኪ ዘራፍ ገዳይ እዚህ ገዳይ አለ፤ ፍከራ፣ ፉከራ፣ ዘራፍ ማለት፤ ድንፋታ ገብዱ ቆጠራ፤ መፎከር፣ መደንፋት፣ ዝሆን፣ አንበሳ፣ ጠላት ገዳይ ማለት" (ደስታ ተክለ ወልድ፤ 1962፣975) ብለው ይገልጹታል። ከሣቴ ብርሃንም "ፉከራ የጀግኖችን ስራ እያወሡ መፎከር ነው" (ከሣቴ ብርሃን፤ 1951፣1380) ይላሉ።

ከላይ የተጠቀሱት ምንጮች እንደሚያስረዱት ፉከራና ቀረርቶ ሁል ጊዜ የማይነጣጠሉ፣ አብረው የሚከወኑና ወኔ ለመቀስቀስ፣ የጉበዝ ጀብድ ለመግለጥ፣ ተብሎ የሚገጠሙ ናቸው። ሁለቱም በባህርያቸው ወኔ ቀስቃሽ መሆናቸው፣ በጦርነት፣ በልዩ ልዩ ጨዋታዎች የሚገጠሙ መሆናቸው ያመሳስላቸው እንጂ በክዋኔ ወቅት የሚቀድመው ቀረርቶ ነው። የቀረርቶ የግጥም ስንኞችም ከፉከራ የግጥም ስንኞች ረዘም ያሉ (ብዙ ሀረጎች ያላቸው) ናቸው። የፉከራ ግጥም ስንኞች ደግሞ ከቀረርቶ አጠር ያሉ ሆነው፣ ብዙ ጊዜ እልህና ቁጣ ባመዘነበት ንግግርና ዜማ፣ ቅልጥፍጥፍ ባለ የሰውነት እንቅስቃሴ የሚገለጹ ናቸው።

ሌላም የሚያመሳስላቸው ነጥብ አለ። ይህም ቀረርቶም ሆነ ፉከራ የሚያተኩሩት በጀብድ ላይ መሆኑ ነው። በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ ጀብደኛ (ጀግና) የሚያስብሉ ሙያዎች ደግሞ አርበኝነት እና አዳኝነት ናቸው። ይህ ጥናት በሚያተኩርበት ማህበረሰብ ግን ከቅርብ

ጊዜ ወዲህ ገበሬነት (አራሽነትና ከብት አርቢነት) ጀብደኛ የሚያሰኝ ሙያ እየሆነ መጥቷል። ጠንካራ ገበሬ እንደጀብደኛ ተቆጥሮ፣ ሲሞት መፎከር የማህበረሰቡ የቆየ ልማድ አይደለም፣ ከጊዜ በኋላ የመጣ እንጂ።

በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያስከብሩ ተግባራት ብዙ ማምረት፣ ብዙ ማርባት፣ ለሀገር፣ ለወገን፣ ለሃይማኖት፣ ወዘተ. በመቆርቆር በሚደረግ ዘመቻ መዝመት፣ አንበሳ፣ ነብር፣ ዝሆን፣ አጋዘን፣ ወዘተ. አድኖ መግደል ናቸው። እነዚህን ተግባራት ሲፈፅም ይወደሳል። ለምሳሌ፣ እንዲህ እየተባለ፣

የእገሌ እናቱ ለምን አትወዛ
ሙሉ ዘጠኝ ወር እሳት አርግዛ
ጀግና ነው ብላ የወለደችው
እትብቱን በሳት ያቃጠለችው
ጥጃ ጠብቋል ስትል እናቱ
መብረቅ ሆነበት ለሠራዊቱ
ገዳይ ----- ከቤቱ በታች
እናቱ እያየች ሚስቱ እያቦካች
መጫኛ ሚያህል አንጀት አስጐታች

በባህሉ መሰረት አንድ ግለሰብ የሚፈለግበትን ተግባር አሟልቶ ያልተገኘ እንደሆነ የተለያየ ተግሳፅ በሚከተለው አኳኋን ይደርስበታል።

ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ
ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደ እናቱ

ከዚህ በላይ በተገለጹት መንገዶች የሚያስከብሩና የሚያስነቅፉ ማህበራዊ እሴቶች እየተነገሩት፣ መጥፎ ተግባራትን ከመስራት እንዲታቀብ፣ የሚያስከብሩና መልካም ተግባራትን ደግሞ ለመተግበር እንዲጣጣር ይደረጋል።

መልካም የሚባሉ ተግባራትን በተደጋጋሚ የፈጸመ ሰው(ቀደም ብሎ ከተገለጹት በተጨማሪ የተቸገረን የረዳ ሁሉ፣) በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ጀግና ነው። እንዲህ ዓይነቱ ጀግና ሲሞት ደግሞ ቀብሩ ሌላው የማህበረሰቡ አባል ሲሞት ከሚደረገው ልዩ ነው። ብዙ

አይለቀስለትም፤ በህይወት ዘመኑ ያደረጋቸው "መልካም ተግባራት" እየተወሱ (ብዙ ሰው የገደለ መሆኑ ያመዝናል)፣ በፈጸመው ድርጊት እየተወደሠና እየተሞገሠ፣ ጠላቱና ሰነፍ፣ ሌባ፣ ውሸታም የሆነ የማህበረሰቡ አባል ሁሉ እየረከሠ ይፎከርለታል።

ሩት ፊነጋን (Ruth Finnegan) የተባሉ ምሁር የውደሳ ግጥሞች (praise poems) በአፍሪካ፣ ልዩ ልዩ ሀገሮች (በናይጀሪያ የዮሩባ (Yoruba)፣ በማላዊ የንጎኒ (Ngoni)፣ በደቡብ አፍሪካ የዙሉ (Zulu)፣ በሩዋንዳ የካጋሜ (Kagame)፣ በኬንያ የካምባ (Kamba)፣ በሶማሊያ የጊርአር (Geeraar)፣ በኢትዮጵያ ወደ ዘመቻ ሲኬድ፣ በጦር ሜዳ ላይና ከጦርነት ድል በኋላ የሚገጠሙ) መሆናቸውን ያስረዳሉ፤ "*It is common for songs celebrating military success to become highly developed after the return home. …When they approach a village, they strike up their songs of victory. The hero is praised…*" *(Finnegan, 1970: 210).*

ዣን ቫንሲና (Jan Vansina) የተባሉ ፀሃፊም የውደሳ ግጥሞችን ያስረዱበት መንገድ እነ ከሣቴ ብርሃንና እነ ማኀተመ ሥላሴ "ቀረርቶ ወታደር በጌታው ፊት የሚያቀርበው የውደሳ ዘፈን ነው" በማለት ከቶገለጹት ሀሳብ ጋር የሚዛመድ ነው፤ "*Praise poems for kings among the Zulu (South Africa) were delivered infront of the king by the poet during a public gathering in different attitudes*" *(Jan Vansina, 1985: 35).*

እነዚህ ግጥሞች በባህርያቸው ወኔ ቀስቃሽና ጀብዱ ገላጭ ስለመሆናቸውም ፊነጋን የሚከተለውን ይላሉ፤

> *Such war songs in fact are sometimes more an experience and reinforcement of the militant strength of a group than a direct incitement to the fight or a part to the battle itself. …They involve glorification the expression of high morale… (Finnegan, 1970: 208).*

እነዚህ ግጥሞች የሚገጠሙት በጦርነት ጊዜና ለጦር አርበኞች ብቻ አይደለም። ለታወቁ አዳኞችም ይገጠማሉ። የሚገጠሙትም በአደን ጊዜ፣ ግዳይ ሲጥሉ፣ ገድለው ሲመለሱና በአዳኞች የቀብር ስርዓት እንደሆነ ፊነጋን ያስረዳሉ።

> *Poetry about both hunting and war seems to involve the same ideas of romance and glory. Sometimes the same genre of poetry is even used to*

*deal with both, ...hunting songs are also often sung at the funerals of skilled hunters (Finnegan, 1970: 207, 224).*

አዳኙ ከአደን ሲመለስ ራሱ ስለጀግንነቱ፣ ስለግዳዩ ዓይነትና መጠን በኩራት እያነሳ ወዳጅ ዘመዶቹና ጐረቤቶቹ በተሠበሠቡበት ቦታ ሊሸልል፣ ሊያቅራራ እንደሚችልም፣ *"The hunter himself also sings boastfully of his exploits and retells his heroism in poetry designed for an audience rather than for the exigencies of the hunt itself" (Finnegan, 1970:223)* በማለት እኒሁ ምሁር ያስረዳሉ።

አዳኙም ይሁን ዘማቹ ድል ቀንቶት አሊያም ግዳይ ጥሎ ሲመለስ የሚደሠተው ራሱ ጀግናው ብቻ ሳይሆን ወዳጅ ዘመዱ ሁሉ ናቸው። ለፈጸመው የጀግንነት ተግባር የተለያየ ክብርም ይሠጠዋል። አዳኙ ዘወትር ከአደን ወደ ቤቱ ሲመለስ ለምግብነት የሚውሉ እንስሳትን ሥጋ ወይም ከብቱን፣ ካልበረታና ካልጠነከረም ራሱን ሊያጠፉ የሚጣጣሩ፣ ወይም ማሳውን የሚያወድሙ አራዊትን ቆዳ፣ ጥርስ፣ ቀንድ፣ ጭራ፣ ወዘተ. አንጠልጥሎ ሲመለስ፣ ራሱ ወይም ሌላው ማህበረሰብ እንዲህ እያለ በግጥም ሊያወድሰው ይችላል።

> የዛች አሽከር ባል ያንገተ ቅጥል
>
> ሳይገድል አይመጣም ሳያንጠለጥል
>
> የዛች አሽከር ባል የቀመጢና
>
> ሀምሳውን ገድሎ መጣ በጤና

ፊነጋን አድኖ መግደል በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የተለመደና የሚያስከብር ተግባር መሆኑን ለማሳየት ኢትዮጵያን እንደምሳሌ አንስተዋል።

> *In general the most commonly mentioned occasion is when the hunter has returned to the village: he is often welcomed and congratulated. The Ethiopian hunter returning from killing an elephant is received by a double chorus.*
>
> *1st chorus. He has slain, he has destroyed him.*
>
> *2nd chorus. Whither went he when he slew him? (Finnegan, 1970:222).*

ከላይ ፊነጋን እንደገለጹት ሁሉ በኢትዮጵያ አደንና አድኖ መግደል በተለይም እንደ ጎሽ፣ ቀጭኔ፣ ዝሆን፣ አንበሳ፣ የዱ፣ ወዘተ. ያሉትን መግደል የተለያየ ክብር እንደሚያስጥ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ዝክረ ነገር በሚለው መጽሐፋቸው ገልጸውት እናገኛለን።

> የአውሬ አደን በኢትዮጵያ የጨዋ ልጆች ዋና ሙያ ሆኖ ክብርም ደረጃም ያስገኝ እንደነበረ እኔም ከደረስኩ ተመልክቼዋለሁ። ...ይህን ያህል የሚደክሙትና የሚጣጣሩት እንደገደሉት አውሬ ዓይነትና ብዛት በቤተ መንግሥቱና በሕዝቡ ዘንድ ክብር ይሰጣቸው ስለነበር ነው (ማኅተመ ሥላሴ፣ 1962፣250)

በአሁኑ ጊዜ የዱር እንስሳትን ማደን በህግ የተከለከለ ይሁን እንጂ ከመንግስታዊ አካላት ተሰውሮ በድብቅ የሚገድል ሰው በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ ዝናውና ክብሩ ከፍ ያለ ነው። በጦርነትም ይሁን በአደን ጀግና መሆን የሚያስከብር ተግባር የሚሆንበት ምክንያት ከፍተኛ ትግልንና መስዋዕትነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። የሚከተሉት ምንጮች የሚያስረዱትም ይህንኑ ነው።

> እነዚህ ጦርነት አደን የመሳሰሉት ሁኔታዎች ብዙውን ጊዜ የሚጠይቁት ወኔ በዕለት ኑሮዋችን ከሚጠበቀው በላይ ነው። በሁለቱም አደጋ አለ፤ ጀግንነት አለ። ስለዚህ ግጥሞቹና ዘፈኖቹ ዘወትር ከሚሰማው ለየት ይላሉ፤ ወኔን ለማነሳሳትና ለማስቀጣት ስለሚገጠሙ። በአገራችን የጀግነነት፣ የአደን፣ ...ግጥሞችና ዘፈኖች ተወዳጅና ታዋቂ ናቸው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ፣ አጭር የኪነቃል አጠናን መመሪያ መነሻ ሀሳብ፣ 1973፣ 28)።

በሌላ በኩል ይህንኑ ሀሳብ ፊነጋን፣

> *Both involve action which is out of the run of ordinary everyday pursuits; in both there is danger, triumph, or heroism and boasting, challenge, and specialized ability... are frequent elements in both (Finnegan, 1970:208).*

በማለት በአደንና በጦርነት (ሁለቱም ጋ) አደጋ መኖሩንና ጀግና መሆንን የሚጠይቁ እንደሆኑ አመልክተዋል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ቀረርቶና ፉከራ በክዋኔ ጊዜ የማይነጣጠሉ፣ በባህርያቸው በፈጣን ንግግር፣ ቅልጥፍና በተሞላበት የሰውነት እንቅስቃሴ የሚገለጡ፣ በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ መስዋዕትነት በሚጠይቁ ተግባራት ለተሳተፉ (በተለይ በጦርነትና በአደን ለታወቁ) ሰዎች የሚገጠሙ፣ የሚዘፈኑና የሚደረደሩ ናቸው።

ለእነዚህ ጀግኖች ከሚፎከርባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የቀብር ሥነ ሥርዓት ነው። በመሆኑም ጥናቱ በሚያተኩርበት አካባቢ ጀግኖች ሲሞቱ የሚደረገው የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ ምን እንደሚመስል በጥናቱ አራተኛ ምዕራፍ ይቀርባል።

### 2.2.4 ክዋኔ (Performance)

አብዛኛዎቹ የስነቃል ዘርፎች እንደአይነታቸውና እንደባህርያቸው የሚለያይ ክዋኔ (performance)፣ የሚከወኑበት የተወሰነ ምክንያት (occasion)፣ ከዋኝ (performer)፣ ታዳሚ (audience)፣ የሚደረሱበት መንገድ (composition)፣ ያላቸው መሆናቸውን የመስኩ ምሁራን ይጠቁማሉ (ፊነጋን፤ 1970፣ 2፣ 1977፣ 28፣ ቦውማን፤ 1977፣ 13፣ ቫንሲና፤ 1985፣ 34፣ ማርታና ማርቲን፤ 2005፣ 128፣ ፈቃደ፤ 1984፣ 3)።

ክዋኔ ለስነቃል ዘርፎች (በቡድንም ይከወኑ በተናጠል) ህልውና መሠረታዊ ከሆኑ ነጥቦች ውስጥ የመጀመሪያው ነው። ይህንን አስመልክተው የመስኩ ምሁራን የሚከተለውን ይላሉ፤

> *...an oral poem is an essentially ephemeral work of art, and has no existence or continuity apart from its performance. ... a piece of oral literature, to reach its full actualization, must be performed. The text alone cannot constitute the oral poem (Finnegan, 1977: 28).*

ፈቃደ ደግሞ በበኩላቸው፣

> አንዲት አልቃሽ በአንድ ለቅሶ የምታደርገውን ግጥም ሰብስቦ በጽሁፍ ማስፈርና ላንባቢ ማስተላለፍ ይቻላል ዛሬ። ነገር ግን ይህ ስብስብ የሙሾውን አከናወን አይጨምርም። አልቃሿ ከግጥሙ ውጭ የሆነውን የክዋኔዋ ማጉልበቻ አድርጋ የምትገለገልባቸው ጠቅላላ ድባቡንም አይጨምርም። የሚያነበውን ሰው ስሜት ምንም ያህል አይነካም፤...አካሉ ከሆነው ማህበራዊ እውነታውና ክዋኔው ተለይቷልና። ... የአፋዊ ኪነተቃል ህልውናው ክዋኔ ነው። ከደራሲውና ከተደራሲያኑ አንደበት በመውረድ፣ በመነገር፣ በመዘመር። (ፈቃደ፤ 1984፣1-3)።

ፊነጋንና ፈቃደ እንዳሉት፣ ግጥሞችን ሰብስቦ መጻፍ የሚቻል ቢሆንም፣ ለአብዛኞቹ የስነቃል ዘርፎች ህልውና መጠበቅ ዋናውና አስፈላጊው ጉዳይ የክዋኔ መኖር ነው። አብዛኛው የስነቃል ዘርፍ ካልተከወነ (ካልተነገረ፣ ካልተዘመረ፣ ካልተጨፈረና ለእይታም ካልበቃ) ለትውልድ የሚተላለፍበት ሌላ መንገድ አይኖረውም። ለስሜት ግልፅ፣ የሚታይና የሚጨበጥ የሚሆነው ሲከወን ብቻ ነው። ሲከወን ነው መኖሩ የሚታወቀው፣ ስሜትን የሚኮረኩረው፣ የሚያሳዝነው፣ የሚያስደስተው፣ የሚያስቀውና የሚያስለቅሰው።

ፈቃደም ከክዋኔያቸው ውጪ ግጥሞች ብቻቸውን ቢቀርቡ "የአፋዊ ኪነተቃልን፣ ኪናዊ እሴቱን አንስተው፣ ቆዳውን ገፈው፣ ስጋውን ቦጭቀው፣ ደሙን አፍስሰው፣ አፅሙን ብቻ

ያቀረቡ አይነት ነው" (ፈቃደ፣ 1970፣8) በማለት ክዋኔና ግጥሞች ተነጣጥለው መታየት እንደሌለባቸው፣ ግጥሞችና ክዋኔ ከተነጣጠሉ ግን ስነቃል ህያውነት እንደማይኖረው ያስረዳሉ።

የሥነቃል እስትንፋስ ክዋኔ እንደሆነ ሁሉ ክዋኔ የሚቆምባቸው የራሱ መሠረቶችም አሉት። እነዚህም የመከወኛ ምክንያት (occasion)፣ ታዳሚ (audience)፣ ከዋኝ (performer)፣ የክዋኔ ጠቋሚዎች (markers)፣ የክዋኔ ቅንብብ (frames)፣ የክዋኔ ጠቅላላ አውድ (physical and social context)፣ ወዘተ. ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች አንዱ ከሌላው ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸውና በክዋኔ ወቅት የማይነጣጠሉ ናቸው፤ በተለይ በቡድን በሚከወኑት።

> *Performance is an expressive activity that requires participation, heightens our enjoyment of experience, and invites response. In order for a performance to "happen", a recognizable setting must exist (we have to know a performance is taking place) and participants of the setting and relationships between participants can be quite complex and fluid (Martha and Martine, 2005: 128-129).*

*በውማንም፣*

> *The term 'performance' has been used to convey a dual sense of artistic action – the doing of folklore – an artistic event – the performance situation, involving performer, art form, audience, and setting (Bauman, 1977:4).*

በማለት ከዋኝ፣ ታዳሚ፣አውድ፣ወዘተ· የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው እንደሆኑ አመልክተዋል።

### 2.2.4.1 የመከወኛ ምክንያት (Occasion)

አብዛኛው የሥነቃል ዘርፍ በዝርውም ይቅረብ ወይም በግጥም፣ የሚዜምበት፣ የሚነገርበትና የሚከወንበት የተወሰነ የመከወኛ ምክንያት (occasion) ይጠይቃል። ለክወናውና ለአፈጣጠሩ የተወሰነ ወቅት ይኖረዋል እንጂ በዘፈቀደ የትም አይዜምም፤ በማንኛውም ጊዜና ቦታ አይነገርም፤ አይከወንምም። ዣን ቫንሲና ሀሳቡን እንደሚከተለው ይገልጹታል፤ *"Performances are not produced at random times. The occasions for performances are limited and can be observed in the field" (Jan Vansina, 1985:39).*

ለቅሶ ሳይኖር ሙሾ አይወርድም። ሰርግ ሳይኖር የሰርግ ዘፈን አይዘፈንም፤ ስራ ሳይኖር የስራ መዝሙር አይዘመርም፤ ቡሄ ሳይኖር ቡሄ አይጨፈርም። ስርዓቱ በሌለበት ቢለቀስ፣ ቢዘፈን፣ ቢጨፈር ክዋኔው ለዛና ድምቀት ያጣል። በባህርይው የሚያስለቅሰው አያስለቅስም፣ የሚያስቀውም አያስቅም። ምክንያቱም የሚያስለቅሰውም ይሁን የሚያስቀው አጠቃላይ ድባቡ ሲኖር ነው። በመሆኑም ለመዝፈን፣ ለመጨፈር፣ ሙሾ ለማውረድ፣ ለመፎከርም ይሁን ለማቅራራት የሚያነሳሳ ምክንያት መኖር ይኖርበታል።

ሰው ሲሞት የሚደረገውም የቀብር ሥነ ሥርዓት የተለያዩ ስነቃሎች እንዲከወኑ የሚያደርግ ምክንያት ነው። ምንም እንኳ እንደየማህበረሰቡ ባህል፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ ወግና ልማድ የሚለያይ ቢሆንም ሙሾ እንዲወርድ፣ ፉክራና ቀረርቶ እንዲደረደር፣ ለሟች ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊና እምነታዊ ስርዓቶች እንዲፈፀሙለት የሚያደርግ አነሳሽ ምክንያት ወይም አጋጣሚ ነው።

### 2.2.4.2 **ከዋኝ** (Performer)

ከዋኝ፣ ስነቃል ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ ከሚያስችሉት መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው ነው። ከዋኝ ሲባል በአንድ በተወሰነ ምክንያት፣ አንድን የስነቃል ዘርፍ በመሪነት የሚያቀርብ፣ የሚከውን ግለሰብ ወይም የተደራጀ ቡድን ማለት ነው። ፊነጋን ከዋኝን የገለፁት፤ *"Oral literature by definition is dependent on a performer who formulates it in words on specific occasion. There is no other way in which it can be realized as a literary product" (Finnegan, 1970:2)* በማለት ነው።

ፊነጋን እንዳሉት፣ ስነቃል ከዋኝ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም አብዛኛው የስነቃል ዘርፍ ራሱን የቻለ፣ በዘርፉ የተካነ፣ ባለው የመከወን ልምድና እውቀት ተመስርቶ ላቅ ያለ ማህበራዊ ደረጃ የተሰጠው፣ አንዳንዴም ለዚሁ ሙያው የሚከፈለው ባለሙያ (ከዋኝ) አለው። የተረት ተራች፣ የለቅሶ አልቃሽ ወይም ሙሾ አውራጅ፣ የዘፈን ዘፋኝ፣ የቀረርቶና የፉከራ አቅራሪና ፎካሪ፣ ወዘተ. እየተባለ የሚጠራ ከዋኝ አለው።

እነዚህ ከዋኞች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ የተለያየ ማህበራዊ ደረጃ ያላቸው ናቸው። ሆን ተብሎ ሙያዊ ስልጠና እንዲወስዱና እንዲለምዱ የሚደረጉ፣ በክወና ሙያ ብቻ የሚተዳደሩ (full time specialists)፣ ከሙያቸው በተጓዳኝ የሚሰሩ (non specialists)

ተብለው የሚመደቡ፣ በክወና ስልቶቻቸውም አንዳንዶቹ ክወናውን አስቂኝና አዝናኝ በሆነ ትእይንት የሚሞሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በክወና ወቅት ምናባዊ ዓለም በመፍጠር ታዳሚው በሙሉ በእውኑ ዓለም ከሚያጋጥመው ተደጋጋሚና አሰልቺ ህይወት ርቆ (አምልጦ) ለጊዜው በፈጠሩለት አስደሳች የሆነ ምናባዊ ዓለም እንዲኖር የሚያደርጉ፣ ሌሎች ደግሞ በችሎታቸው እንደ ልዕለ ሰብ አሊያም የሌላ መንፈስ ማደሪያ ተደርገው የሚቆጠሩ ናቸው (ለዝርዝር መረጃ ፊነጋን፣ 1977፣170-213 እና ቫንሲና፣ 1985፣34-37 ተመልከት)።

ጥናቱ በሚያተኩርበት ማህበረሰብም የጀግኖችን የቀብር ሥነ ሥርዓት በፉከራና በቀረርቶ የሚያሞቁና የሚያደምቁ ከዋኞች አሉ። እነዚህ ከዋኞች በአካባቢው አጠራር "ፈካሪዎች" በመባል የሚታወቁ ናቸው። ይህ ስያሜ የአቅራሪዎችም መጠሪያ ነው።

#### 2.2.4.3 ታዳሚ (Audience)

> *In most performances of oral literature, however, an audience is involved. Sometimes the audience is really part of the performance itself, as in songs for choral singing, or is so at times, as when a lead singer performs partly as soloist, partly as leader in a joint singing with the audience (Finnegan, 1977:216).*

እንደ ፊነጋን አገላለፅ ታዳሚ ማለት በክዋኔ ወቅት ክዋኔን ለመመልከት፣ ለማዳመጥ፣ የከዋኙን ሞራል በተለያየ ዘዴ እያበረታታ፣ በክዋኔውም በከፊል እየተሳተፈ ስርዓቱን የሚያደምቀውን ቡድን የሚመለከት ነው። ከዋኙ ክዋኔውን የሚያቀርብለት አካል ተብሎም ሊገለፅ ይችላል።

አብዛኞቹ የስነቃል ክፍሎች ታዳሚ የሚሹ ናቸው። እንደየባህርያቸውና አይነታቸው የታዳሚዎቹ አይነትና ሚናም የተለያየ ነው። አንዳንዶቹ የከዋኙንና የታዳሚዎችን ጥብቅ መስተጋብር የሚጠይቁ ናቸው። የከዋኙን የግጥም አወራረድ፣ የድምፅ አወጣጥ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ በመከተል ታዳሚዎች እንደከዋኙ እንዲያደርጉ የሚጠይቁ፣ አሊያም በጭብጨባ፣ በእልልታ፣ በዋይዋይታ፣ በተለያዩ የመከወኛ ቁሶች ድምፅ ታዳሚዎች እንዲያጅቡ የሚያደርጉ ናቸው። ይህ አገላለፅ በተናጠል የሚከወኑትን፣ ለምሳሌ በስራ ላይ ስራን ለማቀላጠፍ፣ በመንገድ ላይ ራስን ለማዝናናት የሚደረጉትን ዘፈኖችና እንጉርጉሮዎች አይጨምርም ምክንያቱም ያለ ታዳሚ ይከወናሉና ነው።

የከዋኙና የታዳሚ ጥብቅ መስተጋብር የሚጠይቁት በአብዛኛው በቡድን የሚከወኑት ናቸው። ለምሳሌ፣ የሚከወነው ጉዳይ ዘፈን አሊያም ለቅሶ እንደሆነ የታዳሚዎች ሚና ብዙ ጊዜ ዝም ብሎ ማዳመጥ ወይም መመልከት ብቻ አይሆንም፤ ከከዋኙ ጋር ሚና በመለዋወጥ፣ በተለያየ መንገድ በክዋኔው ተካፋይ ይሆናሉ እንጂ። እነዚህ ታዳሚዎች የሙዚቃ መሳሪያዎችን እና የከዋኙን የድምፅ አወራረድ፣ ዜማና እንቅስቃሴ ተከትሎ መላ ሰውነታቸውን በማወዛወዝ፣ ቁጭ ብድግ በማለት፣ በመዝለል፣ በማጨብጨብ፣ በእግር መሬትን በመምታት፣ እልል፣ ዋይ ዋይ በማለት ይሳተፋሉ።

በተጠኚው ማህበረሰብም በቀብር ጊዜ የታዳሚዎች ሚና የተለያየ ነው። ፎካሪው የሚደረድረውን ዜማ፣ የካህናትን እንቅስቃሴ፣ የመከወኛ ቁሶችን ድምፅ እየተከተሉ ሚናቸው የተለያየ ይሆናል። የተወሰኑት ትእይንቱን ይከውናሉ፤ የተወሰኑት ከዋኞቹን ያበረታታሉ፤ የተወሰኑት ደግሞ ትእይንቱን ቆመው ያያሉ።

### 2.2.4.4 አውድ (Context)

አውድ አንድ የስነቃል ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት የሚኖረውን (ያለውን) አጠቃላይ የሆነ የክዋኔ ድባብ የሚመለከት የክዋኔ አካል ነው። ይኸውም ክዋኔ የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ (መቼት)፣ የክዋኔውን ድርጊቶች (events)፣ የታዳሚና የከዋኝ መስተጋብር ወዘተ. የሚይዝ ነው። ማርታና ማርቲን አውድን እንደሚከተለው ይገልፁታል፤

> *The physical settings and social situations in which members of folk groups share folklore, as well as the relationships among audience members and performers, make up the context of the performance.*
>
> *...context refers to anything and everything that surrounds a text and performance (Martha and Martine, 2005:37).*

ከላይ ያለው ምንጭ እንደሚያስረዳው አውድ ተጨባጭ አውድ (physical context) እና ማህበራዊ አውድ (social context) ተብሎ የሚከፈል ነው።

#### 2.2.4.4.1 ተጨባጭ አውድ (Physical context)

ይህ አውድ ክዋኔው የሚካሄድበትን ቦታ፣ ጊዜና አጠቃላይ ድባብ፣ በወቅቱ የነበረውን (ያለውን) ከዋኝ፣ ታዳሚ በመመልከት ብቻ ተጨባጭ ሁኔታውን ለመግለፅ የሚሞከርበት

የአውድ አይነት ነው። ይህም አንድን ክዋኔ በቴፕ በመቅዳትና በመመልከት ብቻ መረጃ ለመሰብሰብ ሲታሰብ የክዋኔውንና የአውዱን ግንኙነት ለመመርመር፣ በቴፕ ሊቀረፁ የማይችሉ አንዳንድ አካላዊ ሁነቶችን ለመግለፅ ስለሚረዳ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይህ ማለት ግን ሁሉንም አካላዊ እንቅስቃሴዎች በፅሁፍ መግለፅ ይቻላል ማለት አይደለም፤ ለመግለፅ የሚያስቸግሩ አሉና።

> *The reactions of performers and audience members convey details related to performance, beyond the description of a statement or movement. For example, laugher is a physical activity, so we would report someone laughed. But laugher might also signify a particular psychological state in the person who laughed; he or she may be amused, which we typically interpret as a pleasant state, or may be expressing discomfort through nervous laughter. Boos or hisses suggest at a different psychological response, as does squirming in a chair, or storming out of a room. Elements such as these may suggest the types of relationships that exist between audience members and performers (Martha and Martine, 2005:139).*

#### 2.2.4.4.2 ማህበራዊ አውድ (Social Context)

ይህ የአውድ አይነት በክዋኔ ወቅት የሚታየውን ጠቅላላ የክዋኔ መዋቅር ማለትም የከዋኞችን ማንነትና ማህበራዊ ደረጃቸውን፣ የታዳሚዎችን ሁኔታ (በእድሜ፣ በፆታ፣ በጎሳ፣ በመደብ፣ በሃይማኖት፣ በሙያ፣ በባህልና በሌሎች ጉዳዮች) ምክንያት የሚፈጠረውን ጠቅላላ አውድ የሚመለከት እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ። ለምሳሌ፣ ማርታና ማርቲን፤

> *Broad elements of performance context include those things that relate to the group, community, and culture with in which the communicative expression takes place.*
>
> *...Ethnic background, religious affiliations, occupation, regional connections, culture – all these are social aspects of performances, audiences and settings that influence the events taking place during a performance. These kinds of social components influence how those present interact, and may reflect assumed roles or expectations within the group or community (Martha and Martine, 2005:139).*

(ለተጨማሪ ማብራሪያ ፊነጋን፤ 1977፣ 214፤ ቦውማን፤ 1977፣38፤ ቫንሲና፤ 1985፣ 34 ተመልከት)።

ስለዚህ በቀብር ስርዓት ወቅት የሚታደመው ህዝብ በእድሜ፣ በፆታ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በሃይማኖት፣ በሙያና በሌሎችም ሁኔታዎች የተለያየ በመሆኑ እነዚህን ጉዳዮች በጥልቀት መመርመር ተገቢ ነው።

### 2.2.4.5 ድርሰት (Composition)

ድርሰት በዜማ በሚከወኑ ግጥሞች ላይ የሚታይ ጉዳይ ነው። በይበልጥ ደግሞ በክዋኔ ወቅት ግጥሞች የሚገጠሙበትን መንገድ ይመለከታል። ከዋኙ በሚከውንበት ወቅት በየመሐሉ የነባሩን ዜማ አወራረድ፣ አሰነኛኘት ስልት ተከትሎ የራሱን ቃላት፣ ሐረጋት እና አዳዲስ ስንኞች ሊፈጥር ይችላል። ይህም የሚሆነው ከዋኙ የታዳሚዎችን ፍላጐት በመመስረት ስሜታቸውን ለማናርና ክዋኔውን ለማራዘም ሲል፣ ታዳሚው አመለካከቱ፣ አኗኗሩና ፍልስፍናው እንደየወቅቱ ሲለወጥና ሲሻሻል ይህን ወቅታዊ ለውጥ የሚገልፁ አዳዲስ ገጠመኞች ለመግለፅ ሲል የነበረውን ግጥም ስለሚጨምርበት (ስለሚለውጠው) ነው። ይህ የመለወጥ ባህርይ በአብዛኛው በቃል ግጥሞች ላይ እንደሚንፀባረቅና በክዋኔ ወቅት ቃል ግጥሞች በተለያየ መንገድ ሊደረሱ እንደሚችሉ ፊነጋን ያስረዳሉ። ከአደራረስ መንገዶች መካከልም ቃል ጥናት (memorization)፣ እዚያው በዚያው (Improvisation) እና ተመስጦ (Inspiration) ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ አመልክተዋል።

የቃል ጥናት (memorization) ስልት ከዋኙ ነባሩን ቃል ግጥም ደጋግሞ በቃል በማጥናት በክዋኔ ወቅት ይህንኑ ግጥም እንዳለ የሚገጥምበት (የሚደረድርበት) መንገድ ነው። እዚያው በዚያው (improvisation) ደግሞ ከዋኙ የክዋኔውን ጠቅላላ ድባብና ጠባይ ተመስርቶ፣ ነባሩን የዜማ አወራረድ እና ስልት ተከትሎ የራሱን አዳዲስ ስንኞችና ሃሳቦች እየጨመረ (ከነባሩ መጠነኛ ማሻሻያዎች እያደረገ) የሚያቀርብበት የድርሰት አይነት ነው። ተመስጦ (inspiration) ከዋኙ በአንዳንድ ቀስቃሽ ሃይላት ተነሳስቶ ስሜቱ ሲንር የሚገጥማቸውን ግጥሞች የሚመለከት ነው (ፊነጋን፤ 1977፣52-86 ዝርዝሩን ተመልከት)።

በቀብር ጊዜ የሚደረደሩት የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች ደግሞ ከዚህ የድርሰት ባህርይ ጋር ስለሚዛመዱ፣ የአደራረስ መንገዳቸውም ከላይ ከተጠቀሱት ስልቶች የዘለለ አይሆንም።

### 2.2.4.6 የክዋኔ ጠቋሚዎች (Performance markers and Frames)

እያንዳንዱ የስነቃል ዘርፍ ስለክዋኔው ግልጽ መቼት፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቅ መዋቅርና የተለመደ ስርዓት (frame) ያለው ነው፡፡ የክዋኔውን ሂደት (አጀማመሩን፣ አካሄዱንና አጨራረሱን) የሚያመለክቱ ጠቋሚዎችም (markers) አሉት፡፡ የራሱ ከሆነው፣ ተለይቶ ከሚታወቅበት የክዋኔ ስርዓት፣ እንዲከወንበት ባህሉ ከፈቀደለት ቅንብብ (frame) ሊወጣም አይችልም፡፡ የሙሾ ግጥሞች የሚወርዱት፣ ቀረርቶና ፉከራ የሚደረገው፣ ዘፈን የሚዘፈነው የራሱን ነባር ስልትና ስርዓት ተከትሎ ነው፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ በሙሾ ግጥም እስክስታ አይወረድም፤ በለቅሶ ጊዜም አይዘፈንም፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ለቅሶው፣ ቀረርቶውና ዘፈኑ የሚከወኑበት፣ የራሳቸው የሆነ ማህበረ ባህላዊ ስርዓትና ቅንብብ ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡ ይህንኑ ሀሳብ ማርታና ማርቲን ሲገልጹ፤

> *Performances have clear settings and recognizable structures that indicate to participants that the performance is taking place. Many rituals, for example, begin at a predetermined time and place, and an announcement or other signal opens and closes the performance (Martha and Martine, 2005:128).*

በማለት ነው፡፡ በጥቅሱ እንደተገለፀው የክዋኔ ጠቋሚዎች (markers) ሚናቸው አንድ የፎክሎር ዘርፍ በመከወን ላይ እንደሆነ ለታዳሚዎችና ለፎክሎረኛው ማመልከት ወይም መጠቆም ብቻ አይደለም፡፡ ከዋኙና ታዳሚዎች ሚና እንዲለዋወጡ፣ መጠነኛ እረፍት እንዲያደርጉ፣ ስለክዋኔው አስተያየት እንዲለዋወጡና ፎክሎረኛውም ከክዋኔው ተነስቶ ተገቢ ትንታኔ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

> *We often call these signs markers, and they are an important part of describing and analyzing performance. They are the signals that tell the participants to pay attention, something important is happening, something that is set apart from (segregated from) the ordinary. ...clearly stated verbal markers generally signal for performers and listeners that it is time to pay attention, guide them through the performance and let them know when it is time to relax, or perhaps comment on the performance they have just seen (Martha and Martine, 2005:141-142).*

እነዚህ ጠቋሚዎች በከዋኞችና በታዳሚዎች ድምፅ ብቻ የሚገለጹ አይደሉም፡፡ በከዋኞችና ታዳሚዎች የሰውነት እንቅስቃሴ፣ በመከወኛ ቁሶች ድምፅ ጭምር የሚገለጹ ናቸው፡፡

በመሆኑም በቀብር ስርዓት አፈፃፀም ወቅት ስርዓቱ ማህበረሰቡ "ተገቢ ነው" በሚለው መንገድ እንዲከናወን የሚያደርጉ በአልቃሾች፣ በሃይማኖት መሪዎች፣ በአቅራሪዎችና በፎካሪዎች ድምፅ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ እንዲሁም ለስርዓቱ መከወኛ በሚወጡ ቁሶች የሚገለጹ ጠቋሚዎች (markers) ስለሚኖሩ ይህንኑ ማጤን ጠቃሚ ይሆናል።

### 2.2.4.7 የመከወኛ ቁሶች

አብዛኞቹ የስነቃል ዘርፎች በሚከወኑበት ወቅት ለስርዓቱ ማድመቂያነት የሚወጡ አንዳንድ ቁሶች አሉ። እነዚህ ቁሶች በማህበረሰቡ ውስጥ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ (እምነታዊ) መሠረት ያላቸው ናቸው። በነዚህ ቁሶች ማህበረሰቡ ለአገሩ ያለውን ፍቅር፣ ለወገኑ ያለውን ክብርና ታማኝነት፣ ለጠላቱ ያለውን ኃያልነት እና አይበገሬነት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በእጁ ጠመንጃ፣ ጋሻ፣ ጎራዴና ጦር ይዞ በመነቅነቅ ወኔውንና ስሜቱን ይገልፅባቸዋል። ከቀደመው ትውልድ የተረከበውን፣ የሱነቱ መገለጫ የሆነውን የአለባበስ ስልት፣ ምግብና አመጋገብ ያሳይባቸዋል። የሚከተለውን ሃይማኖት (እምነት) ያንፀባርቅባቸዋል፤ መልዕክትም ይለዋወጥባቸዋል። እነዚህን ቁሶች በተመለከተ ዣን ቫንሲና፤

> *Objects as proof of a certain event or as mementos of a past happening are quite common. In the Hopi, …we see the Hopi produce a feather shrine (tiponi) …as proof of an earlier agreement about the boundary between Navaho and Hopi. Wampum were used in the eastern United States in similar ways as proofs of treaties and clues of memory. Similarly a fire brand kept by an Anyi (Ivory Coast) family substantiated their ancient royal status (Jan Vansina, 1985:44).*

በማለት ለክዋኔ የሚወጡ ቁሶች በየሀገሩ መኖራቸውንና ታሪካዊ መሠረት ያላቸው መሆናቸውን ገልፀዋል።

ሩት ፊነጋን ደግሞ የውደሳ ግጥሞችን ባህርይ፣ የመከወኛ ምክንያትና ለክዋኔያቸው የሚያስፈልጉ ቁሶችን አስመልክተው ሲገልፁ የማላዊ ኢሚጉቦ (Imigubo)፣ የደቡባዊ ባንቱ ቤምባ (Bemba)፣ የሶማሊያ ጊርአር (Geeraar)፣ የኦሮሞ ጌሬርሳ (Gheraera)፣ የዮሩባ ኢጃላ (Ijala)፣ የዙሉ አማሁቦ (Amahubo)፣ ሲከወኑ በአብዛኛው ወንዶች ጦር፣ ጋሻ፣ ጎራዴ፣ ጠመንጃ፣ ከበሮ፣ ዋሽንት፣ ደወል፣ ፊሽካ፣ ቀንድ፣ ወዘተ. በመያዝ ፈረስ ላይ ሆነው ጀግኖችን እንደሚያወድሱና ሴቶች ደግሞ እልል (lili, lili…) እያሉ ክዋኔውን እንደሚያጅቡ አመልክተዋል (ፊነጋን፤ 1970፣209-212)።

በሌላ በኩል አንዳንድ ቁሶች ተበታትኖ በሰፈረ ማህበረሰብ ውስጥ በመልእክት መለዋወጫነት ሲያገለግሉም ይታያሉ።

> *In various parts of Africa South of the Sahara and in New Guinea, where the languages are tonal, drum rhythms are used to transmit information. In some West Africa Kingdoms drum slogans and poems recorded historical information. Elsewhere, where drums were used for long distance communication, the drum names and slogans often preserve historical information (Jan Vansina, 1985:46-47).*

ከላይ ባለው ገለፃ መሠረት የከበሮዎች ድምፅና የምት ስልት ተራርቀው ያሉ ሰዎች መረጃ እንዲለዋወጡ ከሚያስችሉ መሳሪያዎች ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው። በኛ አገርም በአንዳንድ አካባቢዎች ነጋሪት ሲመታ (ሲጎሰም)፣ መለከትና ጥሩንባ ሲነፋ፣ ጥይት ሲተኮስ እንደድምጹ ሁኔታ የእድር ስብሰባ፣ የታቦት ንግስ፣ የሠርግ፣ የቀብር፣ ወዘተ. እየተባለ ይተረጎማል።

ከዚህ በላይ በተለገጹት አንዳንድ አካባቢዎች የተጠቀሱት የክዋኔ ማጀቢያ ቁሶች አብዛኞቹ ይህ ጥናት በሚያተኩርበት ማህበረሰብ የቀብር ስርዓት ክዋኔ ወቅት የሚዘወተሩና የተለያየ ተግባር ያላቸው ናቸው። ከነዚህም መካከል ጠመንጃ፣ ጋሻ፣ ጎራዴ፣ ጦር፣ ከበሮ፣ አልባሳት፣ ወዘተ. ይገኙበታል።

እስከአሁን በተደረገው ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት ጥናቱ በትኩረት ሊያያቸው ስለሚገቡ ነጥቦች ለማንሳት ተሞክሯል። ለማጠቃለል ያህል አንድ ፎክሎረኛ አንድን ክዋኔ ለማጥናት ሲነሳ በከዋኙ የግል ድራማዊ ሁኔታ (performer's own dramatization)፣ የአከዋወን ስልት (performing style)፣ ምትን የተከተለ እንስቅቃሴ (rhythmic movement)፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎች (gestures and facial expressions)፣ በከዋኙና በታዳሚዎች መስተጋብር (interactions between performer and audience)፣ በአጠቃላይ ክዋኔውና እያንዳንዱ ድርጊት ምን፣ ለምን፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ በምን፣ በማን፣ ለማን፣ ወዘተ. እንደሚከወን በትኩረት ማጥናት እንዳለበት የመስኩ ምሁራን ያስገነዝባሉ (ፊነጋን፣ 1977፣ 214፤ ባውማን፣ 1977፣ 28፤ ማክዶናልድ፣ 1972፣410፤ ማርታና ማርቲን፣ 2005፣155፤ ፊቃደ፣ 1999፣11)።

## 3. ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢ ዳራ

የላይ አርማጭሆ ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት በሰሜን ጐንደር መስተዳድር ዞን ከሚገኙ 24 ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው። ወረዳውን በሰሜን ምእራብ ታች አርማጭሆ ወረዳ፣ በምስራቅ ወገራ ወረዳ፣ በምዕራብ ጭልጋ ወረዳ፣ በደቡብ ጐንደር ዙሪያና ደንቢያ ወረዳዎች ያዋስኑታል።

ላይ አርማጭሆ ወረዳ 1292.7 ስኩዌር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት አለው (ምንጭ፣ የሰሜን ጐንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ዓመታዊ መጽሔት፣ 2001፣ ገጽ 96)። የህዝብ ብዛቱም እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም በተካሄደው የህዝብና የቤት ቆጠራ መሠረት 79513 ወንድ፣ 78284 ሴት በድምሩ 157797 ነው።

ከዚሁ የህዝብ ቁጥር ውስጥ 5458 ወንድ እና 7088 ሴት በከተማ፣ 74055 ወንድና 71196 ሴት በገጠር ቀበሌዎች የሚኖር ነው። ከአጠቃላዩ ህዝብ ቁጥር 96% የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ሲሆን ቀሪው 4% ደግሞ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነው።

የወረዳው ዋና ከተማ ትክል ድንጋይ ትባላለች። ከተማዋ ከዞኑ ከተማ ጐንደር በስተሰሜን 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።

በወረዳው ሠላሳ ሶስት የገጠርና አንድ የከተማ በድምሩ ሰላሳ አራት ቀበሌዎች ይገኛሉ (ምንጭ:- የላይ አርማጭሆ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽህፈት ቤት ቢሮ)።

ወረዳው ከባህር ወለል በላይ ከ1500 እስከ 2700 ሜትር ከፍታ ሲኖረው ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከፍተኛው 1500 ሚሊ. ሜትር፣ ዝቅተኛው ደግሞ 1200 ሚሊ. ሜትር ነው። የወረዳው ዓመታዊ የሙቀት መጠኑ ከፍተኛው 28 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ፣ ዝቅተኛው 18 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ነው። የመሬት አቀማመጡን በተመለከተ 17% ሜዳማ፣ 68% ተራራማ፣ 15% ሸለቆዋማ ነው (ምንጭ:- የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ቢሮ የ2002 ዓ.ም የ2ኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት፣ ገጽ 1)።

የወረዳው የአየር ጸባይ ሶስት ዓይነት ሲሆን እነዚህም ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላማ ናቸው። በወረዳው ከሚገኙ ጠቅላላ ቀበሌዎች 22 ቀበሌዎች ወይና ደጋ፣ 9 ቀበሌዎች ቆላማና 2

ቀበሌዎች ደግሞ ደጋማ የአየር ጸባይ ያላቸው ናቸው (ምንጭ፡- የወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽህፈት ቤት ቢሮ)፡፡

በወረዳው አርባ አራት የመጀመሪያ ደረጃ፣ አንድ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃና አንድ የመሠናዶ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ (ምንጭ፣ የሰሜን ጐንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ዓመታዊ መጽሔት፣ 2001፣ ገጽ 57)፡፡

ሁለት ጤና ጣቢያዎችና ሃያ ስምንት ጤና ኬላዎች በድምሩ ሰላሳ የሚሆኑ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በወረዳው ይገኛሉ (ምንጭ፣ ከላይ የተጠቀሰው፣ ገጽ 59)፡፡ በወረዳው ቁጥራቸው መቶ ሰላሳ የሚደርሱ አብያተ ክርስቲያን ይገኛሉ (ምንጭ፡- የወረዳው ቤተ ክህነት ጽህፈት ቤት)፡፡

በወረዳው ከሚገኙ አጠቃላይ አስራ ሰባት መስጊዶች ውስጥ አስራ ስድስቱ በገጠር ቀበሌዎች፣ አንዱ ደግሞ በወረዳው ከተማ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

በዚሁ ወረዳ የተለያየ የዘር ግንድ ያላቸው ህዝቦች ይኖራሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ቅማንት፣ ቤተ እስራኤላዊ (በአካባቢው አጠራር "ካይላዎች") እና አማራ ይገኙበታል፡፡

ምንም እንኳ፣ በዚሁ ወረዳ የሚኖሩ የቅማንት ብሔረሰብ አባላት በዚሁ ወረዳ ለረዥም ጊዜ የኖሩና አብዛኞቹ የዘር ሀረጋቸው ከዚሁ ከቅማንት የመጣ እንደሆነ ቢናገሩም ቋንቋቸው፣ እምነታቸውና ባህላቸው በአካባቢው ከሚኖረው ማህበረሰብ የተለየ አይደለም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አጥኚዎች እንደሚሉት በአካባቢው የሚኖረው የሌላው ማህበረሰብ ተጽዕኖ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ስለዚሁ ብሔረሰብ አመጣጥ፣ ቋንቋ፣ ባህልና እምነት ጥናት ያደረጉ ሰዎች ብሔረሰቡ በዚሁ ወረዳ በሚገኙ የተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች ሰፍሮ እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ደስታ ተክለ ወልድ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ቅማንት ህዝብ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል፡፡

> ቅማንት፤ (ከመአንተ)፤ የነገድ ስም፤ በበጌምድር አውራጃ በከርከር በጭልጋ ያለ ህዝብ፡፡ አንድ ቅማንት ዐደን ዐድኖ ከደን ሲወጣ አንድ... አገኘውና መኑ አንተ አለና ቢጠይቀው፤ ከመ አንተ ብሎ ስለመለሠለት በዘመን ብዛት ከመአንተ በማለት ነገዱ ቅማንት ተባለ ይላሉ፡፡ ዳግመኛም አለቃ ታዬ የፃፉትን የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ተመልከት (ደስታ ተክለወልድ፤ 1962፣ 845)፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ የቅማንት መገኛ በማለት ከጠቀሷቸው ቦታዎች መካከል ከርከር አንዱ ነው። ከርከር በላይ አርማጭሆ ወረዳ ከሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ሁለት ቀበሌዎችን የያዘ ቦታ ነው። ከርከር ባለእግዚአብሔርና ከርከር መድኃኔዓለም የሚባሉትን።

ደስታ የጠቀሱትን የአለቃ ታዬን "የኢትዮጵያን ህዝብ ታሪክ" የሚለውን መጽሐፍ ስንመለከት ደግሞ ስለዚሁ ህዝብ የሚከተለው ሀሳብ ሰፍሮ እናገኛለን፤ *«...የቅማንቶች አባት አይነር ሚስቱን እንተላን ይዞ አዋድራ ከነዓን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ሰው ሳያየውና ሳያውቀው በከርከር ዱር በርሃ ውስጥ አውሬ አድኖ የዱር ፍሬ ለቅሞ እየበላ ብዙ ዘመን ተቀመጠ» (አለቃ ታዬ፣ 1955፣13)።*

በዚሁ ወረዳ የሚገኙ ብዙ የገጠር ቀበሌዎችን የቅማንት ብሔረሰቦች መገኛዎች እንደሆኑ የጠቀሱ ምሁራን ከላይ የተመለከቱት ብቻ አይደሉም። ሌሎች ምሁራንም አሉ።

ከነዚህም ውስጥ አቶ ነጋ ጌጤ "የቅማንት ህዝብ ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው ስለዚሁ ብሔረሰብ አመጣጥ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> የቅማንቶች የዘር ምንጭ የኖህ ልጅ ካም ነው። ካም ከነዓንንና ሌሎችን ወለደ። ከነዓን የኻማቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደቅማንት ወይም አገው የሚባሉት በለውጡ ሂደት የተነሳ ወደ አማራነትና ትግሬነት የተለወጡት ህዝቦች አባት ነው። ስለሆነም የቅማንቶች አባት የከነዓን የልጅ ልጅ አዳረይኪን የቅማንት ዘር መነሻ አባት ናቸው (ነጋ፤ 1993፣3)።

ባዩ ቦጋለ የተባሉ ፀሐፊም ስለቅማንት የሚከተለውን ብለዋል።

> የቅማንት አፈ-ታሪክ ጥንታዊና የመጀመሪያው የባህል ጀግና ከሆነው ከአይነር (ያነር) ይጀምራል። ስለአይነር ብዙ ስለማይታወቅ ብዙ አፈ-ታሪክ አዋቂዎች የእሱ ልጅ የሆነውን አይደርኪን ይተካሉ። እንደ ልጁ አይደርኪና እንደ የልጅ ልጁ ክብርዋ፣ አይነር "የመጀመሪያው ቅማንት በኢትዮጵያ" ተብሎ ይታወቃል። አንዳንድ መረጃ ሰጭዎች የእብራውያንን የዘር ሀረግ በመምዘዝ አይነር የከነዓን ልጅ አርዋዲ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ የሚያስረዱ ሲሆን ሌሎች አፈታሪኮች ደግሞ የአርዋዲ ልጅ አይነር ነው በመጀመሪያ የመጣው ይላሉ። ነገር ግን የአይነር ሚስት አንተላ እየተባለች ትጠራ እንደነበር ሁሉም ይስማማሉ (ባዩ፤ 1993፣57)።

ሁሉም አጥኚዎች የህዝቡን የዘር አመጣጥ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ አሁን የሚገኝባቸውን ቦታዎች ጭምር አመልክተዋል። ይኸውም ከላይ በአለቃ ታዬና በደስታ ስራዎች ከተገለጸው አካባቢ በተጨማሪ ይህ ህዝብ በላይ አርማጭሆ ወረዳ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች

(በከርከር፣ በዋላጅ፣ በጋሻ፣ በጋላገር፣ በትክል ድንጋይ፣ በጅሃ፣ በከች ዓይነት ውሃ፣ በጃኒፈንቀራ፣ በጭላና ደወል፣ በአሸላ፣ በኮሶጌ) በብዛት ሰፍሮ እንደሚገኝ ተገልጾ እናገኛለን (ነጋ ጌጤ፣ 1993፣1፤ ባዩ ቦጋለ፣ 1993፣ የመፅሐፉ መቅድም ላይ)።

እ.ኤ.አ በ1994 በተካሄደው የኢትዮጵያ ህዝብና ቤት ቆጠራ ደግሞ በሳንጃ፣ በላይ አርማጭሆ፣ በወገራ፣ በጐንደር ዙሪያ፣ በደምቢያ፣ በጭልጋ፣ በመተማ፣ በቋራ፣ ወረዳዎች በድምሩ 192271 የቅማንት ህዝብ እንደሚኖር ተገልፆ እናገኛለን (Office of Population and Housing Census, 1994:110-110)። ከዚያ ወዲህ በተደረጉ የህዝብና የቤት ቆጠራ ሪፖርቶች ላይ ግን ስለዚህ ህዝብ ብዛት የተገለጸ ነገር አልተገኘም።

ከዚህ በላይ ስለቅማንት ህዝብ መጠነኛ ዳራ መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት በዚሁ ወረዳ የተለያየ የዘር ግንድ ያላቸው ህዝቦች መኖራቸውንና ከነዚህም መካከል የቅማንት ህዝብ አንዱ መሆኑን ለማመልከት እንጂ የጥናቱ ትኩረት በዚሁ ህዝብ ባህል፣ ቋንቋና ሃይማኖት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሆኖ አይደለም።

በዚሁ ወረዳ የሚኖረው ህዝብ ኑሮ የተመሠረተው በእርሻ ላይ ነው። በወረዳው ቆላማ አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ ከብት፣ ንብ በማርባትና እንደ ኑግ፣ ተልባ፣ ሰሊጥ፣ ጥጥ፣ ማሽላ፣ በቆሎ ዳጉሳ፣ ሩዝ፣ ለውዝና በርበሬ በማምረት የሚተዳደር ሲሆን በደጋማና ወይናደጋማ አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ ደግሞ ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ገብስና አንዳንድ የጓሮ አትክልቶችን (እንደ ሽንኩርት፣ ድንች፣ ሎሚ፣ ፓፓያ፣ ብርቱካን፣ ወዘተ.) በማምረት የሚተዳደር ነው። ይሁን እንጂ በወረዳው ከሚገኙ ህዝቦች መካከል ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ነዋሪዎች በሽመናና በንግድ (በተለይም በልብስ ስፌት) የተሠማሩ ሙስሊሞች፣ በብረት ቅጥቀጣና በሸክላ ስራ የሚተዳደሩ ቤተ እስራኤላዊያን (በአካባቢው አጠራር "ካይላዎች" ወይም "ፈላሾች") ይገኛሉ።

የአካባቢው ማህበረሰብ ቤተ እስራኤላዊያንን "ፈላሻ" እያለ የሚጠራቸው ከእስራኤል ተሠደው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ መሆናቸውን ለማመልከት ይመስላል። "ካይላ" የሚላቸውም በሌሎች የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዘንድ ቡዳ እንደሚባለው ሁሉ "እነዚህ ማህበረሰቦች ከራሳቸው ዘር ውጭ የሆነ ማንኛውንም ሰው በዓይናቸው አተኩረው ካዩት ያ ሰው ይሞታል፤ በሌሊት ከሰውነት ወደ ጅብነት በመለወጥ ሰዎችን እና እንስሳትን ይበላሉ፤ ቀን ደግሞ ሰው ይሆናሉ" ተብሎ በአካባቢው ማህበረሰብ ስለሚታመን ነው። ማህበረሰቡ

አንዳንድ ጨካኝና ክፉ የሆኑ ሰዎችን "ካይላ" እያለም ይሠድባል። በመሆኑም በማህበራዊ ህይወታቸው በአብዛኛው ከሌላው ማህበረሰብ አባላት የተገለሉ፣ የሚያርሱት መሬት ስለሌላቸው ኑሮዋቸውን በብረት ቅጥቀጣና በሸክላ ስራ ላይ መስርተው የሚኖሩ ቤተ እስራኤላዊያን በዚህ ወረዳ ልዩ ልዩ ቀበሌዎች ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ማህበረሰቦች ወደ እስራኤል እየሄዱ ቁጥራቸው ከቀድሞው ቢቀንስም ይኖሩባቸው የነበሩ፣ አሁንም የተወሠኑ ሰዎች የሚኖሩባቸውን አካባቢዎች ሌላው ማህበረሰብ "ካይላ ሜዳ" እያለ ሲጠራ ይሠማል።

የሸክላና የብረት ቅጥቀጣ ሙያን ከነዚሁ የማህበረሰብ ክፍሎች በመማር በዚሁ ሙያ የሚተዳደሩ ሌሎች የማህረሰብ አባላትም በወረዳው በብዛት ይታያሉ።

የወረዳው ብዙ ቀበሌዎች (በተለይ ደጋና ወይናደጋ አካባቢዎች) ለዘመናት በመታረሱ ምክንያት ይመስላል መሬቱ የተራቆተ ነው። ይሁን እንጂ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ለዘመናት ተጠብቀውና ተከብረው የሚኖሩ፣ የማይታረሱ አልፎ አልፎ የሚታዩ ጥቅጥቅ ያሉ ደኖች አሉ። እነዚህ ደኖች (በአካባቢው ማህበረሰብ አጠራር "ድግና" ይባላሉ)፣ የቅማንት ህዝብ የድሮ የአምልኮ ስርዓት መፈጸሚያና የሞቱ ስዎች መቀበሪያ የነበሩ ቦታዎች ናቸው።

## 4. በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፤

## በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው

በላይ አርማጭሆ ወረዳ ማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ ትርጉም ከሚሠጣቸው ማህበራዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ የቀብር ሥነ ሥርዓት ነው። ይህ ማህበረሰብ "ታቦትና አስከሬን አንድ ናቸው" የሚል አባባል አለው። ዕድሜው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆነ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት አቅሙ በፈቀደለት መጠን ዳስ በማሳራት፣ የመቃብር ጉድጓድ በመቆፈር፣ አስከሬን በመሸከም፣ አስከሬን በመሸኘት፣ ለወዳጅ ዘመድ መርዶ በመንገር፣ የሟች ቤተሠቦችን በማጽናናት፣ በማስተዛዘንና በሌሎችም ክንውኖች የመሳተፍ ማህበራዊ ግዴታ አለበት።

ሁኔታዎች ፈቅደውለት በቀብር ሥነ ሥርዓት የማይሳተፍ ሰው ቢኖር በዚሁ ማህበረሰብ ዘንድ ይጠላል፤ ከሁሉም ማህበራዊ ግንኙነቶች ይከለከላል (ይገለላል)።

ይህ ለወረዳው ማህበረሰብ ማህበራዊ ህይወት መጥበቅና መላላት መሠረት የሆነው የቀብር ሥነ ሥርዓት ደግሞ የራሱ የሆኑ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ተግባራት የሚከናወኑበት፣ የራሱ የሆኑ ሂደቶችም ያሉት ነው።

በዚህ ወረዳ የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት ጐልተው የሚታዩ ሦስት ዓቢይ ሂደቶች አሉ። እነዚህንም የቅድመ ሞት ዝግጅት (ግለሰቡ ከመሞቱ ጥቂት ቀናት ቀድመው የሚከናወኑ)፣ ጊዜ ሞት (ግለሰቡ እንደሞተ የሚከናወኑ)፣ ከቀብር በኋላ (ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ የሚከናወኑ)፣ ብሎ መከፋፈል ይቻላል። የዚህ ጥናት ርዕስ የቀብር ሥነ ሥርዓት የሚል ቢሆንም፣ የቅድመ ሞት ዝግጅት የሚለውን ሂደት ማየት ያስፈለገበት ምክንያት አለ። ይኸውም በጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት የሚታዩ አንዳንድ ክንውኖች በቀብር ዕለት ብቻ የሚታዩ ክስተቶች ሳይሆኑ ቀደም ብለው ተዘጋጅተው የሚቆዩ በመሆናቸውና ስለ ዝግጅታቸው መጠነኛ ዳራ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

### 4.1 የቅድመ ሞት ዝግጅት

የቅድመ ሞት ዝግጅት በዚሁ ወረዳ ማህበረሰብ ውስጥ አንድ ሰው በጠና ታሞ እንደማይድን ከተገመተበት ጊዜ ጀምሮ ነፍሱ ከስጋው እስክትለይ ድረስ የሚደረጉ

ክንውኖችን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ አገላለጽ በድንገተኛ አደጋ የሚሞቱ ሰዎችንና የሚደረግላቸውን ሥነ ሥርዓት የሚያመለክት አይደለም፡፡

በዚሁ ወረዳ አንድ ሰው ህመሙ ፀንቶ የማይድን መሆኑ እንደተገመተ ለቅርብ ወዳጅ ዘመዶቹ በሙሉ፣ "በጠና ታሟል፤ ተጠብቋልና ድረሡ" የሚል መልዕክት ይላክላቸዋል፡፡ ይህ መልዕክት የደረሳቸው ወዳጅ ዘመዶችም ወዲያውኑ ወደ በሽተኛው ቤት ይመጣሉ፡፡ ወዳጅ ዘመዶቹ እንደተሠባሠቡ፣ በሽተኛው የነፍስ አባት ያለው ከሆነ የነፍስ አባቱ፣ ከሌለው ደግሞ ሌላ በአካባቢው የሚኖሩ ቄስ ተለምነው እንዲመጡ ይደረጋል፡፡ ከዚያ ቄሱና ቁጥራቸው ከሁለት እስከ ሦስት የሚደርስ የአካባቢው ሽማግሌዎች በሽተኛውን ከብበው ይቀመጡና ቤት ውስጥ ያለው ሰው በሙሉ እንዲወጣ ያደርጋሉ፡፡ ይህ የሚሆነው የኑዛዜ ሥርዓትን ለመፈጸምና ሥርዓቱም ምስጢራዊ በሆነ መንገድ የሚከናወን በመሆኑ ነው፡፡

### 4.1.1 የኑዛዜ ሥርዓት አፈፃፀም

በዚሁ ወረዳ ማህበረሰብ፣ ኑዛዜ ማለት የአንድን በሽተኛ ግለሠብ የመጨረሻ ሀሳብ በጽሑፍ ወይም በቃል የመቀበል ሂደት ነው፡፡ አፈፃፀሙም የአካባቢው ሽማግሌዎች ታዛቢ በመሆን፣ የነፍስ አባቱ ወይም ተለምነው የመጡት ቄስ ደግሞ መፃፍ የሚችሉ ከሆነ ራሳቸው፣ የማይችሉ ከሆነ ግን ሌላ ቅርብ ዘመድ የሆነና መፃፍ የሚችል ሰው ሆነው፣ ቄሱ እየጠየቁ፣ በሽተኛው የሚሠጣቸውን መልሶች በመፃፍ ሥርዓቱ ይካሄዳል፡፡ መፃፍ የሚችል ከሌለ ግን ኑዛዜው በቃል ብቻ ይፈጸማል፡፡ አንዳንዴ ራሱ በሽተኛው መፃፍ የሚችል ቢሆን እንኳ ከህመሙ የተነሳ እጆቹ ስለማይታዘዙለት ፀሃፊው ብዙ ጊዜ ሌላ ሰው ይሆናል፡፡

በኑዛዜ ወቅት የሚጠየቁት ጥያቄዎች ብዙ ጊዜ በንብረት ወራሽ ማንነት፣ በሽተኛው የተበደረው ወይም ያበደረው ገንዘብ መኖር አለመኖር፣ በህይወት ዘመኑ ለማንም ሳያሳውቅ የሠራቸው ድርጊቶች (ለምሳሌ፣ ከህጋዊ ጋብቻ ውጭ የወለዳቸው ልጆች መኖር አለመኖር፣ ከሃይማኖታዊ ትዕዛዛት የወጡ ድርጊቶች፣ እንደ ዝሙት፣ ስርቆት፣ በሀሠት መመስከር፣ ወዘተ. ያሉትን) መፈፀም አለመፈፀም ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ኑዛዜው በጽሑፍ የተከናወነ እንደሆነ፣ ጽሑፉ ለበሽተኛው ይነበብለታል፡፡ ከተስማማበት (የሚጨምረውና የሚቀንሰው ከሌለ) የኑዛዜ ወረቀቱ በቄሱ ወይም በአንድ ሽማግሌ ቤት በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ የለቅሶ ሥነ ሥርዓቱ እንደተገባደደ(ብዙ ጊዜ ከወራት በኋላ ነው)

ይኸው የኑዛዜ ወረቀት ይወጣል፡፡ ኑዛዜው በቃል የተከናወነ ከሆነ ደግሞ ሥርዓቱን ያስፈጸሙ ሰዎች ይገኙና በሟቹ ቃል መሠረት የንብረት ክፍፍል ይደረጋል፡፡

የኑዛዜ ሥርዓት የሚፈጸምበትን ዓላማ አስመልክቶ፣ አቶ ተሠራ አምባው የተባሉ መረጃ አቀባይ፣ የግለሠቡን ሞት ተከትሎ በሚደረግ የንብረት ክፍፍል ወቅት በወዳጅ ዘመድ መካከል ግጭት እንዳይፈጠር ስለሚረዳና ሟችም ስለሠራው ሃጢያት ሳይናዘዝ ቢቀር መንግስተ ሰማያት አይገባም ተብሎ በአካባቢው ማህበረሰብ ስለሚታመን እንደሆነ አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 7/2002 ዓ.ም)፡፡

### 4.1.2 ለዋናው ለቅሶና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች

የኑዛዜ ሥነ ሥርዓት ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መንገድ ከተከናወነ በኋላ ወደ ውጭ እንዲወጡ የተደረጉ ሠዎች ወደ ቤት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ቀጥሎ ለበሽተኛው ቅርብ የሆኑና በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች ተመርጠው ከበሽተኛው ጋር ውይይት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በቤቱ ውስጥ ፍርሃት ይነግሳል፤ በሽተኛው የሚናገራቸው የተቆራረጡ ቃላት ሆዱን ያባባው ሁሉ፣ ድምጽ ሳያሰማ ያለቅሳል፡፡ ሲያለቅስ ድምጽ እንዳያሰማ የሚከለከልበት ምክንያት የበሽተኛው ንግግር ጨርሶ እንዳይቋረጥና በሽተኛውም እንዳይረበሽ ሲባል ነው፡፡

በዚህ የውይይት ወቅት የሚነሱት ሃሳቦች በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ቅድመ ዝግጅት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ እነዚህም በቀብሩ ላይ የሚታረደውን የከብት ብዛት መወሠን (ቁጥሩ እንደሟቹ የሀብት መጠን የሚወሠን ሲሆን ከቤት ከሌለ ተፈልጎ እንዲገዛ ወይም እንዲለወጥ ይደረጋል)፣ እውቅ ፎካሪዎች ወደያሉበት አገር መልዕክት በመላክ ተዘጋጅተው እንዲጠብቁ ማድረግ፣ ለፉከራ ሥርዓቱ ማድመቂያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችና እንስሳት (እንደ ጠመንጃ፣ ጦር፣ ጎራዴ፣ ጋሻ፣ ዝናር ከነ ጥይቱ፣ ለምድ፣ በቅሎና ማስጌጫዎች፣ የሟች ቤተሠቦች የሚለብሷቸው አልባሳት፣ ጥሩንባ፣ ወዘተ.) ከያሉበት እንዲመጡ፣ የመገነገኛ ጨርቅ ከገበያ እንዲገዛ የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡

በዚሁ ወረዳ ማህበረሰብ ዘንድ ፎካሪዎች ለድካማቸው ብዙውን ጊዜ የሚከፈላቸው ዋጋ ባይኖርም፣ አንዳንዴ ግን በሽተኛው ብር፣ የእርሻ መሬት፣ አልያም የቀንድ ከብት እንዲሠጣቸው በቅድመ ዝግጅቱ ወይም በኑዛዜ ጊዜ ሊናገር ይችላል፡፡ በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ሲፎክሩ ደስ ያለው ታዳሚም ጥይት ጆሮዋቸው አስጠግቶ ወደ ላይ በመተኮስ፣ ብርም በመሸለም እንደሚያበረታታቸው አቶ ጌታ ጣፈጠ፣ አቶ አወቀ ታከለና አቶ ሙሌ

አውላቸው የተባሉ በወረዳው የሚገኙ እውቅ ፎካሪዎች አሥረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም)።

ሌላው የቅድመ ዝግጅት ስራ በቀብሩ ዕለት የሚሠበሠበውን ለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚሆን ቦታ ማዘጋጀት ነው። ይኸውም የሟቹን ደጃፍ አጥር በማፍረስ፣ እሾህና ቆንጥሮችን በማስወገድ የማለስለስ ስራ ከተከናወነ በኋላ ለቀስተኛውን ከዝናብ ወይም ከፀሐይ የሚከላከል ዳስ እንዲሠራ ማድረግ ነው። ዳሱ የሚሰራው ብዙ ጊዜ ከቅጠል፣ ከኑግና ከማሽላ አገዳ ነው። በቆርቆሮ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ከዚያ ረጃጅም ጣውላዎችንና ወንበሮችን ከጎረቤት፣ ጠፍጣፋ ድንጋዮችን ከሜዳ፣ ፈልጎ በማምጣት ለመቀመጫ አመቺ በሚሆኑበት መንገድ በዳሱ ውስጥ ይደረጋሉ። ቀሪው የዳሱ ክፍል ሳር፣ ገለባ ወይም ቅጠል ይጎዘጎዝበታል። በዚህ ቅድመ ዝግጅት ወቅት «ለእዝን» እንጀራ፣ ጠላና የተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል እህልም እንዲፈጭ ይደረጋል።

«እዝን» የቀብር ሥነ ሥርዓት እንደተከናወነ ወዲያውኑ ለለቀስተኛው የሚቀርብ እህል ውሃ ነው። ብዙ ጊዜ ለእዝን የሚቀርበው ምግብ እንጀራ፣ ስጋ ወይም የባቄላ (የሽንብራም ሊሆን ይችላል) በቆልት ነው።

ይህንን ለሟች የሚደረግ የእዝን ምግብ አቀራረብ የሚወስነው ሟቹ የሚሞትበት ጊዜና የሟቹ የአቅም ሁኔታ ነው። ይኸውም ሟቹ የሞተበት ቀን ረቡዕና አርብ በመሳሠሉት የፆም ቀናት ከሆነ፣ ሁለት ሦስት ቀናት አስከሬኑ ሳይቀበር እንዲሠነብት ይደረግና በፍስክ ቀን እንዲቀበር ይሆናል። ይህ የሚሆነው ለእዝን የሚቀርበው ምግብ፣ ስጋ እንዲሆን ሲፈለግ ነው። ይህንኑ የሚወስኑትም የሟች ቤተሠቦች ናቸው። ሟቹ ለረጅም ጊዜ በሚፆም ወቅት ከሞተ እና ለእዝን የሚቀርብ ከብት የሌለው ከሆነ ግን፣ ለለቀስተኛው የሚቀርበው ምግብ ባቄላ ወይም ሽንብራ እንዲሆን ተወስኖ በዚሁ ወቅት እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

ከላይ ከተገለጸው ምክንያት በተጨማሪ በዚሁ ማህበረሰብ አስከሬን ሳይቀበር ሁለት ሶስት ቀናት የሚሰነብትበት ሌላም ምክንያት አለ። ይህም ሩቅ አገር የሚኖሩ የሟች ዘመዶች በመልእክተኛ እየሰሙ መጥተው እንዲቀብሩ እና ሃዘናቸውን ከወዳጅ ዘመድ ጋር እንዲካፈሉ ለማስቻል ሲባል የሚሆን ነው። ይኸ ደግሞ በሌላ በኩል ለሟች ቤተሠቦች ጠቀሜታ አለው። ይህም የሟች ቤተሠቦች በየጊዜው በሚመጣ ለቀስተኛ ምክንያት እንዳያለቅሱና በመስተንግዶ እንዳይጎዱ ይረዳል።

በሽተኛው እስከሚሞት ድረስ ወዳጅ ዘመዶቹ ሳይለዩት፣ እነዚህ ቅድመ ዝግጅቶችም እየተደረጉ ይቆያል።

## 4.2 ጊዜ ሞት

በሽተኛው ህይወቱ ሲያልፍ በቤት ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ አምርሮ ያለቅሳል። ለቅሶው ድብልቅልቅ ይላል። ዋይታ፣ ጩኸት ይበዛል። ሴቶች ይወድቃሉ፤ ይነሳሉ። በዚህ ወቅት የሟች ወንድም ወይም ወንድ ልጅ ጠመንጃ ይዞ ከቤት ይወጣና ደጃፉ ላይ በመሆን አንድ ጥይት ብቻ ወደ ሠማይ ይተኩሳል።

የዚች የአንድ ጥይት መተኮስ በማህበረሰቡ ውስጥ ትርጉም አለው። መረጃ አቀባዮች ስለዚህ ድርጊት ሲናገሩ፣ "አንድ ጥይት ብቻ ስትተኮስ፣ በተለይ መንደር ውስጥ ከሆነ፣ ነገር አላት፤ ጫካ ቢሆን ግን ለሚዳቋ፣ ለዝግራ ተተኮሰች ይባላል፤ መንደር መሃል ከሆነ ግን መርዶ ነው ይባላል" (አቶ ሞላ መኮንን፣ ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002ዓ.ም)።

ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ የተባሉ ሌላ መረጃ አቀባይ ደግሞ፤

> ተመንደር ግድም እምትተኮስ አንድ ጥይት የድረሱልኝ ናት። በተለይ በጠና ታሞ የቆየ ሠው ታለና በየመንደሩ ወሬው ሲወራ ተቆየ፣ ያ የተጠበቀው ሠው አረፈ ይባላል። እሂ እንግዲህ የጥይቲቱ ድምጥ ተዚያው ተታማሚው መንደር የተሰማ እንደሆነ ነው። በዚህ ጊዜ እሩቅ ያለ ዘመድ ሁላ ተቤቱ እየወጣ ያዳምጣል። ዛዲያ ሠው ሲላቀስ፣ ውሻውም ሲንጫጫ፣ ተሠማ ሁሉም አይ ወንድሜ! እያለ ወደዚያው ይሄዳል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)

በማለት የአንድ ጥይት መተኮስን ትርጉም አስረድተዋል።

የማህበረሰቡ አሠፋፈር የተበታተነ በመሆኑ፣ የሰዎች ለቅሶና ጩኸትም ራቅ ብለው ለሚገኙ መንደሮች ሊሰማ ስለማይችል፣ይህችው አንድ ጥይት የድረሱልኝ መልዕክት፣ የመርዶ መንገሪያ መንገድ ናት። የአካባቢው ሰውም የጥይቷን ድምፅ ወደሰማበት አቅጣጫ እየመጣ፣ በዚህ መንገድ የለቀስተኛው ቁጥር እየጨመረ፣ ለቅሶውና ዋይታው እየበዛ ይሄዳል።

### 4.2.1 በምሽት የሚካሄዱ ሥነ ሥርዓቶች

ሟች ጥዋትም ይሙት ከቀትር በኋላ፣ ከላይ በተገለፀው መንገድ መንደርተኛው ሁሉ ወደ ሟች ቤት እየመጣ፣ ደጅ ላይ ተሰብስቦ በግምት እስከ ምሽት አንድ ሰአት ድረስ ይላቀሳል። ከቤት ካሉትና ከመንደር ከሚመጡት ለቀስተኞች መካከል በዕድሜ ጠና ያሉ የሟች የቅርብ

ዘመዶች (ብዙ ጊዜ ወንዶች ናቸው) ሮጠው ወደ ቤት ይገቡና ቤት ውስጥ ያለው ለቀስተኛ ሁሉ ወደ ደጅ እንዲወጣ ያደርጋሉ። ከዚያም ተጣድፈው ወደ አስከሬኑ በመሄድ የተከፈተ አፉንና ዓይኖቹን ይዘጋሉ። አስከሬኑ ያለበት አልጋ በተገኘው ልብስ (ብዙ ጊዜ ነጠላ ወይም ጋቢ ነው) ይጋረዳል። አስከሬኑ የተኛበት አልጋ ላይ የነበረው የጀንዲ ንጣፍ ይነሳና ሌላ ልብስ ይነጠፍበታል (ብዙ ጊዜ ውሃ ሊያሳልፍ የሚችል ልብስ አንዳንዴ ደግሞ ሰሌን ነው የሚነጠፈው)። ቀጥሎ አስከሬኑ ይታጠባል፤ የብልቱ ፀጉርም ይላጫል። ከዚያም በአልጋው ላይ ተስተካክሎ እንዲተኛ ይደረጋል። ከተኛ በኋላ ሁለቱ እጆቹ በቀኝና በግራ ጐኑ ትይዩ ከተዘረጉ በኋላ ከታፋዎቹ ጋር ይታሠራሉ። የሁለት እግሩ አውራ ጣቶችም በአንድነት ይታሠራሉ። ቀጥሎ አስከሬኑ ለብሶት በነበረው ጋቢ ይጠቀለልና ተደፍቶ በደረቱ እንዲተኛ ይደረጋል። ከዚያም ትከሻው፣ ጀርባውና ባቱ አካባቢ ትልልቅ ድንጋይ ይጫንበታል። አስከሬኑ ያለበት አልጋ ስር ድመት ይታሠርና ኩራዝ በማብራት አስከሬኑ ይጠበቃል። እነዚህ ሥርዓቶች ለምን እንደሚደረጉ የተጠየቁ መረጃ አቀባዮች ሲመልሱ፣ "አስከሬኑ የሚታጠበው ፍታት ለሚቆሙ ካህናትና ጥዋት ለሚገንዙ ሰዎች መጥፎ ሽታ እንዳይፈጥር ነው" ብለዋል (ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ፣ አቶ ተሠራ አምባው፣ ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5 እና መጋቢት 7/2002 ዓ.ም)። አቶ ብርሃን አዱኛ የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ አስከሬኑ የተለያዩ ቦታዎች የሚታሠርበትንና ድንጋይ የሚጫንበትን ምክንያት አስመልክተው፣ "ሬሳ ተንጋሎ ቢተኛ፣ ፊቱ የማበጥ፣ እግሮቹና እጆቹ የመታጠፍና የመድረቅ፣ ሆዱ የመነፋት፣ ነገር ይኖራል። ይህ ሲሆን ደግሞ ሰውነቱ ተሎ ይሸታል። እንዲህ እንዳይሆን ነው የሚታሠረውና ደንጊያ ሚደረግበት" በማለት አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)።

ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ የብልት ፀጉር መላጨትንና በጀርባ እንዲተኛ መደረግን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣ "እህ! ብልቱ ሚላጨው ተነገመናው እንዳይሄድ ነው። ደሞ ሬሳውን የሚገንዙ ሰዎች ቢያዩ ‹ምን ያለ ቤተሠብ ነው› ብለው ያነውራሉ፤ ያፍፋሉ። ተደፍቶ የሚያስተኙትም ደሞ ሆዱ ይነፋፋና ፈሳሽ፣ አንዳንድ ነገር ተሆዱ ወጥቶ እንዳያውክ ነው" በማለት ነው (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)።

አስከሬኑ ያለበት አልጋ ዙሪያውን በጋቢ የሚከለልበት ምክንያት አስከሬኑ በቀጥታ ሲታይ እንዳያስፈራና እንዳያስደነግጥ ተብሎ እንደሆነ፣ ከአልጋው ሥር ድመት ታስሮና ኩራዝ

በርቶ የሚጠበቅበት ምክንያት ደግሞ አስከሬኑም ሆነ የታሠረበት ነገር በዓይጥ እንዳይበላና እንዳይበላሽ ተብሎ እንደሆነ ወይዘሮ አሰለፍ አስረድተዋል።

እነዚህ ዕድሜያቸው ጠና ያሉ ሽማግሌዎች ይህንኑ ሥነ ሥርዓት እንዳጠናቀቁ፣ የተወሠኑት አስከሬኑን ይጠብቃሉ፤ የተወሠኑት ደግሞ ወደ ውጭ ይወጡና ከለቀስተኛው ጋር ይቀላቀላሉ። እነዚህ ወደ ውጭ የወጡ ሽማግሌዎች ሚናቸው እንደሌላው ቤተሠብ ብዙ ማልቀስ ሳይሆን ለቅሶው ሥርዓት እንዲይዝ ማስተናበር ነው።

እነዚህ አስተናባሪዎች ከለቀስተኛው መካከል ወጣት ወንዶችን ይመርጣሉ። ከዚያም ሁለት ሁለቱን እያጣመሩ የሟች ወዳጅ ዘመድ ወደሚገኝበት አገር ሁሉ መርዶ ይነግሩ ዘንድ ይልካሉ። ለምን ወንዶች ብቻና ሁለት ሆነው እንደሚላኩ አቶ ተሠራ አምባው ሲገልጹ፣ "ለምን ሁለት አድርገው እንደሚሰዱ አላውቅም፤ ወንዶች መሆናቸው ግን በምሽት ሁሉ በእግራቸው ስለሚጓዙ ይደክማቸዋል፤ በመንገድም አንዳንድ ችግር ሊያጋጥም ይችላል። ሴቶች ድካሙንም፣ ችግሩንም አይችሉትም ተብሎ ነው" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 7/2002 ዓ.ም)። ወይዘሮ አሠፋ በለጠ የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ፣ "አይ አንተ! ወንድ የሆነ እንደሆነ ዳገት ቁልቁለቱን ነጠቅ ነጠቅ ብሎ ይሄዳል፤ ሴት ግን አይሆንላትም። ውሻ እንኳ ው! ቢል ትፈራለች። ደሞ በምንገድ እኒ (ወንዝ ማለታቸው ነው) ቢሞላ፣ ጠሃይ ቢሆን፣ መች ትችላለች። ሴት ልጅ ልጩህ ብትልም አይሆንላትም። ድምጧ ሩቅ አይሠማም" በማለት ሴት ልጅ መርዶ ለመንገር የማትሄድበትን ምክንያት አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 16/2002 ዓ·ም)።

መርዶ ይነግሩ ዘንድ ወደየአቅጣጫው የተላኩት ወንዶች በመንገድ ለሚገኝ ዘመድ ሁሉ እየነገሩ ሌሊቱን በሙሉ ተጉዘው በየተላኩበት የመጨረሻ ሥፍራ ሲደርሱ (ጊዜው ብዙ ጊዜ ከንጋቱ 11፡30 እስከ 12፡30 ገደማ ነው) ከአካባቢው ከፍ ወዳለ ቦታ (ብዙ ጊዜ ጉብታ ወይም መጠነኛ ተራራ ነው) ላይ ይወጣሉ። ከዚያ በአካባቢው የሚገኝ የሟች ቅርብ ዘመድ የሆነን ግለሠብ ስም ጮክ ብለው "እያ እገሌ ኡው!" በማለት ይጣራሉ። ስሙ የተጠራው ግለሰብ "አቤት" ሲል፣ "እያ እገሌ ተጐድቷልና ኑ አቃብሩን ይላሉ፤ ቀብሩ በ--- ቤተ ክርሥቲያን ነው፤ ላልሠሙትም አሠሙልን" በማለት ያረዳሉ። መርዶውን የሰማ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ እንደዝምድናው ዓይነት "አዬ ወዳጄ፣ አዬ አባቴ፣ አዬ ወንድሜ" እያለ በየቤቱ ከተላቀሰ በኋላ፣ አንድ ቦታ ላይ ይሠባሠባል። ከዚያም የሟች ወዳጅ ዘመዶች ከየቤታቸው ለለቀስተኛ የሚሆን ምግብና መጠጥ በማምጣት በአህያ ይጭናሉ። ወንዶች ባንዲራ፣

ጠመንጃ፣ ጋሻ፣ ጉራዴ፣ ድባብ፣ ያሠባስቡና ሴቶች ከመሃል፣ ወንዶች ደግሞ ከፊትና ከኋላ በመሆን፣ የሟች የቀብር ሥነ ሥርዓት ወደሚፈጸምበት ቦታ ይጓዛሉ። በዚህ ጉዞ ወቅት ትንሽ የሚያለቅሱት ለሟች ቅርብ የሥጋ ዝምድና ያላቸው ሴቶች እንጂ፤ ሌሎች አያለቅሱም። በዚህ ጉዞ ወቅት ሴቶች መሃል ላይ የሚደረጉት አንድም ጉዞው ጥድፊያ ስላለበት ወድቀው እንዳይጐዱ፣ አንድም ብዙ ጊዜ ሴቶች ወደ ሟች አገር የሚያደርሰውን አቋራጭና ቀና መንገድ ስለማያውቁ እንደሆነ፣ እማሆይ ጥሩ ዓይነት ሺበሺ የተባሉ መረጃ አቀባይ ገልፀዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም)።

በዚህ አኳኋን ቀባሪው ህዝብ ከየቦታው እየመጣ እንዲሰባሰብ ይደረጋል።

ምሽት ላይ አስተናባሪዎች በዚህ ሁኔታ መርዶ ነጋሪዎች በየአገሩ ሄደው እንዲነግሩ ካደረጉ በኋላ፣ ቀጣዩ ተግባራቸው ወደ ካህናት መልዕክተኛ መላክ ነው። ወደ ካህናት የሚላኩት መልዕክተኞች ሁለት መልዕክቶችን ይዘው ይሄዳሉ። የመጀመሪያው መርዶውን ለካህናት ማርዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመቃብር ቦታ መጠየቅና እንዲሠጣቸው ማድረግ ነው። መርዶው የተነገራቸው ካህናት ልብሠ ተክህኖዋቸውን ለብሠው፣ ቅዱሳን መፃህፍት፣ መስቀል፣ ጃንጥላ፣ ከበሮ፣ ማጠንት፣ ጽናጽል፣ ወዘተ. ይዘው ወደ ሟቹ ቤት ይመጣሉ። በዚህ ጊዜ አስተናባሪዎች የአስከሬኑን ቁመት በገመድ፣ በሀረግ ወይም በማሽላ አገዳ ይለኩና የተለካበትን ነገር፣ አካፋ፣ ዶማ፣ ማጭድ፣ መጥረቢያ፣ አስይዘው ቁጥራቸው ከአምስት እስከ ስድስት የሚደርስ መቃብር ቆፋሪዎች ወደ ቦታው እንዲያመሩ ያደርጋሉ። ለዚህ ሥራ የሚመረጡት ሠዎች ለሟች ራቅ ያለ ዝምድና ያላቸው፣ በዕድሜ ወጣትና በአካል ፈርጠም ያሉ ናቸው። ለመቃብር ቆፋሪነት የሚመረጡት ሰዎች ለምን ለሟች ቅርበት የሌላቸው እንደሚሆኑ ሲጠየቁ፣ ወይዘሮ ስስት ውብነህና አቶ ጐዶ ጌጤ የተባሉ የማህበረሰቡ አባላት ሲያስረዱ፣ "አዘኑ የሟች ዘመዶችን እንዳይጐዳ ነው። አልቅሰው፣ የቀብር ቦታ ቆፍረው፣ ስንቱን ይችሉታል? ነገ እኮ ሌላውም ይሞታል፤ እነሱም ብድራቸውን ያስተዛዝናሉ፤ ይቆፍራሉ" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 12/2002 ዓ.ም) ። ቁፈራው የሚካሄደው የሟች ነፍስ እንደወጣች ማታ ወይም በቀብሩ ቀን ጥዋት ነው። ማታ ወይም ጠዋት የሚቆፈርበትን ምክንያት አስመልክተው ደግሞ አቶ አማረ መከተና አቶ ዘመነ ተሻገር ሲገልጹ፣ "ክረምት ታልሆነ ማታ ይቆፈራል፤ ክረምት ተሆነ ግን ዝናብ ጥሎ በጉርፍ ጉድጓዱ ሊደፈን ስለሚችል አይሆንም። በበጋ ማታ የሚቆፈረው ቆፋሪዎች ለማለዳ ሥራ እንዲደርሱ ነው" በማለት ነው (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 12/2002 ዓ.ም)። ማታ የመቃብር

ጉድጓድ የቆፈሩ ሰዎች ማለዳም በተለያዩ ስራዎች ይሰማራሉ። ለምሳሌ፣ ቅርብ አገር ለሚገኝ ወዳጅ ዘመድ መርዶ ይነግራሉ።

እነዚህ መቃብር ቆፋሪዎች ቤተ ክርስቲያን እንደደረሡ አንድ ካህን ለምነው ለመቃብር የተሠጠውን ቦታ እንዲባርኩ ያደርጉና መቆፈር ይጀምራሉ። መቃብር ቆፋሪዎች የሚይዟቸው መሳሪያዎች፣ የመቃብር ጉድጓዱን ለመቆፈር፣ አፈር ለማውጣት፣ አካባቢውን ለማጽዳት፣ ወዘተ. አገልግሎት የሚውሉ ናቸው። ሲቆፍሩ በመጀመሪያ ምስራቅና ምዕራብ አቅጣጫን (ፀሐይ መውጫና ፀሐይ መግቢያ ይሉታል) ይለያሉ። ቀጥሎ አስከሬኑ የተለካበትን ነገር በነዚህ አቅጣጫዎች ትይዩ ያስቀምጣሉ። ከዚያ ጥልቀቱ በግምት ሁለት ሜትር፣ ስፋቱ ደግሞ አንድ ሜትር ተኩል የሚሆን ጉድጓድ ያዘጋጃሉ። ከጉድጓዱ የወጣውን አፈር በአንድ ጐን፣ ድንጋዩን በሌላ ጐን በሥርዓት ያስቀምጣሉ። በመጨረሻ አፈሩን፣ ድንጋዩንና ጉድጓዱን በቅጠል በመሸፈን ለቀብር አመች በሆነ መንገድ ካዘጋጁ በኋላ ወደ ሟች ቤት ይመለሳሉ።

መልዕክት ተልኮባቸው ወደ ሟች ቤት የመጡ ካህናት ደግሞ ወደ ቤት በመግባት አስከሬኑን ከብበው ለፍታት ይቆማሉ። ለፍታት ሲቆሙ ጧፍ በርክት ብሎ እንዲበራ፣ ማጠንቱ ላይ ዕጣን በብዛት ተጨምሮ እንዲጨስ፣ ውሃ በብርሌና በትልቅ ዕቃ ተሞልቶ እንዲቀርብ በማድረግ ነው።

ካህናት በዚህ ሁኔታ ለፍታት ሲቆሙ አስከሬኑ ከመካከል ሆኖ እነሱ ደግሞ ዙሪያውን ከብበው ነው። ለፍታት ሲቆሙ አንድ ዲያቆን ከሟቹ የነፍስ አባት ወይም ሥርዓቱን ከሚመሩት ካህን ፊት ለፊት የሚነበበውን መፅሐፍ ከደረቱ አስጠግቶ ይይዛል። የሟቹ የነፍስ አባት ወይም ሥርዓቱን እንዲመሩ ተለምነው የመጡት ካህን የሟችን የመፅሐፍ ስም ጮክ ብለው እየጠሩ ሲያነቡ፣ ዙሪያውን ከበው የቆሙት ካህናትና ዲያቆናት ደግሞ እየተቀባበሉ ይቀድሳሉ። በምሽት ካህናት በዚህ ሁኔታ ለፍታት ሲቆሙ፣ ለቀስተኛው ደግሞ ከቤት ውጭ፣ ደጃፍ ላይ ተሠባስቦ ያለቅሳል። በዚህ ለቅሶ የሚታደሙት ጐረቤትና የሟች ቤተሠቦች ብቻ ናቸው። ለቅሶው ሙሾ የማይወርድበት፣ የመለቀሻ አልባሳት የማይወጡበት፣ ድብልቅልቁ የወጣ፣ ያዙኝ ልቀቁኝ የበዛበት ነው።

ሟቹ የሞተበት ሰአት ከቀትር በኋላ ከሆነ ይኸው ለቅሶ በግምት እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት የሚቀጥል ነው። ከዚያ የለቅሶው አስተናባሪዎች ለቀስተኛውን በሙሉ ከማልቀስ

እንዲቆጠብ፣ "በሉ በቃችሁ፤ ዝም በሉ፤ ነገ ሙሉ ቀን ልታለቅሡ አይደለም?" ብለው ይናገራሉ። ንግግራቸውን አልሠማ ወይም አልቀበል ብሎ የሚያለቅስ ቢኖር፣ "ወዲያ ዝም በል፣ ምን ይነፋረቃል!" ብለው ይቆጡታል (ይገስጹታል)።

በዚህ ጊዜ ሁሉም ለቀስተኛ ለቅሶውን ቀስ በቀስ ያቆማል። ከዚያ ሁሉም ወደሟች ቤት ይገባል። ከሟች ቤትና ከጐረቤት የተውጣጣ እንጀራና ጠላ ቀርቦ ይበላል፤ ይጠጣል። ከዚህ በኋላ ንጋት ድረስ ለቅሶ አይኖርም። ዘግይተው የሚደርሱ የሟች የቅርብ ዘመዶች ሲመጡ ብቻ ቤተሠብ ተላቅሶ ከተቀበላቸው በኋላ፣ ቶሎ ለቅሶ አቁመው እንዲቀመጡ ይደረጋል።

በዚህ ጊዜ አስተናባሪዎች ቤተሠቦችን እየጠየቁ፣ ለቀብር ሥነ ሥርዓቱ የሚሆኑ ያልተሟሉ ነገሮችን እንዲያሟሉ ያደርጋሉ። ንጋት ላይ ተነስተው በመኪዝ ትንሽ ራቅ ብለው ለሚገኙ የሟች ወዳጅ ዘመዶች መርዶ የሚነግሩ ወጣቶችንም ያዝዛሉ። የተወሠነው መንደርተኛ ደግሞ ወደየቤቱ ተመልሶ የየግል ንብረቱን በንቃት እንዲጠብቅ ያደርጋሉ። ይህ የሚደረገው አጋጣሚውን ተጠቅሞ የቅርብ ጠላት ስርቆት እንዳይፈጽም ሲባል ነው። አስተናባሪዎች ይህንኑ ካደረጉ በኋላ፣ የሟች የህይወት ታሪክ እንዲፃፍ ያደርጋሉ። በዚህ ጊዜ የሟች ሚስት፣ ልጆች፣ በእድሜ ጠና ያሉ የአካባቢው ሽማግሌዎች (አስተናባሪዎችም ጭምር)፣ በጋራ በመሆን ሟች በህይወት ዘመኑ የሰራቸውን ድንቅ ስራዎች የሚያስታውሱትን እየነገሩ የህይወት ታሪኩ ይፃፋል። የሚጽፈው ሰው መፃፍ የሚችል ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው ሊሆን ይችላል፤ በኋላ የሚያነበውም ይኸው ጽሑፉን የፃፈው ሰው ነው። በዚህ ጊዜ እንዲፃፍ የሚደረገው ሲነጋ ሁሉም በለቅሶው ስለሚታደምና ለመፃፍ በቂ ጊዜ ስለማይኖር እንደሆነ እማሆይ ጥሩ ዓይነት ሺበሺ የተባሉ አዛውንት አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም)።

የህይወት ታሪኩ ተጽፎ እንደተጠናቀቀ አንዴ ይነበብና ሁሉም ከተስማሙበት፣ "በል እንግዲህ ነገ እንዳትንተባተብ፣ ጥሩ አድርገህ አጥናው!" ብለው ለፃፈው ሰው ሀላፊነቱን ይሠጡታል። ከዚህ በኋላ በማንኛውም ማህበራዊ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ወሬ ይቀጥላል። ሳቅና ጨዋታው ይደራል። ይህ የሚሆነው ሃዘንተኞችን ሃዘናቸውን ለማረሳሳት ሲባል ነው። ቀጥሎ በግምት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ገደማ ቤት ውስጥ ወለሉና መደቡ ሳር ይጐዘጐዝበታል፤ ከላዩ ላይም ጀንዲ፣ ጀንያ፣ ሰሌን፣ ተቀጣጥሎ ይነጠፍበትና ለቀስተኛው ሁሉ እንዲተኛ ይደረጋል።

የካህናት ተግባር ግን አይቋረጥም። በሚች የነፍስ አባት ወይም ተለምነው በመጡት ካህን መሪነት፣ የሚች የመጽሐፍ ስም እየተጠቀሠ ቅዳሴው (ካህናት ሠዓታት ይሉታል) ይቀጥላል።

### 4.2.2 በንጋት የሚካሄዱ ሥነ ሥርዓቶች

ንጋት በግምት አስራ ሁለት ሰዓት ገደማ ሲሆን የሚች ቤተሠቦች ተነስተው መላቀስ ይጀምራሉ። ከሚቹ ቤት ያደረው ለቀስተኛም እየተጣደፈ ተነስቶ፣ ወደየቤቱ በመሄድ ልብሱን ለውጦ ይመለሳል። ከየቤቱ ያደረው መንደርተኛም ቀስ በቀስ እየመጣ በመቀላቀል በሚች ቤት ደጃፍ ለረጅም ጊዜ ይለቀሳል። ይህ ለቅሶ ከምሽቱ ለቅሶ የተለዩ ነገሮች የሚታዩበት ነው። ይኸውም በንጋቱ ለቅሶ ለመለቀሻ የሚሆኑ ቁሳቁሶች በብዛት ይወጣሉ፤ የለቀስተኛው ቁጥር እየጨመረ እስኪሄድ ሙሾ እየወረደ ሲለቀስ ይቆይና የለቀስተኛው ቁጥር ሲጨምር ሙሾው አቁሞ ፉከራ ይጀመራል። የሚች ቤተሠቦችና የሌላው ለቀስተኛ አለባበስም ከምሽቱ የተለየ ይሆናል። በምሽቱ ለቅሶ ሁሉም በድንጋጤ ከየቤቱ እየወጣ ስለሚመጣ ከነዘወትራዊ አለባበሱ ይታያል። በንጋት ለቅሶው (በጥቅሉ በቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት) ግን የሚች ቤተሠቦችና ሌሎችም ሴቶች ፀጉራቸውን በጥቁር ሻሽ ይሸፍናሉ። የእጅ፣ የእግር፣ የጆሮ፣ ጌጣቸውን ያወልቃሉ። ነጠላቸውን ዘቅዝቀው ይለብሣሉ። የሚች ሚስት የሚችን ሱሪ ዘቅዝቃ ትደርባለች። ኮቱን ደግሞ የሚች ሴት ልጆች ወይም እህቶች ከቀሚሳቸው በላይ ይደርባሉ። ሴት የሚች ቤተሰቦች ጥቁር የነበረ የአንገት ማተባቸውን ትተው፣ ነጭ የፈትል ክር ያስራሉ። ሲያለቅሱ (ከሚች ቤተሰቦች በስተቀር) ወንዶችም ሴቶችም አፋቸውን በነጠላ ወይም በጋቢ ጫፍ ሸፍነው ነው። በወንድ የሚች ቤተሠቦችም ይሁን በሌሎች ወንዶች ግን አፋቸውን በጋቢ ከመሸፈናቸው በስተቀር በአለባበሳቸው ላይ የሚታይ ለውጥ የለም። ሴቶች እንዲህ የሚለብሡት ለሚች ያላቸውን ቅርበት ለመግለጥ፣ ፍጹም ያዘኑና ምቾች ከሚሠጧቸው ጉዳዮች ሁሉ የራቁ መሆናቸውን ለመግለጥ ብለው እንደሆነ፣ አቶ ደርበው ፈረደና አቶ ተሠራ አምባው ገልጸዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5 እና 7/2002 ዓ.ም)። በዚህ የንጋት ለቅሶ ወቅት አስተናባሪዎች ለቅሶው ሥርዓት እንዲይዝ በሚከተለው አኳኋን ያደራጁታል። በመጀመሪያ የሚች ቤተሠቦች መሃል ላይ፣ ሌላው ለቀስተኛ ደግሞ እነሱን ተከትሎ ክብ እንዲሠራና ቆሞ እንዲያለቅስ ያደርጉታል። ቀጥሎ ሙሾ አውራጅ (ብዙ ጊዜ ወንድ ነው) መሃል ይገባል። ከዚያ ድምጹን ከፍ አድርጐ፣ "አይ እኔን፣ አይ እ...ኔ...ን ይብላኝ" በማለት ሙሾ መደርደር

ይጀምራል፡፡ በዚህ ጊዜ ለቀስተኛው በሙሉ ትኩረቱ ወደ ሙሾ አውራጁ ይሆናል፡፡ ድብልቅልቁ ወጥቶ የቆየው ለቅሶም ሥርዓት ይይዛል፡፡ ሳግ፣ የተቆራረጠ ድምጽ የሚያሠማና የሚያለቅስ ቢኖር፣ "እስኪ ዝም በሉ በስርዓት እናልቅስበት፤ የአልቃሹን ፍሬም እንስማው" የሚል ተግሳጽ ከለቅሶው አስተናባሪዎች ወይም አጠገብ ቆሞ ከሚያለቅስ ሌላ ሰው ይደርስበታል፡፡ ቤት ውስጥ ሆነው ካህናት ከሚያስሙት ቅዳሴና አንዳንድ ለቀስተኛ ብዙ ከማልቀሱ የተነሳ አላስችል ብሎት ከሚያወጣው የታፈነና የተቆራረጠ ሳግ በስተቀር በዚህ ጊዜ የሚሰማ ምንም ነገር የለም፡፡ ሁሉም ፀጥ ይላል፡፡ ሙሾ አውራጁም መሃል ገብቶ የሟቹን ፎቶግራፍ ወይም ዋንጫ ከፍ አድርጐ በመያዝ፣ ከወዲያ ወዲህ በመንጐራደድ ሙሾውን እንዲህ እያለ መደርደሩን ይቀጥላል፡፡

ሙሾ አውራጅ - አይ እኔን፣ አይዋ እንትና

ተቀባይ (ለቀስተኛው) - እ...ህ...ህ...!

ሙሾ አውራጅ - አይ እኔን... አባት የሌላችሁ እንሂድ ምናኔ (2 ጊዜ)

ተቀባይ (ለቀስተኛው) - እ...ህ...ህ...!

ሙሾ አውራጅ - አባት የሚሠራ ብናገኝ ሸማኔ፡፡

በዚህ ጊዜ ሙሾ አውራጁ የሁለተኛውን ስንኝ የመጨረሻ ሀረግ ከመጥራቱ ጋር ተደባልቆ ለቀስተኛው የስንኙን ሀረግ አብሮ በማለት ይጨርሰውና ለቅሶው፣ ሁካታው፣ ጩኸቱ እንደ ድብልቅልቅ ይላል፡፡ ይህ ሙሾ ተደርድሮ እንዳበቃና ሙሾውን ተከትሎ ሁሉም ለቀስተኛ መላቀስ ሲጀምር የመጣው አዲስ ለቀስተኛ ወደ መሃል ፈጥኖ በመግባት፣ አፉን በጋቢ ወይም በነጠላ እየሸፈነ የሃዘንተኞችን ግራ ትከሻ፣ በቀኝ እጁ ይነካል፡፡ ሃዘንተኞችም በቀኝ እጃቸው የለቅሶ ደራሹን ግራ ትከሻ ይነካሉ፡፡ ሌላው የሙሾ ድርደራ እስኪጀምር ድረስ ከተለቀሠ በኋላ፣ ሙሾው እንደገና ሲጀምር ወደ መሀል የገባው ለቅሶ ደራሽ ወዲያውኑ ወደ ዳር ይወጣል፡፡

ሙሾ አውራጁ የሟችን ፎቶግራፍ ወይም ዋንጫ ከፍ አድርጐ በመያዝ ሙሾውን የሚያወርድበት ምክንያት የሟቹ ምስልና ልግስና በለቀስተኛው አዕምሮ እየተከሠተ፣ ከሚወርደው ሙሾ ጋር እየተባበረ የለቀስተኛውን ሆድ እንዲያባባውና አምርሮ እንዲያለቅስ ተብሎ እንደሆነ ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ እና አቶ ተሠራ አምባው አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5 እና 7/2002 ዓ.ም)፡፡

የሟች ቤተሠቦች መሃል ላይ እንዲሆኑ የሚደረጉት፣ የሟች ሚስት ሱሪውን አንገቷ ላይ ዘቅዝቃ የምትደርበው፣ ሴት ልጆቹ ወይም እህቶቹ ሌሎች የሟች አልባሳትን ለብሠው የሚያለቅሱት፣ ከሩቅ የሚመጣና ቤተሠቦችን በውል ለይቶ የማያውቅ ወዳጅ ዘመድ በቀላሉ እንዲለይና ለቅሶ መድረስ እንዲችል ተብሎ የሚደረግ እንደሆነ አቶ ደርበው ፈረደ፣ ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ እና አቶ ተሠራ አምባው የተባሉ መረጃ አቀባዮች አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5 እና 7/2002 ዓ.ም)፡፡

አፍ በነጠላ ወይም በጋቢ የሚሸፈነው ደግሞ፣ "አንዳንዱ ሲያለቅስ ይገርምሃል! አንዳንዱ የሚስቅ ይመስላል፡፡ ደሞ ሌላው ምራቁን፣ ንፍጡን ይለቀዋል፡፡ እሂ እንዳይሆን ነው ሰው ሁላ በነጠላ ሚሸፍን አፋን" በማለት የገለጹት አቶ ሞላ እንየው የተባሉ መረጃ አቀባይ ሲሆኑ (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 7/2002 ዓ.ም) ፣ አቶ ብርሃን አዱኛ የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ

> ይገርምሃል አፍ አለመሸፈን ብዙ ጉድ ነው ያለው፡፡ አንድ ____ የሚባል ሰው [ስሙን ጠቅሰው] አንድ ግዜ በአንድ ሰው ቀብር ላይ ተገኘ፡፡ ለቅሶው ከአንድ ትልቅ ዋርካ እግር [ሥር ማለታቸው ነው] እየተለቀሠ፣ እንዲያው ሁሉ እየጮኸ እያለቀሠ ሳለ ዋርካው ላይ የተቀመጠ አሞራ ኩሱን ለቆ ቢተወው፣ ካንዱ መላጣ ሰውዬ ራስ ላይ አርፎ እንዲያው የሰውዬው ራስ በአጓት የተጫወተ ጨቅላ መሠለ፡፡ በዚህ ጊዜ ይሂ ሰውዬ ይህን ሲያይ ከት ብሎ ሳቀበት፡፡ ሌላው ሰውም "ምን ነካው?" እያለ ዙሮ ሲያይ፣ ሁሉም ማፌር ጀመረ፡፡ የሟች ልጅም ብረቱን አንስቶ ያን የሳቀውን ሰውዬ ታልገደልኩ ብሎ፣ በኋላ በስንት አማላጅ ታረቁ፡፡ ይህ እንግዲህ አፋን ሳይሸፍን ቀርቶ እንጂ ቢሸፍን ኑሮ ለቅሶ ይመስልና ሰውዬው አይለይም ነበር

በማለት የገጠማቸውን ሁሉ በዝርዝር አውግተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)፡፡

ብዙ መረጃ አቀባዮች ለቅሶ ደራሽ የሃዘንተኞችን ትከሻ የሚነካው ለቅሶ ደርሻለሁ፣ የሃዘናችሁ ተካፋይ ሆኛለሁ ብሎ ለሃዘንተኞች ለመታየት (ፊት ለማስመታት) ነው ብለው ሃሳባቸውን ሲሰጡ፣ ለምን የግራ ትከሻ ሆነ? ለሚለው ጥያቄ ግን የሰጡት ምላሽ "ያው ልማድ ስለሆነ ነው፤ የአባት ነው" የሚል ነው (ለምሳሌ፣ አቶ ብርቁ ሚካኤል፣ አቶ ብርሃን አዱኛ፣ ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3 እና 5/2002 ዓ.ም)፡፡ ሙሾ እየወረደ፣ ለቅሶው በዚህ መልክ የሚካሄደው በቤት ውስጥ የግንዘት ሥነ ሥርዓት እስኪጠናቀቅና ከሩቅ የሚመጣው ለቀስተኛ እንዲሁም ፎካሪዎች እስኪደርሱ ብቻ ነው፡፡

#### 4.2.2.1 ግንዘት

ግንዘት፣ አስከሬንን ለሥርዓተ ቀብር በሚያመች መንገድ የማዘጋጀት ሂደት ነው፡፡ ሥነ ሥርዓቱ የሚፈፀመው ረፋድ ላይ ነው፡፡ በግምት ሁለት ሠዓት ተኩል ገደማ ከአስተናባሪዎች መካከል የመገነዝ ችሎታ ያላቸው ተመርጠው ወደ ቤት ይገቡና ሥነ ሥርዓቱን ያከናውናሉ፡፡ አፈፃፀሙም በመጀመሪያ ገናዥቹ ስድስት ክንድ (ሦስት ሜትር) የሚሆን ከጥጥ ፈትል የተሠራና ንጹህ የመገነዣ ጨርቅ (ከፈን ይሉታል)፣ ምላጭ፣ መርፌ፣ ነጭ የፈትል ክር (ዘሃ ክር ይሉታል)፣ ውሀ፣ ለስላሳና ርጥብ ቅጠል ይዘው ወደ አስከሬኑ ይጠጋሉ፡፡ ቀጥሎ የተለያየ ቦታ የተጫነውን ድንጋይ፣ የተሸፈነበትን ልብስ ያነሱና በደረቱ ተደፍቶ የተኛውን አስከሬን ገልብጠው በጀርባው ቀጥ ብሎ እንዲተኛ ያደርጉታል፡፡ ከዚያ ካህናት ጸሎት ሲያደርጉበት ባደረ የተባረከ ውሃ (ካህናት ፀበል ወይም ማየ ህይወት ይሉታል) አስከሬኑን ያጥቡታል፡፡ ሲያጥቡ አስከሬኑን በቅጠል እንጂ በእጃቸው አይነኩትም፡፡ ቀጥሎም የአስከሬኑ የተለያዩ ክፍሎች እንዳይጐብጡ ታስሮበት የነበረ ገመድ ይፈታና የሁለት እግሩ አውራጣቶች፣ ባቱ፣ ታፋው፣ ሽንጡ ወይም ሆዱ፣ ደረቱ፣ አንገቱና ራሡ ላይ በነጭ ፈትል ክር ይታሠራል፡፡ ከዚያ በመገነዣ ጨርቁ ይሸፈንና በመርፌ ይሠፋል፡፡ ከመገነዣ ጨርቁ በላይ አስከሬኑ በሰሌን፣ በጀንዲ፣ የሚጠቀለልበት ጊዜም አለ፡፡ አስከሬኑን እንዲህ ከገነዙ በኋላ በአልጋ ላይ ያጋድሙታል፡፡ ከዚያ ዥጉርጉር የሆነ ልብስ (ግምጃ ይሉታል) ያለብሱታል፡፡ ቀጥሎ ሁለት ጠንካራና ቀጥ ያሉ እንጨቶች ያመጡና ለሠው ትከሻ ሸክም አመቺ በሆነ መንገድ በሁለቱ የአልጋው ግራና ቀኝ አጠናዎች ስር ያስራሉ፡፡

ገናዦች ብዙ ጊዜ ወንዶች ናቸው፡፡ ይህ ለምን እንደሆነ የተጠየቁ መረጃ አቀባዮች፣ ሴቶች እንዲህ ዓይነቱ ነገር ስለሚያስፈራቸውና ስለሚያስደነግጣቸው እንደሆነና አንዳንድ ጠንካራ ሴቶች ግን እንደሚያደርጉት አስረድተዋል (አቶ ብርሃን አዱኛ እና አቶ ተሠራ አምባው ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5 እና 7/2002 ዓ.ም)፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ ፣ "ሁሉ ሴት ይፈራል፤ እኔ ግን የባለቤቴን ሁሉ እኔ ራሴ ነው የገነዝኩት፡፡ ተዛ ወዲህ የወንድሜ ልጆች ሲሞቱ፣ ጐረቤትም ሲሞት እኔ ነኝ የገነዝኩ፤ የባለቤቴን ጨምሮ እስታሁን ዘጠኝ ሬሳ ገንዥለሁ" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)፡፡

በግንዘት ወቅት አስከሬን በፀበል የሚታጠበው፣ በንጹህ ጨርቅ የሚሸፈነውና ሰባት ቦታ በፈትል ክር (በማግ) የሚታሰረው፣ ሃይማኖታቸው ስለሚያዝ እንደሆነም የማህበረሰቡ አባላት ያስረዳሉ። እማሆይ ጥሩ ዓይነት ሺበሺ ይህንኑ ጉዳይ ሲያስረዱ፣ "ሬሳን መገነዝ የአባት ነው፤ ቀድሞ ተአባቶቻችን የተቀበልነው ነው። ቄሶችም አርጉ ይላሉ እንጂ ዝም ብሎ ቢቀበር ዝም ይላሉን?" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም)። ይህ ጉዳይ ሃይማኖታዊ መሆኑን የወረዳው ቤተ ክህነት ጽህፈት ቤት ፀሐፊ የሆኑት መሪጌታ አራጌ ባዩ የተባሉ ሰው፣ "አስከሬን በጸበል የሚታጠበው ሟች ከምድራዊ ህይወት ወደ ሰማያዊ ህይወት ሲሸጋገር ታጥቦና ከሐጢያቱ ነጥቶ እንዲሄድ ሲባል የሚደረግ ነው፤ በነጭ የፈትል ጨርቅ መገነዙም ያው የማንፃት ስራ ነው" በማለት አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3/2002 ዓ.ም)።

ዓለሙ ጉዶ የባሉ ቄስም፤

> ከጨርቁ በላይ በሰሌን ምንጣፍና በቆዳም ይጠቀለላል። ሰሌኑ ሃይማኖታዊ ነው። እሱም እየሱስ ክርስቶስ በሆሳዕና ጊዜ ሲመጣ ህፃናት የዘንባባ ቅጠል ይዘው፣ አፈር እንዳይነካው እየጠረጉ ስለተቀበሉት ያንን ለማስታወስ ነው። አስከሬን በሰሌን ምንጣፍ የሚጠቀለለው ሟች የሠራውን ሐጢያት ያነፃል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ቆዳው ግን ሟቹ ሀብታም መሆኑንና ጥሩ ኗሪ ነበር ለማለት ካልሆነ በቀር ቤተ ክርስቲያን ያዘዘችው አይደለም

ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 6/2002 ዓ.ም)።

የአካባቢው ማህበረሰብ አስከሬን በንጹህና በነጭ ጨርቅ የሚሸፈንበትንና ሰባት ቦታ የሚታሠርበትን ሁኔታ አስመልክቶ በደፈናው ከቀደመው ትውልድ እንደወረሰውና ሃይማኖቱ ስለሚያዝ እንደሚደረግ ቢገልጽም፣ ይህንኑ አስመልክተው ካህናት የሚሠጡት ሀሳብ ደግሞ ፍጹም የተለያየና ርስበርሱ የሚጣረስ ነው።

ይኸውም አስከሬን በነጭና በንጹህ ጨርቅ ተሸፍኖ፣ ሰባት ቦታ የሚገነዘው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሞት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በንጹህ ሃር ሸፍነው፣ ሰባት ቦታ ላይ ስለገነዙት ያንን ለማሠብ የሚደረግ መሆኑንና ይህ ሥርዓት ማንኛውም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ሰው ሲሞት እንደሚደረግ ቄስ ዓለሙ ጉዶና መሪጌታ አራጌ ባዩ የተባሉ መረጃ አቀባዮች ሲያስረዱ (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3 እና 6/2002 ዓ.ም)፤ ሊቀ ካህናት መልአከ ገነት አበበ የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ ስለዚህ ጉዳይ የሰጡት ሀሳብ ከዚህ ፍጹም የተለየ ነው። ይህም፤

> የሰው ልጅ አፈጣጠሩ ከሶስቱ ባህርያተ ነፍስ ማለትም ህያዊት፣ ለባዊት፣ ነባቢትና ከአራቱ ባህርያተ ስጋ ከሚባሉት መሬት፣ ውሀ፣ እሳት፣ ነፋስ ነው፡፡* በነዚህ ሰባት ባህርያት ተደፋፍሮ፣ በሳምንቱ ሰባት ቀናት የሠራቸውን ሐጢያቶች እግዚአብሔር ይቅር በለው ለማለት ነው ይኸ የግንዘት ሰባት ቦታ መታሠር (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም)

የሚል ነው፡፡

የግንዘት ሥነ ሥርዓቱ በቤት ውስጥ በዚህ አኳኋን እንደተጠናቀቀ አስከሬኑን ሁለት ሰዎች ይሸከሙና በካህናት መሪነት ወደ ደጅ ይወጣል፡፡ የሟች ደጃፍ ላይ ቀስ አድርገው ያሳርፉትና ጃንጥላቸውን በመዘርጋት ካህናት አስከሬኑን ይከባሉ፡፡ የመጀመሪያውን የጉዞ ፍታትም በዚሁ ጊዜ ያደርጋሉ፡፡ የካህናቱ የጉዞ ፍታት አፈፃፀም ማታ በቅዳሴ ከሚያከናውኑት ብዙ የተለየ አይደለም፡፡ ይኸውም ልክ እንደ ማታው ቅዳሴ አንድ ዲያቆን ከሟቹ የነፍስ አባት ወይም ሥርዓቱን ከሚመሩት ካህን ፊት ለፊት የሚነበበውን መፅሐፍ ከደረቱ አስጠግቶ ይይዛል፡፡ ካህኑም መፅሐፉን ያነባሉ፤ ሌሎችም ካህናት እየተቀባበሉ ይቀድሳሉ፡፡ ከማታው ቅዳሴ ለየት የሚያደርገው በዚህ ጊዜ ከበሮ የሚመታ መሆኑ ነው፡፡ አስከሬን ለጉዞ ፍታት ባረፈበት ጊዜና ቦታ ሁሉ የጉዞ ፍታት ስርዓቱ እንዲህ ባለ አኳኋን ይቀጥላል፡፡

አስከሬኑ ወደ ደጅ እንደወጣ በሙሾ አውራጆች፣ በፎካሪዎችና በአስተናባሪዎች ትብብር ስርዓት ይዞ የነበረው ለቅሶ ድብልቅልቁ ይወጣል፡፡ ብዙ ሰው ይጮሀል፤ አምርሮ ያለቅሳል፡፡ የሟች ወንድ ልጅ፣ ወንድም፣ ወይም የቅርብ ዘመድ የሆነ ሁሉ፣ ወደ ሰማይ ብዙ ጥይት ይተኩሳል፡፡ ሴት የሟች ቤተሠቦች ደግሞ ጨኸታቸውን ይለቁታል፤ ይወድቃሉ፤ ይነሳሉ፡፡ ስንብትን የሚገልፁ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞችም ከተለያዩ አካባቢዎች በመጡ ፎካሪዎች ይደረደራሉ፡፡

> ጥይቱና በምሬት የሚለቀሠው ከሩቅ የሚመጣ ቀባሪ ሬሳው ከቤት መውጣቱን ማሳወቂያ ነው፡፡ ለሟቹም የሚደረግ የመጨረሻ ስንብት ነው፡፡ ቤተሰቡም የተከሠ እንደሆነ "አያችሁ በክላሽ፣ በማስራራት [ኤም 14 ለማለት] ብረት አንደገደገው" ተብሎ በሌላው ሰው ስሙ ይጠራል

* "ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ ህያውነት" ለመተንፈስ፣ ለማሰብና ለመናገር የሚረዱ የሰው ልጅ ባህርያት ናቸው፡፡ በተፈጥሮው ተናዳጅ በመሆኑ የሰው ልጅ በህፃንነት እድሜው የሚጨበጥ ባህርይ ስለሌለው የነፋስን፣ ሁሉንም ቻይ፣ አስተዋይ ሲሆን የመሬትን፣ ባህርያት የእሳትን፣ የሚናደድበት ጊዜ ሲያልፍ የውሀን፣ ይይዛል፡፡

በማለት ጥይት የሚተኮሠው አንድም ለዝና፣ አንድም ሟችን ለመሠናበትና አስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ወደ መቃብር ቦታ ጉዞ መጀመሩን መግለጫ እንደሆነ ያስረዱ አቶ አቶ ሞላ መኮንን የተባሉ መረጃ አቀባይ ናቸው (ኢንተርቪው፣ መጋቢት፣ 20/2002 ዓ.ም)።

### 4.2.3 በአስከሬን ጉዞ ወቅት የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች

ካህናት በሟቹ ደጃፍ ቆመው የመጀመሪያውን የጉዞ ፍታት አድርገው ከጨረሱና አስተናባሪዎች አብዛኛው ቀባሪ መሠባሠቡን ካረጋገጡ በኋላ፣ ሁለት ሰዎች አስከሬኑን እንዲሸከሙ በማድረግ ወደሚቀበርበት ቤተ ክርስቲያን ጉዞ እንዲጀመር ያደርጋሉ። አስከሬን እንዲሸከሙ የሚመረጡት ሰዎች፣ ወጣትና ጠንከር ያሉ ወንዶች ሆነው ለሟቹ የቀረበ ዝምድና የሌላቸው ናቸው።

የአስከሬኑን ጉዞ መጀመር ተከትሎ ጨኸቱና ዋይታው ከበፊቱ የጨመረ ይሆናል። የጥይት እሩምታ ይወርዳል፤ ጥሩንባ ይነፋል። ጥሩንባው የሚነፋው ትንፋሽን ወደፊት በመግፋት ብቻ (ቱቱቱ በማድረግ) ነው። ጥሩንባ የመንፋት ሂደት የሚከናወነው አስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጉዞ ሲጀምር፣ መንገድ ላይ ለፍታት አርፎ ሲነሳ፣ አዳዲስ ለቀስተኛ መጥቶ ሊቀላቀል ሲል፣ አስከሬኑ ወደ መካነ መቃብር ወርዶ ሥርዓተ ቀብሩ ሲጠናቀቅ፣ ብቻ እንጂ በተገኘው አጋጣሚና በተፈለገው የአነፋፍ ሥልት ሁሉ አይነፋም። ይህ የሚደረግበት ምክንያት ለቀስተኛው የጥሩንባውን ድምጽ እየተከተለ በየሂደቶቹ የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶችን በጋራ እንዲያከናውን ለማድረግ ነው።

የቀብር ጥሩንባ ትንፋሽን ወደፊት በመግፋት ብቻ የሚነፋበት ምክንያት ይህንኑ ድምጽ ከሩቅ የሚሠማ ሰው የቀብር ሥነ ሥርዓትና ሌሎች የለቅሶ ዓይነቶች እየተካሄዱ እንደሆነ በቀላሉ እንዲረዳ፣ ትንፋሽን ወደፊትና ወደኋላ በመመላለስ ሲነፋ ደግሞ ሰርግ መኖሩን እንዲያውቅ ማድረጊያ መንገድ እንደሆነ የማህበረሰቡ አባላት አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ አቶ ይደሠት በለጠ፣ አቶ ጐዶ ጌጤ፣ መጋቢት 21/2002 ዓ.ም)።

ይህ የጥሩንባ ድምጽ ከሩቅ አገር ወደ ሟች ቤት በመጓዝ ላይ የሚገኝ ለቀስተኛ ከሟች ቤት አካባቢ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በቀላሉ በመለየት ጉዞውን ከድምጹ ሁኔታ ጋር እንዲያስተካክል ያደርጋል። ይኸውም በመቃብሩ አቅጣጫ የሚመጣው ለቀስተኛ የድምጹን ሁኔታ ቆም ብሎ በማዳመጥና በመመርመር “አይ አስከሬኑ እየመጣ ነው፤ እዚሁ እንጠብቀው” በማለት ባለበት ሆኖ እንዲጠባበቅ፣ ከመቃብሩ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣው

ለቀስተኛ ደግሞ "ኧረ ቶሎ ቶሎ እንሂድ፤ አስከሬኑ ወጥቷል እንድረስበት" በማለት ጉዞውን እንዲያፈጥን እንደሚያደርግ፣ እነ አቶ ጎዶ አስረድተዋል።

አስከሬን ጥሩንባ እየተነፋ፣ ጥይት እየተተኮሰ ወደሚቀበርበት ቦታ ሲጓዝ የሚይዘው ቅርጽ ካህናት ከፊት፣ ቀጥሎ አስከሬኑ (ራሱ ወደፊት፣ እግሩ ወደ ኋላ ተደርጐ)፣ ከአስከሬኑ ጐን ደግሞ ስንጴ ወይም ጤፍ የያዘና መሃሉ ላይ ውሃ የተሞላ ብርሌ የተቀመጠበት አገልግል በሁለት እጆቹ የያዘ ሽማግሌ (ውሃውን ፀበል፣ ስንጴውን ወይም ጤፉን ደግሞ መገበሪያ ይሉታል)፣ ከዚያ የሟች ቤተሠቦች፣ በመጨረሻም ቀባሪው ህዝብ ሆኖ ነው።

ጉዞው ይህን የመሠለ ቅርጽ የሚይዘው በሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆነ የማህበረሰቡ አባላት ይናገራሉ።

ይኸውም ካህናት ከፊት የሚሆኑት ታቦትም ይሁን አስከሬን የሚመራው በመስቀል ነው፤ መስቀልን የሚይዙት ደግሞ ካህናት ብቻ እንደሆኑ ታቦትም ይሁን አስከሬን በነሱ እንዲመራ ሃይማኖቱ ስለሚያዝ እንደሆነ፣ አስከሬኑ መሃል መደረጉ ደግሞ በማህበረሰቡ ልማድ መሠረት የሚሸኝ ነገር ምን ጊዜም መሃል ላይ ስለሚደረግና፣ የሟች ቤተሠቦች ከአስከሬኑ ቀጥሎ እንዲጓዙ የሚደረግበት ምክንያትም በቀብሩ ላይ የማያውቃቸው ታዳሚ ቢኖር በቀላሉ እንዲለያቸውና ለቅሶ እንዲደርስ ለማድረግ እንዲሁም ቤተሠቦችም ከሃዘን ብዛት ደክሚቸው ቢወድቁ አስፈላጊውን ርዳታ ለመስጠት ሲባል የሚደረግ እንደሆነ ይናገራሉ (መሪጌታ አራጌ ባዩ እና አቶ ተሠራ አምባው፣ ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3 እና 7/2002 ዓ.ም)።

አስከሬን በዚህ አኳኋን ከቤት ወጥቶ ወደቤተ ክርስቲያን ጉዞ ሲጀምር የሚሠማው ዋይታና ጩኸት የሚዘልቀው አስከሬኑ በግምት ከአምስት እስከ አስር ደቂቃ ተጉዞ ለጉዞ ፍታት እስኪያርፍ ድረስ ብቻ ነው።

ከዚያ በኋላ ግን አስከሬኑ ከቤት ከተደረገለት የጉዞ ፍታት በተጨማሪ በየመንገዱ አምስት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን ሲደርስ አንድ ጊዜ በጥቅሉ ሰባት ጊዜ አርፎ ከ25 እስከ 30 ደቂቃ የሚፈጅ ፍታት እየተደረገለት፣ በነዚህ ቦታዎች ሁሉ ቀረርቶ እና ፉከራ እየተደረገለት ይዘልቃል እንጂ፤ ለቅሶ አይኖርም። አስከሬኑ ለፍታት በሚያርፍባቸው ቦታዎች ሁሉ (የሚመረጡት ቦታዎች ሜዳማና ለቀስተኛውን ማስተናገድ የሚችሉ ናቸው) አስተናባሪዎች ለቀስተኛውን በሚከተለው አኳኋን ያደራጁታል። ይህም አስከሬኑ ወደፊት ፊንጠር ብሎ

እንዲያርፍ ይደረግና ካህናት ከብበውት ለፍታት ይቆማሉ። ከአስከሬኑ ትንሽ ወደኋላ አካባቢ ደግሞ ለቀስተኛው ክብ ሰርቶ እንዲቆም ያደርጋሉ። ከዚያ ልዩ ልዩ የጦር መሳሪያዎችንና አልባሳትን እንዲሁም የጋማ እንስሳትን የያዙ ሰዎች (የሟቹ አልባሳት፣ ባንዲራ፣ ጦር፣ ዝናር፣ ጋሻ፣ ጕራዴ፣ ጠመንጃ፣ ፈረስ ወይም በቅሎ ናቸው) ክቡ መሃል እንዲገቡ ያደርጋሉ። ቀጥሎ "እንግዲህ ማነህ ጃሎ በል!" በማለት ለሚፎክር ሰው ዕድሉን ይሠጣሉ።



ካህናት ለፍታት ቆመው



አስተናባሪዎች ለቀስተኛው ክብ እንዲሰራ ሲያደርጉ

በዚህ ጊዜ ዕውቁ ፎካሪ ወደፊት በመምጣት፣ ማቅራራት የሚችል ከሆነ ራሱ በማቅራራት፣ የሚችል ካልሆነ ደግሞ ከሚያጅቡት ወንዶች መሃከል "ማነህ ጃሎ በል!" በማለት አንዱ እንዲያቅራራ ይጋብዛል። አንዱ ከመሃል "እረ መገን፣ እረ ደኑ!" በማለት ድምጹን ዘለግ አድርጎ ማቅራራት ይጀምራል። ማቅራራት የጀመረው ሰውዬ በመጀመሪያ ራሱ የሚያውቃቸውን ማናቸውንም የቀረርቶ ግጥሞች በመደርደር ይጀምራል። ቀጥሎ ፎካሪው ከሟቹ ማንነት ጋር የሚዛመዱ ሌሎች ግጥሞችን እየነገረው እንዲያቅራራ ካደረገ በኋላ ጠመንጃውን በቀኝ እጁ ይዞ፣ ወደፊት እመር ብሎ በመውጣት "አይ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ" በማለት በሚያምር ዜማና ለሁሉም ታዳሚ ሊሰማ በሚችል ድምፅ የፉከራ ግጥሙን መደርደር ይጀምራል።



ፉከራው ሲካሄድ የሚያሳይ ፎቶ

ፉከራ በቀረርቶ የሚጀመርበት ምክንያት ቀረርቶ በባህርይው ድምጽን ከፍ በማድረግ፣ ግጥሞችን በተለይም የመጀመሪያውን ስንኝ በመደጋገም የሚከናወን በመሆኑና ይህ ባህርይውም ለቀብር የተሠበሠበው ለቀስተኛ ድምጹን እየሠማ ትኩረቱ ወደፎካሪው እንዲሆን ስለሚረዳ እንደሆነ በወረዳው የሚገኙ ዕውቅ ፎካሪዎች አስረድተዋል (አቶ ጌታ ጣፈጠ፤ አቶ አወቀ ታከለና አቶ ሙሌ አውላቸው፣ ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም)።

ከላይ በተገለጸው መንገድ በማቅራራት መፎከር የጀመረው ፎካሪ፣

አዬ ጉድዬ አዬ ጉድዬ
ያ ጀግና ዘማች ከዓለም ተለየ
ማን ለማን ፈርቶ ማን ለማን አንሶ
ጉድብ አስነቃይ ደገላ ጥሶ
ሳለ ለኩራት ሲሞት ለለቅሶ
ይፊክርለት በዓይነት በዓይነቱ
በላም በበሬው በርስት በጉልቱ
ለፍከራማ ለውስዋሶው
መቼ ያሳፍራል ሱሪ ያለው ሰው
ሱሪ ቢኗችሁ ጨርቅ ነው ወይ
የታጠቀ ነው ክልቡ ላይ

ደራርቦ ጣይ ነው ሰው በሰው ላይ
ዘማች ጐንደር
ለዚህ ቀን ብሎ ለማስፈከር
አርብ ተጉዞ ገዳይ ቅዳሜ
ወትሮም ጀግና ሰው የለው ዕድሜ
ኧረ አርማጭሆ ይምጣ ጠገዴ
ሠዎች ቀጫጭን ልባቸው ዳንዴ
አጭር ቁመቱ ሰፊ ደረቱ
አባርሮ ደፋው በቁልቁለቱ
ውረድ በግራ ውጣ በስተቀኝ
ገድሎ መፈከር እንዴት ናፈቀኝ
ለዝና ብሎ ለመሞናደል
እየገደለ ሰደደው ገደል
መሬት እንደሰው የሳቀለት
ሰው እንደ ፍየል የሮጠለት
ይኸ ነበረ የወንድ አባት
ሲሄድ ነበረ ጋራ ለጋራ
የተማከረው ክላሹ ጋራ
ሁል ጊዜ ስጋ ዱለት ሚበላ
አውራ ሚዳቋ አውራ ድኩላ
የሰውዬ ልጅ የባለጸጋ
ቤቱ አይጐድልበት ክረምት ተበጋ
ላሙ ነጫጭ ነው ጊደሩ እምብርታም
የሰውዬ ልጅ ጥንት ነው ሃብታም
ጐሹን በቀኝ ዘውዴን በግራ
ሰርዶ አራጋፊ እንደጨንራ

ወዘተ. በማለት በግጥሙ የሚቹን ጀግነነት፣ ለጋስነት፣ የዘር የበላይነት፣ ሙያ፣ መልክ፣ ሃብት፣ ጸባይ፣ እና ሌሎችንም ባህርያቱን የሚያወድሱ ግጥሞችን ይደረድራል፡፡ ታዳሚዎች ደግሞ በፎካሪው የድምጽ ቅላጼ፣ የግጥም አደራደር፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ወዘተ. ምክንያት

በስሜት ሲቅበጠበጡ ይቆዩና ቤት የሚመቱ ስንኞችን ደርድሮ እንደጨረሰ፣ አንዳንዴም ፍካሪው "ሲል ነበር አንተ!" በማለት ጮክ ብሎ እንደተናገረ ወንዶች፣ "እንዲያበል!" ሴቶች ደግሞ፣ "እልል..." ይላሉ። "እንዲያ በል!" ወይም "እልል..." ከማለት በተጨማሪ ወኔው የመጣበት ሰው ሁሉ ወደ ሰማይ የቻለውን ያህል ጥይት ይተኩሳል። አንዳንዱ ደግሞ ሮጦ ወደ ፍካሪው በመሄድ አቅሙ የፈቀደውን ያህል ብር ሸልሞ ወደ መጣበት ይመለሳል። ፉከራ በፍካሪውና በታዳሚው ላይ የሚፈጥረውን ስሜት አስመልክተው ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ የተባሉ መረጃ አቀባይ፣ "በፍከራ ግዜማ ምኑ ቅጡ ተወርቶ አንተ? እንኳንስ ወንዱ ሴቱ ሁላ ያብዳል። እኔም ሲፈከር ስሰማና ሳይ እይይ... እያልኩ ተፈካሪው ኋላ እንቀለቀላለሁ። ፈካሪው ደሞ ጫንቃው [ጫንቃ ጀርባ ማለት ሲሆን በምስጠው ሞራል ይደስታል ማለታቸው ነው] ይሞቃል። ተመቀነቴ ትንሽ ታለችኝ ደሞ ሩጨ ሂጀ እሸልመዋለሁ" በማለት ፉከራውና ፍካሪው የሚፈጥርባቸውን ስሜት ሲገልጹ (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)፣ አቶ ጌታ ጣፈጠ የተባሉ በወረዳው የሚኖሩ እውቅ ፍካሪ ደግሞ፣ "ፉከራ እንኳንስ መሳሪያ የያዘውን ያልያዘውንም ያስተኩሰዋል። የለለው ሞቅ ሲለው ካለው ተቀብሎ ይለቀዋል። ታግሎ ቀምቶ የሚተኩስና የሰው ካዝና ባዶ አስቀርቶ የሚመልስም ሞልቷል" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 11/2002 ዓ.ም)።

ይሁን እንጂ በፉከራ ጊዜ ጥይት መተኮስ፣ ፍካሪውን መሸለም፣ እንዲያ በልም ሆነ እልል ወይም እይይ ማለት የሚፈቀደው፤ ፍካሪው ቤት የሚመቱ ስንኞችን ደርድሮ ሲጨርስ ብቻ ነው። ይህ የሚሆነው የፍካሪውን ግጥሞች (ግጥሞችን ፍሬ ወይም ቁም ነገር ይሏቸዋል) ታዳሚው በአግባቡ እንዲሰማቸው ሲባል ነው።

ፍካሪው በክቡ ውስጥ ሲፎክር ከግጥሙ መልዕክት ጋር የሚዛመዱ የተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ነው። ጠመንጃውን ወይም ጐራዴውን ከቀኝ ወደግራ፣ ከግራ ወደቀኝ በሀይል በማወዛወዝ፣ ወደ ላይና ወደታች በመነቅነቅ፤ መሬት ላይም ይሁን በቅሎ ወይም ፈረስ ላይ ከወዲያ ወዲህ በመንጐራደድ፤ ራሱን በሀይል በመነቅነቅ፣ ቁጭ ብድግ በማለት፣ የድምጹን አወጣጥ አንዴ ከፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ በማድረግ፣ የግጥም ድርደራውን ፍጥነት አንዴ ፈጠን ሌላ ጊዜ ቀስ በማድረግ ይፎክራል። ፍካሪውን የከበቡት ሌሎች ፍካሪዎች ደግሞ ተራ አግኝተው መፎከር እስኪችሉ ድረስ "እንዲያ በል" እያሉ፣ የማይፎክሩ ሌሎች ወንዶችና የሚች ሚስትም "አዎ!"፣ "ልክ ነው!"፣ "እሠይ!"፣ እያሉ

የምስክርነት ቃላቸውን እየሰጡ ከፍካሪው ጋር ሲንጐራደዱ፣ ከክቡ ራቅ ብሎ የተሰበሰበው ታዳሚ ደግሞ ትዕይንቱን ቆሞ ይመለከታል።

ታዳሚውም የፍካሪውን ችሎታ የሚመዝነው ፍካሪው በሚያሳያቸው ልዩ ልዩ ትርኢቶችና ከሟቹ ማንነት ጋር አዛምዶ በሚያነሳቸው ግጥሞች ይዘት ነው። ይህንን አስመልክተው አቶ ሞላ መኮንን የተባሉ መረጃ አቀባይ ያስረዱት፣ "ጥሩ ፈካሪ የሚባለው የሟቹን ሙያ በትክክል ሲያስረዳ ነው፤ ሳይጨምርበት፣ ሳይቀንስበት። ገበሬም እንደሆነ ስለግብርናው፣ ዘማችም እንደሆነ የዘመቻውን ጊዜ፣ ከነማን ጋር እንደተሰለፈ፣ የዘመተበትን አገር ሁሉ ሲያስረዳ ነው" በማለት ነው (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 20/2002 ዓ.ም)።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ለገበሬውም "ገዳይ፣ ዘራፍ" እያሉ ሲፎክሩለት ይታያል። ይህም የመጀመሪያው ፍካሪ ባገኘው አጋጣሚ የሟቹን ማንነት በተለይም የግብርና ሙያውን የሚያወድሱ ግጥሞችን ከደረደረ በኋላ፣ ትኩረቱን ወደ ሟቹ ዘማችና አዳኝ ወገኖቹ አድርጐ፣ የሟቹንም ስም ከነዚህ ሰዎች ስሞች ጋር አብሮ እያነሳ ይፎክራል። ቀጥሎ ዕድሉን አግኝቶ ወደ ክቡ ውስጥ የሚገባው ፍካሪ ደግሞ የቀዳሚውን ፍካሪ ሃሳብ በሚከተለው አኳኋን ተችቶ ይጀምራል።

> ያልገደለውን ገደለ አትበሉ
> ያልዘረፈውን ዘረፈ አትበሉ
> የሚጠድቅ ነፍስ አታስኮንኑ
> ይልቅስ በሉ የላሞች ጌታ የነድምቡሉ
> ያልገደለውን ገደለ ምነው
> ያልዘረፈውን ዘረፈ ምነው
> እኔ እምፈክር በበሬዎቹ ነው
> ገዳይ አትበለው ያልገደለውን
> ዘራፍ አትበለው ያልዘረፈውን
> ስጠው ጅራፉን የለመደውን
> ገበሬ ነበር የሰደድ እሳት
> የእባብ ልብ እንጂ የለውም አንጀት

በማለት ስለ ግብርናው መፎከሩን ይቀጥላል።

ገበሬው ገዳይ እየተባለ የሚፎከርለት፣ በሁለት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው በፉከራ ጊዜ ዘራፍ፣ ገዳይ ካልተባለ አይሞቅም የሚል አመለካከት በማህበረሰቡ ዘንድ በመኖሩ ነው። ሌላው ደግሞ በፉከራ ጊዜ የሟቹ ገድል ብቻ ሳይሆን የጓደኞቹና የወገን ዘመዶቹ ገድል ሁሉ በአጋጣሚው አብሮ የሚነሳ በመሆኑ ነው።

ፎካሪው ሲፎክር ክዋኔውን የበለጠ ግልጽ እና ምስል ከሳች ለማድረግ የሚጨምራቸው ነገሮች ልክ እርሱ በአካል በቦታው ተገኝቶ፣ የተመለከታቸውና የተከታተላቸው በማስመሰል ነው። ለምሳሌ እንደሚከተለው በማለት፤

ዘራፍ የኢትዮጵያ ጀግና
ጦር ሲጥመለመል እንደደመና
አንበሳው ወንዱ መሃሉን ገባ
መሃሉን ገብቶ አረገው ኦና
ምስጥ እንደበላው እንደብሳና
አየር በሰማይ ሲያንዣብብበት
ታንክ በመሬት ሲሮጥበት
ጉም ጉም ሲል ቦምብ እንደመብረቅ
መድፍና አዳፍኔ ሲብለቀለቅ
አለ አንዳንድ ጅል ስሙን ማያውቅ

በየፎካሪው የሚደረደሩ ግጥሞችን ስናይ ደግሞ፣ አንዴ ዕድሉን አግኝቶ መፎከር የጀመረ ዕውቅ ፎካሪ ከሟቹ ማንነት ጋር የተያያዙ፣ ብዛታቸው ከሶስት እስከ አምስት የሚደርሱ የቀረርቶ ግጥሞችንና ከሃምሳ እስከ መቶ የሚደርሱ የፉከራ ግጥሞችን ሊደረድር ይችላል። ግጥሞች፣ ከሟቹ ማንነት ጋር ለማዛመድ ከሚደረገው መጠነኛ የስም ለውጥ በስተቀር በቃል ጥናት (memorization) የሚደረደሩ ናቸው። ለምሳሌ፣ በከበደ የቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት "አንበሳው ከቤ" ሲል የገጠመውን በሌላ ጊዜና የቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ደግሞ በአዲሱ ሟች ስም ተክቶ "አንበሳው አቤ" በማለት የሚገጥማቸው ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ፎካሪው ዓውዱን ተመስርቶ እዚያው የሚገጥማቸው ናቸው። ይህ ጉዳይ ከቃል ግጥም የአደራረስ ባህርይ አኳያ ሲታይ የከዋኞች አቅም ነባሩን ግጥም በቃል በማጥናትና በመጠነኛ አዲስ ፈጠራ ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑን የሚጠቁም ነው።

በክዋኔ ወቅት ፎካሪዎች እየገቡ የሚፎክሩት እንዳሻቸውና በዘፈቀደ አይደለም፤ የራሳቸው የሆነ ሚና መለዋወጫ ዘዴን በመጠቀም እንጂ። ፎካሪዎች ሚና የሚለዋወጡበት ዘዴ አንድም በድምጽ፣ አንድም በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚገለጽ ነው።

ሚና መለዋወጫ ዘዴዎች፣ ፎካሪው ብዙ ከፎከረ በኋላ መጨረሱን ለማሳወቅ "ማነህ ግባ!፣ ጃሎ በል!" የሚሉትን ሃረጋት በመጥቀስ፣ የያዘውን የጦር መሳሪያ ለመፎከር ተራ ለሚጠብቁ ሌሎች ፎካሪዎች በመስጠት እና በምልክት ግባ ብሎ ቦታውን በመልቀቅ የሚገለጹ ናቸው። አንዳንዴም መሬትን በእግሩ በሀይል በመምታትና "ቻይ ምድር" ብሎ በመናገር ድምጹንና የሰውነት እንቅስቃሴውን በማጣመር ይገልፃል። በዚህ ጊዜ አብረውት ይንጎራደዱ ከነበሩት አጃቢዎች አንዱ ዘሎ ይገባና መፎከሩን ይቀጥላል።

ፎካሪዎች በዚህ ሁኔታ ሚና እየተለዋወጡ ፉከራውን የሚያካሂዱት አስከሬን ለፍታት በሚቆምበት ጊዜና ቦታ ብቻ ነው። ይህ ሁናቴ ግን የሟች ወዳጅ ዘመዶች ከሩቅ አገር እየመጡ ሲቀላቀሉ ይለወጣል። እነዚህ ሰዎች በየመንገዱ እየመጡ ሲቀላቀሉ ይህንን ሚና መለዋወጫ ጠብቀው አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ሲቀላቀሉ እንዲሁ በዘፈቀደ አይደለም። በመጀመሪያ ለቅሶው እየተካሄደ ካለበት ቦታ ትንሽ ራቅ ብለው ይሰባሰቡና ጥሩንባ ይነፋሉ። ቀጥሎ ወንዶች ከፊት፣ ሴቶች ከኋላ ይሆኑና ወንዶች እየተቀባበሉ ማቅራራት ይጀምራሉ። ምንም እንኳ፣ ቀድመው መሃል የገቡና በመፎከር ላይ የነበሩ ሰዎች ቢኖሩም፣ ከአስከሬኑ አጠገብ ያለው ለቀስተኛ ትኩረት እያቅራራ ወደሚመጣው አዲስ ለቀስተኛ አቅጣጫ ይዞራል። በዚህ ጊዜ ራቅ ብለው አስከሬኑን ከበው የጉዞ ፍታት የሚያደርሱ ካህናት ከሚፈጥሩት ድምፅ በስተቀር በሌላው ለቀስተኛ የሚፈጠር ምንም ድምፅ የለም። ከዚያ ከአዲሶቹ ለቀስተኞች ጋር የመጣው ፎካሪ እየፎከረ እንደተጠጋ፣ ከኋላ ያሉት የሟች ወዳጅ ዘመዶች በተከታታይ ጥይት ተኩሰውና ጥሩንባ ነፍተው ይቀላቀላሉ። ከዚያ ፉከራው ከሁለቱም በኩል ድብልቅልቅ ይላል። የክቡ መጠንም ይሰፋና ፉከራው በዚያው በክቡ ውስጥ ሁለትም ሶስትም ስፍራ ይካሄዳል።



የለቀስተኛው ቁጥር ሲጨምር ፋክራው ሁለትም ሶስትም ክብ ሲሰራ (ከኋላ ሌላ ክብ እንዳለ ልብ ይሏል)

የሟች ወዳጅ ዘመዶች ከሩቅ አገር ሲመጡ የራሳቸውን ፎካሪ፣ የፋክራ ማድመቂያ ቁሳቁስ፣ ለለቀስተኛው የሚሆን ምግብና መጠጥ በማስጫን ነው። በቦታው ርቀት ምክንያት አስከሬኑ ከቤት ሳይወጣ መድረስ ስለማይችሉ በየመንገዱ አስከሬኑ ለፍታት ሲያርፍ ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን እየመጡ ይቀላቀላሉ።

ምግቡን፣ መጠጡን፣ ፎካሪውን፣ ወዘተ. ከራሳቸው አገር የሚያመጡበት ምክንያት ለሟችና ለቤተሰቦች ያላቸውን ቅርበት ለመግለፅ፣ የሃዘናቸው ተካፋይ መሆናቸውንና የዋሉትን ውለታ ለቤተሠቦች ለማስገንዘብ ሲሉ ነው።

አስከሬን ጉዞ እስኪጀምር ድረስ ከላይ በተገለጸው አኳኋን እየተፎከረ ይቆይና ጉዞ ሲጀምር፣ አቀንቃኝ - "ጉሜ ሎጋው ጉሜ" ሲል ተቀባይ ደግሞ "አመልማል ጉሜ" እያለ ፎካሪውና ሌላው ወንድ በሙሉ የያዘውን ጠመንጃም ሆነ በትር አንዴ ከፍ፣ አንዴ ዝቅ በማድረግ ይጓዛል። በዚህ ጉዞ ወቅት ወንዶች «ጉሜ» ሲሉ፣ በሴቶች ግን የሚፈጠር ምንም ድምጽ የለም።

"ጉሜ" ምን ማለት እንደሆነና ለምን እንደሚባል መረጃ ያቀበሉ አንዳንድ የማህበረሰቡ አባላት (ለምሳሌ፣ አቶ ሞላ መኮንን፣ አቶ ጌታ ጣፈጠ፣ አቶ አወቀ ታከለ) መልሳቸው "እንጃ፣ ለምን እንደሚባል አላውቅም" የሚል ቢሆንም፣ በክዋኔ ወቅት ከሚሠጠው አገልግሎት በመነሳት ግን የሚከተለውን አስተያየት መሠንዘር ይቻላል። ይኸውም "ጉሜ" አስከሬኑ ጉዞ በጀመረ ቁጥር የሚባል በመሆኑ እንደ የጥሩንባና የጥይት ድምጽ ሁሉ የአስከሬን ጉዞ መጠቆሚያ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል። በጉዞ ወቅትም ለፉከራ አመቺ ጊዜና ቦታ እስኪገኝ ድረስ እንደመሸጋገሪያ ሆኖም ሲያለግል ይታያል።

እያንዳንዱ ፎካሪ በክቡ ውስጥ እየገባ በግጥሙ የሟቹን ዘር እየቆጠረ፣ ጀግንነቱንና ለጋስነቱን እያወደሰ፣ የግዳዩን አይነት፣ የምርኮውን ብዛት፣ የዘመቻውን ጊዜና ቦታ እየጠቀሰ፣ ፈሪ፣ ሌባ፣ ውሸታም ሰነፍ፣ የሆነን ሰው እየወቀሰ፣ ሲያቀርብ የሚጠቀሱት የሰው፣ የእንስሳት፣ የቦታ፣ የቁሳቁስ፣ ስሞች በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት ዘንድ የሚታወቁና ልዩ ክብር የሚሰጣቸው ናቸው። የሚጠቀሱት የሰው ስሞች ቀድመው የሞቱ የሟች ወዳጅ ዘመዶችና ታዳሚው በቅርብ የሚያውቃቸው በጀግንነታቸው የሚታወቁ የሌሎች ሰዎች ስሞች ናቸው።

እነዚህን በፉከራ ጊዜ የሚወጡ ቁሳቁሶች፣ እንስሳት፣ እንዲሁም ስለፉከራ ዓላማ አስመልክተው አቶ ሞላ መኮንን ሲያስረዱ እንደሚከተለው ነው።

> አገራችን በጣሊያን በተወረረች ጊዜ፣ የጠላት ጦር ወደ መሃል አገር ከመግባቱ በፊት፣ አንዳንድ ወኔ ያላቸው ጀግኖች እንደዛሬው መኪና የለም፤ በቅሎ፣ ፈረስ ጭነው፣ አንዳንድ ኋላ ቀር ጠመንጃዎችና ጋሻ፣ ጦር፣ ጉራዴ፣ ይዘውና በእግራቸው ተጉዘው ተዋግተዋል። በሌላ አቅጣጫ ዙሮ ጣሊያን መሃል አገር ሲገባም "እምቢ አሻፈረኝ!" ብለው በዱር በገደል ሸፍተዋል። ለውጊያ የተጠቀሙት በነዚህ መሳሪያዎች ነው። ታዲያ ያን ለማስታወስ እነዚህ ዘማቾች ሲሞቱ መሳሪያዎች ይወጣሉ። በቅሎና ፈረሱም ያው የጦር አጋር የነበረ ነው። አሁን ቅርብ ጊዜ በኤርትራ ጦርነት ለተሳተፉም ያው ይኸ ዘመን አመጣሽ መሳሪያ [ክላሽንኮቭ እና ኤም ፎርቲን ማለታቸው ነው] ተይዞ ይፈከርላቸዋል። መሳሪያው ሟች በጦርነት ወቅት፣ አደን ሲያድን፣ ይዞ የተሰለፈው ይህን ነው ለማለት ነው። የአሁኑ ትውልድም የሰዎችን ሙያና ዝና እንዲያውቅ፣ መሳሪያዎችን ደግሞ በዚያው ያውቃል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 20/2002 ዓ.ም)።

አቶ ሞላ መኮንን እንዳሉት፣ በፉከራ ጊዜ የሚወጡት ጋሻ፣ ጉራዴ፣ ጦር፣ ጠመንጃ፣ ፈረስ፣ ወዘተ. አገልግሎታቸው ፎካሪው ወደ ቁጣ ባደላ ንግግሩና በፈጣን የሰውነት እንቅስቃሴው፣ "ሟች ጠላትን የተዋጋበት፣ አድኖ የገደለበት፣ በዚህ መሳሪያ እንዲህ

እያደረገ ነበር” ብሎ ለትውልዱ ታሪኩን የሚገልፅበት፣ ትውልዱንም የሚያስተምርበት መንገድ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ለኛ ሲል ከፍተኛ ትግልን አድርጎና መስዋዕትነትን ከፍሎ፣ አገራችን ከጠላት ጠብቆ ያቆየልንን፣ ጋሻችንን፣ ጥላችንንና መከታችንን ዛሬ አጣን፤ በሞት ተነጠቅን ማለትም ይሆናል።

ፉከራ የአባቶችን ታሪክ በመንገር፣ በወጣቶች ዘንድ ጀግንነት፣ አልደፈርም ባይነት ወኔ እንዲኖራቸው ማድረጊያ መንገድ ስለመሆኑ ብዙዎች የማህበረሰቡ አባላት የሚስማሙ ቢሆንም የአንዳንዶቹ አመለካከት ደግሞ ከዚህ የተለየ ነው። የተለየ አመለካከት ካላቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች መካከል ካህናት የመጀመሪያዎቹ ናቸው።

ካህናት ፉከራን የሚቃወሙበት ምክንያት፣ ሟችን እያሞገሱና እያወደሱ፣ ስለገደለው የሰው፣ የእንስሳት አይነት እያነሱ፣ በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ማቅራራትና መፎከር የሟች ነፍስ ሲኦል ትገባ ዘንድ የምስክርነት ቃል መስጠት ነው በማለት እንደሆነ መሪጌታ አራጌ ባዩ አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3/2002 ዓ.ም)። በሌላ በኩል፣ አቶ ብርቄ ሚካኤል የተባሉ መረጃ አቀባይ፣ “ቄሶች ያልገደለውን ገዳይ አትበሉ፤ ለሰይጣን እየመሰከራችሁ ነው። እኛ በጉን ይማረው እያልን እናንተ ደሞ ትመሰክራላችሁ ይላሉ” በማለት ካህናት እንዳይፎከር የሚከለክሉበትን ምክንያት አስረድተዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3/2002 ዓ.ም)።

በማህበረሰቡ ዘንድ መንግስታዊ አካላት በተለይም ፖሊሶች በፉከራ ክዋኔ ላይ “አሉታዊ ተፅእኖ” የሚፈጥሩ ተደርገው ይታመናሉ። ማህበረሰቡ ተጽእኖ የሚለው በፉከራ ወቅት ከሚተኮሰው ጥይት ጋር የተያያዘ ነው።

ረዳት ኢንስፔክተር ሞላ እንየው የተባሉ ፖሊስ ፉከራንና ክዋኔውን ሲገልጹ፣

> ፎካሪዎች ጦር መሳሪያቸውን ይዘው በመውጣት በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ የሚያሳዩት ትርኢት ራሱ ወኔን ይጨምራል፤ በጣም አስደሳች ነው። ለወጣቱ ትውልድ ለሃገሩ ፍቅር እንዲያድርበት፣ የአባቶችን ጀግንነት እንዲያውቅ ያደርጋል። ወጣቱን ያነሳሳል። ይሁን እንጂ፤ ጥይት ሲተኮስ እንከለክላለን። መተኮስ፣ የአካባቢን ሰላም ያናጋል፤ አንድ ጥይት ዛሬ ከአስራ አምስት ብር በላይ ነው። የዘመኑ መሳሪያ ደግሞ አውቶማቲክ ነው፤ በአንድ ጊዜ ብዙ መተኮስ የሚችልና ብዙ ካልተተኮሰ የማያሞቅ ነው። በመሆኑም መተኮስ ኢኮኖሚን በዳይ በመሆኑና ሰላምን ስለሚያናጋ “አትተኩሱ” እንላለን። “እምቢ” የሚል ቢኖር፣ በመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ፣ ሲያልፍ

ደግሞ መሳሪያውን ለመንግስት ገቢ በማድረግ፣ ተኳሹም በእስር እንዲቀጣ ይደረጋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 10/2002 ዓ.ም)

ብለዋል፡፡

ረዳት ኢንስፔክተር ሞላ እንዳሉት፣ በጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚደረገውን ቀረርቶና ፉከራ የመንግስት አካላት ያበረታታሉ፡፡ የሚነቅፉት በሥነ ሥርዓቱ አፈፃፀም ወቅት የሚተኮሰውን ጥይት ነው፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ የፀጥታና የኢኮኖሚ ጉዳይ እንጂ፤ ካህናት እንደሚሉት፣ ከፅድቅና ከኩነኔ ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡ ከካህናት፣ ከመንግስታዊ አካላት፣ ወይም ከፖሊሶች በተጨማሪ በእድሜ የገፉ አዛውንቶችም በአሁኑ ጊዜ የሚደረገውን የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ በተመለከተ የተለየ አመለካከት ያላቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች ናቸው፡፡ የነዚህኞቹ አመለካከት እንደካህናቱና እንደመንግስታዊ አካላት ወይም ፖሊሶች ሁሉ ከሃይማኖታዊና ከፖለቲካዊ ጉዳይ ጋር የተያያዘ አይደለም፤ ከሚፎከርላቸው ሰዎች ማንነት ጋር የተያያዘ እንጂ፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክተው የአካባቢው የእድሜ ባለፀጎች ሲያስረዱ፣ "በፊት ለዘማችና በአደን ለሚታወቅ ነበር ሚፈከር፡፡ አሁን ግን እንዲያው ለገበሬው፣ መቆፈሪያና እርፍ ለጨበጠው ሁላ ይፈከርለታል፡፡ ሚዳቋ እየገደለ የቤቱን ግድግዳ በቆዳ የገጠገጠ ሁላ እንደ አዳኝ ይፈከርለታል፡፡ ቀድሞ ምናውቀው እንዲያ አልነበረም" በማለት የሚፎክርላቸው ሰዎች ማንነትና የፉከራ ልማድ እየተለወጠ መምጣቱን ገልጸዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)፡፡

ይህ ደግሞ በቀደመው ትውልድና በአሁኑ ትውልድ መካከል የአመለካከት ልዩነት መፈጠሩን ያሳያል፡፡ ይኸውም፣ ለቀደምቶቹ ጀግና ማለት ከፍተኛ ትግልንና መስዋዕትነትን በሚጠይቁ ተግባራት ተሰልፎ፣ ማለትም በዘመቻ፣ በአደን (በተለይም ቀንዳቸው፣ ጭራቸው፣ ቆዳቸውና ጥርሳቸው ውድ በሆኑና ክብርም በሚያስጡ እንደ ጐሽ፣ አንበሳ፣ ቀጭኔ፣ አውራሪስ አደን) ገድል ለፈጸመ እንጂ፤ ጠንካራ ገበሬም ይሁን ሚዳቆና ድኩላ የገደለ ሁሉ ጀግና አይደለም፡፡ ለአሁኑ ትውልድ ደግሞ ብዙ አምርተው ገበያውን ያጠገቡ፣ የአካባቢያቸውን ነዋሪ ያበሉና ያጠጡ ገበሬዎችም፣ ሚዳቆና ድኩላ አድነው የገደሉም፣ እንደቀደምቶቹ ጀግኖች ተቆጥረው ይፎከርላቸዋል፡፡

በተጨማሪም አቶ ደርበው፣ የድሮው ቀረርቶና ፉከራ ክዋኔ ምን ይመስል እንደነበረ ሲያስረዱ፣ «ቀድሞ ሲፈከር ምናውቀው ፈካሪው መሃል ገብቶ ተዚህ ገዳይ፣ እያለ ሲፈክር ተጎን ያሉትና መዝመቱን ሚያውቁ ደሞ ‹ልክ ነው!፣ ትክክል ነው› እያሉ ሲፈክሩ ነው፡፡

አሁን ግን አደባልቀውታል። ዛዲያ ሌላው ሰው ‹አሁን ተምን የገደለውን ነው፤ ማናውቅ?› እያለ ያነውራል" ብለዋል(ምንጭ፣ እንደላይኛው)።

አቶ ብርሃን አዱኛም፣ "የቀድሞው ፍከራ ለአዳኝና ለዘማች ብቻ ነበር። ፈካሪው ሲፈክርም ታሪኩን በትክክል በመናገር እንጂ ዝም ብሎ አልነበረም። ፈካሪው ገዳይ፣ ማራኪ እያለ ሲዘረዝር፣ የሟቹን ታሪክ የሚያውቁ ሰዎች ‹አዎ፣ አውቃለሁ› ይላሉ። ሟቹ ያልሰራውን ታሪክ ፈካሪው የተናገረ እንደሆነ እዚያው ላይ ጓደኛው ‹ሃሰት፣ የት አየህ? የት ሰማህ?› ብሎ ፈካሪውን ያሳፍረዋል። አሁን ግን ይሽ ይሽ ተለውጧል" በማለት የድሮውንና የአሁኑን የፉከራ ክዋኔ በማነፃፀር አስረድተዋል(ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም) ።

አቶ ብርሃን ያሉት እንዳለ ሆኖ፣ በክዋኔ ወቅት ፎካሪውን መንቀፍና መተቸት ዛሬም ይታያል። ይህም የሚታየው ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ለገበሬው "ገዳይ" እያለ ሲፎክር "ገዳይ አትበለው..." ብሎ ሲነቅፍ ነው።

ከዚህ ቀደም በተገለጸው አኳኋን አስከሬኑ ለጉዞ እስኪያርፍ ጉሜ እየተባለ፣ ባረፈበት ጊዜና ቦታ ሁሉ ቀረርቶና ፉከራ እየተደረገ ቤተ ክርስቲያን ይደረሳል።

ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ከገባ በኋላ የመጨረሻው የጉዞ ፍታት ይደረግና አስከሬኑ ቤተ ክርስቲያኑን አንድ ጊዜ እንዲዞር ይደረጋል። ይህን አስከሬን የማዞር ሥርዓት ካህናት ዑደት ይሉታል።

አስከሬን ለምን ዑደት እንደሚያደርግ መሪጌታ አራጌ ባዩ ሲያስረዱ የሚከተለውን ብለዋል፤

> ታቦት ነግሶ ወደ መቅደስ ሲመለስ ቤተ ክርስቲያኑን አንድ ጊዜ እንዲዞር ይደረጋል፤ ዑደት ይባላል። ዑደቱ የምዕመናን ልመናና ጸሎት ሰማየ ሰማያት ደርሶ በረከት እንዲያገኙ ተብሎ የሚደረግ ነው። አስከሬኑም ዑደት የሚያደርገው ለቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ ስንብት ለማድረግና ይህንኑ በረከት እንዲያገኝ ተብሎ ነው (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3/2002 ዓ.ም)

መሪጌታ አራጌ እንዳሉት፣ ዑደት አስከሬን ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚያደርገው የመጨረሻ ስንብት ነው። ዓላማውም ሟች ምህረት እንዲያገኝ ተብሎ የሚደረግ ነው።

አስከሬኑ ዑደት ካደረገ በኋላ የሟቹ የነፍስ አባት ወይም ስርዓቱን የሚመሩት ካህን ወደ ለቀስተኛው ዞረው ቀረርቶውና ፉከራው እንዲቆም ያዛሉ። ከዚያም ጮክ ብለው ሶስት ጊዜ "የሟች ነፍስ ይቅር በሉኝ ትላለች ፤ ይቅር ብላችሁ ሸኟት" ይላሉ። ለቀስተኛውም ሶስት ጊዜ «ይቅር ስለ እግዚአብሔር» ይላል። ቀጥሎ አስከሬኑን በቤተ ክርስቲያኑ ምዕራብ በኩል

ወደ ምስራቅ ሶስት ጊዜ ያሠግዱታል፡፡ መሪጌታ አራጌ ባዩ፣ አስከሬን ሶስት ጊዜ ይቅር መባሉንና ሶስት ጊዜ እንዲሰግድ መደረጉን፣ በዑደት ወቅት ታቦትና አስከሬን፣ ቤተ መቅደስና መቃብር የሚነፃፀሩበትን ሁኔታ አስመልክተው ሲያስረዱ፤ "ሶስት ጊዜ ይቅር የሚባለውና ሶስት ጊዜ ወደ ምስራቅ የሚሠግደው ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ የሚጠየቅ ይቅርታና ለሶስቱም የሚደረግ ስግደት ነው፡፡ ዑደቱም ስግደቱም በልምድ የመጣ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለዑደትና ስለስግደት አላነበብኩም" በማለት አስረድተዋል(ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3/2002 ዓ.ም)፡፡ ይህ ደግሞ ሃይማኖትና ልማድ ድንበር ሳይለይላቸውና አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው የሚከናወኑ መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡

ዑደቱና ስግደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀረርቶውና ፉከራው ይቀጥላል፡፡ አስከሬኑም በካህናትና በጥቂት ሰዎች ታጅቦ ወደ መቃብር ቦታው ይወሠዳል፡፡ ከዚያም የሟች የነፍስ አባት ወይም ስርዓቱን የሚመሩት ካህናት ጉድጓዱን ይባርኩትና በብርሌ ተሞልቶ ጸሎት ሲደረግበት በዋለው ውሃ (ማየ ህይወት ወይም ጸበል ይሉታል) የመቃብር ጉድጓዱን ይረጩታል፡፡ ከዚያም አስከሬኑ ወደ ጉድጓዱ ከመግባቱ በፊት ሁለት ሰዎች ወደ ጉድጓዱ ገብተው በሁለቱ የጉድጓዱ ጫፎች ይቆማሉ፡፡ ከዚያ ጉድጓዱ ውስጥ ርጥብ ቅጠል ጨምረው ይጉዘጉዛሉ፡፡ ከጉድጓዱ ውጭ የቆሙት ሰዎች ደግሞ አስከሬኑ ወደ ጉድጓድ ሲወርድ እንዳይታይ የጉድጓዱን ዙሪያ በጋቢ ወይም በነጠላ ይከልላሉ፡፡ የሚከለለው በቀጥታ ሲታይ ሌላውን ለቀስተኛ እንዳያስደነግጥ ነው፡፡ እርጥብ ቅጠል የሚጉዘጉዘውም አስከሬኑ አፈር ላይ እንዲሁ እንዳያርፍ ለማድረግ ነው፡፡

ቀጥሎ ከውጭ ያሉት ሰዎች አስከሬኑን ከነበረበት አልጋ ያነሱና ቀስ አድርገው በገመድ ጉድጓዱ ውስጥ ላሉት ሁለት ሰዎች ያቀብላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎችም አስከሬኑን ተቀብለው ራሱን ወደ ምዕራብ፣ እግሮቹን ደግሞ ወደ ምስራቅ አድርገው በጀርባው እንዲያርፍ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያ ከጉድጓዱ ይወጡና ከስር የተጉዘጉዘው አይነት ቅጠል ከአስከሬኑ ላይ ይጨምራሉ፡፡ ቀጥሎ በአካፋ አፈር ወደ ጉድጓዱ ይመልሳሉ፡፡ ጉድጓዱ በአፈር ከተሞላ በኋላ፣ መቃብሩ ከስሩ ሰፋ ወደ ላይ ደግሞ ሾጠጥ እንዲልና በግምት አንድ ሜትር የሚደርስ ተደርጐ ይገነባል፡፡ የሚገነባው ሰዎች እዚያው አካባቢ በሚያመጡት ድንጋይ ነው፡፡ በድንጋይ የሚገነባው አንድም አስከሬን ፈንቅለው ከሚበሉ አራዊት ለመከላከል፣

አንድም በጊዜ ብዛት ቦታው እንዳይጠፋ፣ ለሌላ መቃብርነት ሁለተኛ እንዳይቆፈርና እንደሐውልት እንዲቆጠር ለማድረግ ነው።

ከዚያ ካህናቱና አስከሬኑን የቀበሩ ሰዎች አፈር እየጨበጡ ወደመቃብሩ ይበትኑና ትንሽ ራቅ ብለው በመቆም ካህናቱ የቤተ ክርስቲያኑን ደወል በዲያቆናት ያስደውላሉ። በዚህ ጊዜ የሟች ቤተሠቦች የቀረርቶውንና የፉከራውን ትዕይንት ሲመለከትና አንዳንዴም ሲሳተፍ በቆየው ህዝብ ታጅበው እየጮኹና አምርረው እያለቀሱ (ሴቶች ይበዛሉ) ወደ መካነ መቃብሩ ይመጣሉ። ወንድ የሟች ወዳጅ ዘመዶች ደግሞ ወደ ሰማይ አከታትለው ጥይት ይተኩሳሉ። ጩኸቱ፣ ዋይታው ድብልቅልቅ ይላል።



1. ጉድጓዱን በጋቢ ሲከልሉ



2. አስከሬኑን ለሚቀብሩ ሰዎች ሲያቀብሉ



3. አስከሬኑን ወደ ጉድጓድ ሲያስገቡ



4. መቃብሩን በድንጋይ ሲገነቡ

የሟች ወዳጅ ዘመዶች እዚያው ቆመው ለትንሽ ጊዜ አምርረው ካለቀሱ በኋላ፣ አፈር እየጨበጡ መቃብሩ ላይ እየበተኑ ይመለሳሉ። አፈር ጨብጦ መቃብር ላይ የመበተንን ሥርዓት «እርም ማውጫ» ይሉታል። ቀጥሎ ፍኳሪዎች መቃብሩን ከበው፣ የጥይት እሩምታ እያወረዱ ለመጨረሻ ጊዜ ፎክረው ወደ አውደ ምህረቱ ይመለሳሉ።

በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት አስከሬን ሰባት ጊዜ የጉዞ ፍታት እንደሚደረግለት፣ ቤተ ክርስቲያኑን አንድ ጊዜ ከዞረ በኋላ፣ ወደ ምሥራቅ ሶስት ጊዜ እንደሚሰግድ፣ ሲቀበርም ራሱ ወደ ምእራብ፣ ፊቱ ደግሞ ወደ ምስራቅ ተደርጐ እንደሆነ፣ ቀደም ብሎ ተገልጿል። የሰባትንና የምስራቅን ሃይማኖታዊ መሠረት ካህናት እንደሚከተለው ያስረዳሉ፤

> ሰባት፣ አንድም ቀደም ብሎ በግንዘት ሥነ ሥርዓት እንደተገለፀው የሰው ልጅ በሰባቱ ባህርያት (በሶስቱ ባህርያተ ነፍስና በአራቱ ባህርያተ ሥጋ ያልነው ነው) ተደፋፍሮ፣ በሳምንቱ ሰባት ቀናት የሰራቸውን ሃጢያቶች እግዚአብሔር ይቅር በለው ማለት ነው። ወደ ጉዞ ፍታት ሰባትነትስንመጣ ደግሞ ሰባት ጊዜ መደረጉ፣ እያሱ በጽንዓ እጣን እያጤሰ በመፀለይ የእያሪኮን ግንብ ሰባት ጊዜ ዞሮ ግንቡ ፈርሶለታል። እያሱ በፀሎት ግንቡን እንዳፈራረሰው ሁሉ፣ የሟቹም ሃጢያት በዚህ ፀሎት እንደግንቡ ይፈራርስለት ተብሎ ሰባት ጊዜ ፀሎት ይደረግለታል። ሌላው ኤልሳ ሰባት ጊዜ ፀልዮ የሞተውን ብላቴና አድኖታል፤ "የእኛ የጉዞ ፀሎትም፣ ግንዘትም ይሄ የአምላክ ፈቃድ ይሁንልን" ብለው ካህናት የሚያደርጉት ነው

በማለት የጉዞ ፍታት ሰባት ጊዜ የሚደረግበትን ምክንያት አስረድተዋል (ሊቀ ካህናት መልአከ ገነት አበበ፣ ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም)።

አስከሬን ወደ ምሥራቅ ሶስት ጊዜ እንዲሰግድ፣ ሲቀበር ራሱ ወደ ምዕራብ እግሮቹ ወደ ምስራቅ የሚደረጉበትን ምክንያት ደግሞ እኚሁ ካህን ሲያስረዱ፣ "ፊተ ገፁ ወደ ምስራቅ ሆኖ ሶስት ጊዜ ሰግዶ፣ አስከሬኑ የሚቀበረው ቅድስት እየሩሳሌም በምስራቅ በኩል የምትገኝ በመሆኗ ያንን ለማመልከት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም ይኸው ሥርዓት እንዲፈፀም ታዛለች" ብለዋል፡፡

መሪጌታ አራጌ ባዩ የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ፣ "አስከሬን ፊቱ ወደ ምስራቅ ተደርጐ የሚቀረበረው፣ ክርስቶስ በምፅዓት ቀን በምስራቅ በኩል ሲመጣ፣ ሙታንም በዚያ ጊዜ ስለሚነሱና ሟችም ያችን ቀን በተስፋ የሚጠብቅና ከመቃብርም የሚነሳ መሆኑን ለማመልከት ነው" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 3/2002 ዓ.ም)፡፡

ቄስ ዓለሙ ጐደም፣ "መፅሐፉ ‹ፀሐይ ከምስራቅ ይወጣል› ይላል፡፡ እንግዲህ ፀሐይ የተባለው የዓለም ብርሃን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ምስራቅ የተባለችውም ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ከማርያም ተወልዶ ጨለማውን ዓለም ብርሃን ያደርጋል ለማለት ነው" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 6/2002 ዓ.ም) ፡፡

ካህናት ከዚህ በላይ ለምስራቅ አቅጣጫ የሰጡትን ትርጓሜ ስናይ፣ ትርጓሜዎቹ በጥቅሉ ከእየሩሳሌም መገኛ አቅጣጫ ጋር፣ ከዳግም መነሳት (ትንሳኤ) ተስፋ ጋር፣ ከማርያምና ከክርስቶስ ጋር፣ የተያያዙ ናቸው፡፡ ካህናት ያሉት እንዳለ ሆኖ፣ይህንን ሁሉ ሃሳብ "ተስፋ" የሚለው ቃል ይገልፀው ይመስለኛል፡፡ ይኸውም የክርስቶስ ዳግም መምጣትም ይሁን የሟች ዳግም መነሳት ሁሉም ተስፋን የሚገልፁና በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ "ከሞት በኋላ ህይወት (Life after deathን)" የሚያፀኑ በመሆናቸው ነው፡፡

## 4.3 ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች

የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ፍፃሜ ተከትሎ የሚከተሉት ሥነ ሥርዓቶች ይከናወናሉ፡፡ በመጀመሪያ ለቀስተኛው በሙሉ በአውደ ምህረቱ ይሠባሠባል፡፡ ቀጥሎ የሟች ቤተሠቦች ከለቀስተኛው ነጠል ብለው መሃል ላይ በመቆም ይላቀሳሉ፡፡ ለቀስተኛውም በየተራ እየሄደ የግራ ትከሻቸውን እየነካ ትንሽ ካለቀሰ በኋላ፣ ተራውን ለሌላው ለቅሶ ደራሽ እየተወ ወደመጣበት ይመለሳል፡፡ በዚህ አኳኋን ትንሽ ከተለቀሠ በኋላ፣ ለቅሶውን ሲያስተናብሩ የቆዩ ሽማግሌዎች ተነስተው "በቃችሁ ዝም በሉ፤ እሱ ፈጠረ እሱ ወሰደ እንጂ ሌላ ምን ይባላል? ምን አውርድ ነው የምትሉት? ምነው ሞት በእናንተ አልተጀመረ፤ በሉ ተዉት!"

በማለት ምክርም ተግሳፅም ይናገራሉ። የሟች ቤተሰቦችም ምክሩንና ተግሣጹን ወይ ተቀብለው፣ ወይ ፈርተው፣ ቀስ በቀስ ሁሉም ማልቀስ ያቆማሉ። ይህ ዝምታ ከሃዘኑ ብዛት በመድከም፣ ሽማግሌዎች ያሉትን በማክበር ወይም በይሉኝታ፣ አልያም ሽማግሌዎች ያሉት የፈጣሪ ቁጣ እንዳይከሰት በመፍራት ሊመጣ የሚችል ነው። የሽማግሌዎችን ንግግርም እንደ ውግዘት በመቁጠር፣ ሁሉም ከማልቀስና ከማውራት ተቆጥቦ ትኩረቱን ወደ ቀጣይ ሥነ ሥርዓቶች ያደርጋል።

በዚህ ጊዜ የሟቹ የነፍስ አባት ወይም ሥርዓቱን ሲመሩት የዋሉት ካህን "መፅሐፈ ግንዘት" የሚባል መፅሐፍ ጮክ ብለው ያነባሉ። ይህ መፅሐፍ የሚነበበው በግዕዝ ነው።



ካህኑ መጽሐፈ ግንዘት ሲያነቡ

ሊቀ ካህናት መልአከ ገነት አበበ መፅሐፈ ግንዘት ምን ማለት እንደሆነና ለምን እንደሚነበብ ሲገልጹ፤

> መፅሐፈ ግንዘት ከመፃሕፍት ተውጣጥቶ በሊቃውንቱ የተደረሰ እና ለሙት ያስፈልገዋል ተብሎ የሚነበብ የፀሎት መፅሐፍ ነው። የሟች ነፍስን ተቀብላት፤ ይቅርም በላት እየተባለ የሚነበብለት የፀሎት መፅሐፍ ነው። በጥቅሉ ለእርቅ የሚነበብ መፅሐፍ ነው (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 19/2002 ዓ.ም) ብለዋል።

ይህን መፅሐፍ ካህኑ አንብበው እንደጨረሱ፣ "የሟች ነፍስ ከምድራዊ ወደ ሰማያዊ ህይወት ተሸጋግራለችና በገነት ያኑርሽ ብላችሁ ሸኟት" ይላሉ። ይህንን ንግግራቸውን ተከትሎ ለቀስተኛው በአንድነት፣ "እግዚአብሔር ይማራት፤ በገነት ያኑራት" ይላል። ምህላም ይደረጋል። ከዚህ ቀጥሎ ለቀስተኛው በለቅሶው አስተናባሪዎች በያለበት እንዲቀመጥ ወይም እንዲቆም ከተደረገ በኋላ የሟች የህይወት ታሪክ ይነበባል። የሟችን የህይወት ታሪክ የፃፈው ግለሰብ ካህኑ መፅሐፈ ግንዘት ወዳነበቡበት ቦታ ይሄድና ድምፁን ከፍ አድርጎ "የአቶ እገሌ አጭር የህይወት ታሪክ" በማለት ማንበብ ይጀምራል። ከዚያም ሟች ከማን፣ የት፣ መቼ እንደተወለደ፣ እንዴት እንዳደገ፣ የሥንት ልጆች አባት እንደሆነ፣ ምን ምን መልካም ሥራዎች እንደሰራ፣ ምን ያህል አመት እንደኖረ፣ መቼ እንደሞተ፣ የሚያትት ፅሁፍ ያነባል።



የሟች የህይወት ታሪክ ሲነበብ

የህይወት ታሪክ ሲነበብ የለቀስተኛው ስሜት የሚሳበው በሚከተሉት ጉዳዮች ነው። እነዚህም በህይወት ታሪክ አንባቢው የአነባበብ ፍጥነት፣ በሟቹ መልካም ሥራዎችና በስንት አመቱ መሞቱ ናቸው። ይህም የሚታየው የህይወት ታሪኩ ሲነበብ ለቀስተኛው ድምፁን ዝቅ በማድረግና ከንፈሩን በመምጠጥ፣ "አይ መማር አንበለበለው እኮ!፣ እድሜውስ በቅቶ

ኖሮ ወይም ውይ አፈር ልብሳ ገና ልጅ ኖሮ፣ ሥራውስ ታምር ነው፣ ወዘተ.» እያለ አስተያየቱን ሲሰነዝር ነው፡፡

የህይወት ታሪክ የሚነበበው፣ በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት የሟችን ማንነት የማያውቁ ለቀስተኞች ሁሉ ሊቀብሩ ስለሚመጡ፣ በሚነበበው ታሪክ ሟችን እንዲያውቁ ለማድረግ እንደሆነ የማህበረሰቡ አባላት ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ፤ ሟቹ አንዴ ሞቷል፤ የህይወት ታሪኩ ታወቀ አልታወቀ ለሟቹ የሚፈይደው ነገር የለም፡፡ ከዚህ በላቀ ግን፣ የሟች ወገኖች "የዚህ ታሪክ ፈፃሚ ወገኖች ናቸው" ተብሎ ዝናቸው እንዲወራ፣ ክብራቸው እንዲጠበቅ የሚያደርጉበት ስልትነት ያመዝናል፡፡

የሟች የህይወት ታሪክ እንደተነበበ የሟች ቤተሰቦች ለየት ብለው ይቆማሉ፡፡ ከዚያ አጋጣሚ አግኝተው ለቅሶ ያልደረሱ ለቀስተኞች ወደነዚህ ሃዘንተኞች በመሄድ፣ በቀኝ እጃቸው የግራ ትከሻቸውን እየነኩ፣ "እግዚአብሔር ያጥናችሁ" ይላሉ፡፡ ሃዘንተኞችም "አሜን! በእኛ የደረሰ አይድረስባችሁ፤ ክፉ አይንካችሁ" በማለት መርቀው ይሸኛሉ፡፡

"ያጥናችሁ" ለምን እንደሚባል አቶ ብርሃን አዱኛ ሲገልጹ፣ "ያጥናችሁ ከመጽሐፍ ቅዱስ የመጣ ነው፡፡ አዳም ከገነት በተባረረ ጊዜ አምርሮ ለረጅም ጊዜ ሲያለቅስ ጌታችንም፣ ‹ሄዳችሁ ያጥናህ በሉት› ብሎ ላከ፡፡ እሱንም ያጥናህ ሲሉት ሃዘኑን አቆመ ይባላል" ብለዋል (ኢንተርቪው፣ መጋቢት 5/2002 ዓ.ም)፡፡ ካህናት ግን "ልማድ ነው" ይላሉ፡፡

ለቅሶ ደራሾች የሃዘንተኞችን ትከሻ የሚነኩት፣ "ሃዘናችሁን ተካፍያለሁ፤ ሟችን ቀብሬያለሁ" የሚል ትርጉም እንዳለውና ሃዘንተኞችም በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ማን እንደተገኘና ማን እንዳልተገኘ የሚያውቁበት መንገድ እንደሆነ፣ በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝቶ እንኳ የሃዘንተኞችን ትከሻ ሳይነካ ቢቀር ለቅሶ እንዳልደረሰ እንደሚቆጠር የማህበረሰቡ አባላት ይናገራሉ፡፡ ትከሻ ለዚያውም የግራ ትከሻ ለምን ሆነ? ተብለው ሲጠየቁ ደግሞ፣ "ፊት ለፊት ሄዶ ለመንካትና እየኝ ለማለት ስለሚቀል ነው" ይላሉ፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ግራ ትከሻ ሌላም ትርጉም ያለው ይመስላል፡፡ ይኸውም በተፈጥሮው ግራኝ ከሆነ ሰው በስተቀር፣ ማንኛውም ሰው ሸክም የሚሸከመው በግራ ትከሻው ነው፡፡ ሃዘንም በመውደቅና በመነሳት ከሚገለፀው ባሻገር ትልቅ መንፈሳዊ ሸክም በመሆኑ፣ "ሃዘናችሁ ሃዘኔ ሆኖ ይኸው ተካፈልኩ፤ እናንተም ሸክሙ ይቅለልላችሁ" ማለት ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል፡፡

የለቅሶ ደራሾች ለቅሶ የመድረስ ጉዳይ ጋብ ሲል፣ አንድ በእድሜ ጠና ያሉ የሟች ቅርብ ዘመድ ለቀስተኛው በሙሉ ዝም እንዲል ከለመኑ በኋላ፣ "ወገን በእኛ የደረሰ አይድረስባችሁ፤ ቀባሪም አይንሳችሁ" በማለት ይመርቁ እና "የተዘጋጀ እህል ውሃ አለ እና ሳትቀምሱ እንዳትሄዱ!" የሚል መልዕክት ያስተላልፋሉ። ከዚያም ከሟች ቤትና ከወዳጅ ዘመድ ቤት ተዘጋጅቶ የመጣው የእዝን ምግብ ይቀርባል። የዚህ ምግብ አይነትና መጠን እንደሟች ግለሰብ አቅምና እንደተቀበረበት ቀን የሚለያይ ነው። ለምሳሌ፣ ሟቹ ግለሰብ የተቀበረው በፆም ቀን ከሆነ እንደሟቹ አቅም መጠኑ ይለያይ እንጂ ለእዝን የሚቀርበው ምግብ የባቄላ ወይም የሽንብራ በቆልት ነው። ቀብሩ በፍስክ ቀን የተከናወነ ከሆነ ደግሞ ለእዝን የሚቀርበው ምግብ እንጀራና ሥጋ ይሆናል። ይህ እንጀራና ሥጋ የማቅረብ ጉዳይ አሁንም እንደሟቹ አቅም የሚወሰን ነው።

ሟች የተቀበረው በፆም ቀን ከሆነ፣ የሚቀርበው ምግብ ከቤት ተዘጋጅቶ፣ በአህያ ተጭኖ የመጣ የባቄላ ወይም የሽንብራ በቆልት ይሆናል። አመጋገባቸው በሰፋፊ እቃ እየዞሩ ከሚያድሉ ሰዎች እየዘገኑ በየነጠላቸው ወይም በየጋቢያቸው ጫፍ በማድረግ ነው። ሟች የተቀበረው በፍስክ ቀን ከሆነ ደግሞ ቁጥሩ እንደሟቹ አቅም የሚወሰን የቀንድ ከብት ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወሰድና የቀብር ሥነ ሥርዓቱ በጐን እየተከናወነ፣ በጐን ደግሞ የእርድ ሥነ ሥርዓት ይከናወናል። ከዚያም ስጋው ወደ አውደ ምህረቱ ይመጣና በብረት ምጣድ ይጠበሳል። ቀጥሎ ለስላሳ ቅጠል መሬት ላይ እየተነጠፈ፣ እላዩ ላይ እንጀራ ይዘረጋበትና ስጋው ተደርጎበት ለቀስተኞች በየፆታቸው ተለያይተው ዙሪያውን እየከበቡ ይመገባሉ። በየፆታቸው ተለያይተው የሚመገቡበት ምክንያት በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ከተለያየ ቦታ የሚመጡ፣ የማይተዋወቁ ለቀስተኞች ስለሚኖሩና ብዙዎቹ የግለሰቡን ሞት እንደሰሙ በድንጋጤ እህል ሳይቀምሱ ስለሚወጡ፣ ከተቃራኒ ፆታቸው ጋር ቀርበው እንዲመገቡ ቢደረግ ተፋፍረው ብዙ ሳይበሉ ሊመለሱ ስለሚችሉ ነው።



ሟች የተቀበሩት በጾም ቀን በመሆኑ የቀረበ የእዝን ምግብ

በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ በየቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት የእዝን ምግብ የሚቀርበው በተለያዩ ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ባቂላም ይቅረብ ወይም ስጋ፣ የእዝን ምግብ የሃዘን ማብረጃ ወይም እርም ማውጫ ነው ተብሎ ይታሰባል። ሌላው ምክንያት ለቀስተኛው ከምግብ በኋላ፣ "የሟችን ነፍስ ይማር" እያለ በሚያደርገው ምርቃት፣ "የሟች ነፍስ ገነት ትገባለች" ተብሎ ስለሚታመን ነው።

የእዝን ምግብ አቅርቦት ከዚህ ያለፈ ማህበራዊ መልዕክትም አለው። ይህም የሟች ቤተሠቦች በኢኮኖሚ የበላይነትን ለማሳየት የሚጠቀሙበት መንገድ መሆኑ ነው። በተለይ ለእዝን የቀረበው ምግብ ሥጋ ከሆነ፣ "ይህን ያህል አርደው ያበሉ፤ የለጋስ ዘሮች" ተብለው ስማቸው እንዲጠራና ዝናቸው እንዲታወቅ የሚያደርጉበት መንገድ ነው። አንዳንዴ ደግሞ ማህበራዊ ተፅእኖን በመፍራት የሚደረግ ነው። ይህም የሟች ቤተሰቦች አቅም የሚፈቅድ ሆኖ በቀብር ሥነ ሥርዓቱ እለት አርደው ባያበሉ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደሆዳም ተቆጥረው፣ "ለአባታቸው፣ ለወንድማቸው፣ ለልጃቸው፣ ክብር የሌላቸው ጅቦች" ተብለው ይሰደባሉ፤ ይናቃሉ። የሟች ቤተሰቦችም ይህን የመሰለውን ማህበራዊ ተፅእኖ ፈርተው አርደው ያበላሉ።

የእዝን ምግብ ቀርቦ በሚበላበት ጊዜ ሌሎች ድርጊቶችም ይከናወናሉ። ለምሳሌ፣ መፃፍ የሚችሉ የሟች የቅርብ ዘመዶች የተለያዩ ቦታዎች ተቀምጠው የእድር ገንዘብ ይሰበስባሉ።

ተመግቦ የጨረሰ ለቀስተኛም ወደነዚህ ሰዎች በመሄድ ስሙን እያስመዘገበ፣ ከሀምሳ ሳንቲም ጀምሮ እስከ አምስት ብር እየሰጠ ይመለሳል።



የእድር ገንዘብ ሲሰባሰብ

ካህናትና የሟች ቤተሠቦች ደግሞ በመመካከር የሳልስት፣ የሰባት፣ የአስራ ሁለት፣ ወዘተ. የሚባሉ የፍታት ቀናትን ይወስናሉ። ከዚያ የሟች ቤተሠቦች ብቻ ከተመካከሩ በኋላ፣ የደመር ለቅሶ ቀጠሮ ቀን ወስነው ለለቀስተኛው ይናገራሉ።

የደመር ለቅሶ የሚቀጠረው በተለያዩ ምክንያቶች ነው። ይህም በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ወገን ዘመድ ተሟልቶ ሳይገኝ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ የተፈፀመ ከሆነ፣ ሟች ሃብታም ሆኖ ሳለ፣ በፆም ወቅት የቀብር ሥነ ሥርዓቱ የተፈፀመ ከሆነና በዚሁ ፆም ምክንያት የእዝን ምግብ ያልቀረበ እንደሆነ ነው።

በአካባቢው ማህበረሰብ ባህል መሠረት የደመር ለቅሶ የተለያዩ ማህበራዊ ሙያዎች አሉት። ከነዚህም መካከል፣ በተለያየ ምክንያት በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ላልተገኘ ሰው ለቅሶ እንዲደርስ ምቹ አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑ አንዱ ነው። አንድ የማህበረሰቡ አባል፣ ቢችል በቀብር ሥነ ሥርዓቱና በደመር ለቅሶ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ቢገኝ ይመረጣል። ካልቻለ ግን ከሁለቱ በአንዱ የመገኘት ማህበራዊ ግዴታ አለበት። ከሁለቱ ምርጫዎች በአንዱ የማይገኝ የማህበረሰቡ አባል ቢኖር "እርመ ቢስ፣ እርመ በላ" እየተባባለ ማህበራዊ ውግዘት ይገጥመዋል። ከማንኛውም ማህበራዊ ህይወትም ይገለላል።

ሌላው የደመር ለቅሶ ማህበራዊ ሙያ፣ በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ያልተገኘው ሠው ሁሉ፣ በየጊዜው ወደ ሟች ቤተሠቦች ቤት እየሄደ፣ ሃዘንተኞችን በየጊዜው በመስተንግዶና

በለቅሶ እንዳይጎዳቸው የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ሟቹ ግለሰብ ሃብታም ከሆነና የቀብር ሥነ ሥርዓቱ በያም ወቅት ከተፈፀመ፣ ቤተሠቦቹ የደመር ለቅሶው በፍስክ ቀን እንዲሆን ቀድመው በመወሰን፣ ድግሱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው የሚያደርጉበት መንገድ መሆኑ ነው፡፡

እነዚህ ሥነ ሥርዓቶች በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቁ በኋላ አብዛኛው ለቀስተኛ ወደየአገሩ ሲበታተን ሃዘንተኞች፣ ጐረቤቶችና ከሩቅ አገር የመጡ ሰዎች ደግሞ ወደ ሟች ቤት ያመራሉ፡፡ አካሄዳቸውም ሃዘንተኞች ከመሃል፣ ከሩቅ የመጡ ሠዎችና ጐረቤቶች ደግሞ ከፊትና ከኋላ ሆነው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ከውይይት በስተቀር ለቅሶ የለም፡፡ ውይይቱም በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ድምቀት፣ በተለይም፣ በቀባሪው ህዝብ ብዛት፣ በፉከራውና በፎካሪው ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እንዲህ እየተወያዩ ከሟች ቤት ይደርሳሉ፡፡ ከዚያም በሟች ቤት ደጃፍ በተዘጋጀው ዳስ ውስጥ ገብተው ይቀመጣሉ፡፡ አቀማመጣቸው የሟች ቤተሰቦች ከዳሱ መሃል ላይ ለነሱ ተብላ በተዘጋጀች ድንክ አልጋ ላይ፣ ሌሎች ደግሞ ዙሪያቸውን ከበው ለመቀመጫነት በተዘጋጀው ቦታ ሁሉ ይቀመጣሉ፡፡ ቀጥሎ ጐረቤቶች ሃዘንተኞችንና ከሩቅ የመጡ እንግዶችን ማስተናገድ ይጀራምሉ፡፡ ቡና ይፈላል፣ ምግብ ቀርቦ ይበላል፡፡






በሚች ቤት የተዘጋጀውን ዳስና በዳሱ ውስጥ የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች

# 5. ማጠቃለያና ይሁንታ

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ያተኮረው በላይ አርማጭሆ ወረዳ የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓትና በሥነ ሥርዓቱ ላይ በሚደረግ ቀረርቶና ፉከራ ክዋኔ ላይ ነው። ይህ የቀብር ሥነ ሥርዓት የሚከናወነው በወረዳው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ ዘንድ ሲሆን ሥነ ሥርዓቱ የአካባቢው ማህበረሰብ ጀግና ለሚለው (ለዘማች፣ ለገበሬ፣ ለአዳኝ፣) ሰው የሚከናወን ነው። የሥነ ሥርዓቱን ክዋኔ ለማሳየት ሂደቱ ቅድመ ሞት፣ በሞት ጊዜና ከሞት በኋላ፣ ተብሎ ተመድቧል። ቅድመ ሞት ሥነ ሥርዓት ተብሎ የተገለፀው ሂደት አንድ ሰው በጠና ታሞ እንደማይድን ከተገመተ ጊዜ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ የሚደረጉትን ክንውኖች የሚያመለክት ነው። በሞት ጊዜ ተብሎ የተገለፀው ሂደት ደግሞ የግለሰቡ ነፍስ ከስጋው ከተለየች ጀምሮ ግብዓተ መሬቱ እስኪፈፀም ድረስ የሚደረጉትን ክንውኖች የሚገልፅ ነው። በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚደረጉት ቀረርቶና ፉከራም በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ። ከቀብር በኋላ ተብሎ የተለገፀው ሂደትም የአስከሬኑን ግብዓተ መሬት ተከትሎ የሚደረጉትን ክንውኖች የሚገልፅ ነው።

በነዚህ ሂደቶች በጥቅሉ በወረዳው ባሉ አካባቢዎች አንድ ጀግና ሲሞት የሚደረገው የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በእያንዳንዱ ሂደት የሚከናወኑ አቢይና ንኡሳን ጉዳዮች፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ እንዲሞቅ የሚያደርጉ ቀረርቶዎች፣ ፉከራዎች፣ እና ሌሎችም በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚታዩ ሁሉ፣ በስፋት ተገልፀዋል። ጥናቱ በመስክ ሥራ በተገኙ መረጃዎች ተመስርቶ የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ክዋኔ ዓለማዊና መንፈሳዊ ገጽታ በማጥናት እንዲቀረስ ለማድረግ ታቅዶ የተከናወነ ነው። በተገኙት መረጃዎች መሰረትም በወረዳው የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት በተለይም፣ ከአስከሬን ግንዘት፣ለሟች ከሚደረግ የጉዞ ፍታት፣ ከአስከሬን ስግደት፣ ከአስከሬን የአቀባበር አቅጣጫ፣ ወዘተ.፣ ጋር ተያይዘው፣ በካህናትና በሌላው ማህበረሰብ የሚፈፀሙ እርስ በርስ የሚጣረሱ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ሥነ ሥርዓቶች እንዳሉ ታውቋል። የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔን በተመለከተም፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከኢኮኖሚና ከልማድ፣ የመነጩ የአመለካከት ልዩነቶች እንዳሉ በጥናቱ ታውቋል። ይኸውም በወረዳው በሚደረግ የጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ከቀረርቶውና ከፉከራው ጋር ብዙ ጥይት የመተኮስ ልማድ በመኖሩ፣ ከዋኞች በየመንግስት አካላት "ሰላምና ፀጥታ አደፍራሽ" ተብለው በመወንጀል፣ ጠመንጃቸውን

እንዲነጠቁ፣ በእስርና በገንዘብ እንዲቀጡ፣ እያደረገ ነው። ካህናትም፣ «ገዳይ፣ ዘራፍ እያሉ ሚችን እያሞገሱና እያወደሱ፣ በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ማቅራራትና መፎከር የሟች ነፍስ ሲኦል ትገባ ዘንድ የምስክርነት ቃል መስጠት ነው» በማለት ድርጊቱን ያወግዛሉ። የሚተኮሰው ጥይት ዋጋም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ የሥነ ሥርዓቱ ነባር ይዘት እየተለወጠ እንዲመጣ አድርጎታል። በተጨማሪም በማህበረሰቡ ዘንድ በቀደምቶቹ ትውልዶችና በአሁኑ ትውልድ መካከል ከሚፎከርላቸው ሰዎች ማንነት ጋር የተያያዘ የልማድ ለውጥ አለ። በቀደምቶቹ ትውልዶች በቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት የሚፎከርላቸው አርበኞችና አዳኞች ብቻ ነበሩ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለጠንካራ ገበሬዎችም መፎከር ተለምዷል። በአሁኑ ጊዜ አዳኝ ተብለው የሚፎከርላቸውም እንደ ቀደምቶቹ አዳኞች ዝሆን፣ ጉሽ፣ ቀጭኔ፣ አንበሳና ሌሎችንም ትልልቅና አደገኛ የዱር እንስሳት የገደሉ ብቻ ሳይሆኑ ለምግብነት የሚውሉ የዱር እንስሳትን አድነው የገደሉ ናቸው። በማህበረቡ ጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት ከሚደረገው ቀረርቶና ፉከራ ጋር የሚተኮሰው ጥይት አንድም ማህበረሰቡን በኢኮኖሚ ስለሚበድል አንድም ብዙ ሲተኮስ ባርቆ በማህበረሰቡ ላይ አደጋ እንዳያደርስ በማሰብ በመንግስት አካላት እንዳይተኮስ መከልከሉ ተገቢነት ቢኖረውም፣ በአዋጅ ከመከልከል ይልቅ ማህበረሰቡ የግንዛቤ ለውጥ እንዲያመጣ ማስተማሩ የተሻለ ነው።

## 5.2 ይሁንታ

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ከጥናቱ ግኝት በመነሳትና ለመረጃ ስብሰባ መስክ በወጣሁባቸው ጊዜያት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ላየኋቸው ችግሮች፣ መስሪያ ቤቶቹም ሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ቢያደርጓቸው ይበጃሉ የምላቸው የይሁንታ ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

1. በዚህ ጥናት የመረጃ ስብሰባ ወቅት ስለ ላይ አርማጭሆ ወረዳ ዳራ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ወደ ወረዳው ማስታወቂያና መረጃ ቢሮ ሄጀ ነበር። ይሁን እንጂ ከቢሮው ያገኘኋቸው መረጃዎች በጣም ጥቂትና በወረዳው በሚገኙ ልዩ ልዩ መስሪያ ቤቶች የተጠናቀሩ የስራ ሂደት ሪፖርቶች ናቸው። ቢሮው እነዚህን ሪፖርቶች በአግባቡ ማስቀመጡ ተገቢ ቢሆንም (ግዴታውም ስለሆነ) በየሪፖርቶቹ ውስጥ ወረዳውን በተመለከተ የተቀመጡትን መረጃዎች ለምሳሌ፣ የወረዳውን የህዝብ ብዛት፣ የወረዳውን የቆዳ ስፋትና የወረዳውን አዋሳኝ ወረዳዎች፣

ወዘተ· ስናይ ደግሞ የአንዱ ከሌላው የተለያዩ ናቸው። ይህ ደግሞ በመረጃ ተጠቃሚው ላይ ትልቅ የመረጃ ክፍተት የሚፈጥር በመሆኑ፣ ቢሮው ሪፖርቶችን በመመርመር፣ ለተጠቃሚው አሻሚ በማይሆኑበት መንገድ የማቅረብ ግዴታውን ቢወጣ፣

2. የወረዳው የቀድሞው ወጣቶች፣ ባህልና ስፖርት ቢሮ፣ አሁን ደግሞ የስም ለውጥ አድርጎ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የስራ ሃላፊነቱ በወረዳው በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የሚከናወኑ ባህል ነክ ጉዳዮችን፣ መሰብሰብ፣ ማጥናትና መሰነድ ሆኖ ሳለ፣ የቀድሞው ቢሮ በባህላዊ ስፖርቶችና በባህላዊ ጨዋታዎች ለምሳሌ፣ ገና፣ ገበጣ፣ ትግል ላይ ትኩረት በማድረጉ፣ የስም ለውጥ ካደረገ በኂላ ደግሞ በባለሙያ እጥረት ምክንያት በስነቃሎች ላይ ያደረገው ጥናት እንደሌለ አንዳንድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ነግረውኛል። በመሆኑም ለባህላዊ ስፖርቶች ትኩረት እንደሰጠ ሁሉ ለስነቃሎችም ትኩረት ሰጥቶ፣በሙያው የሰለጠኑ ባለሙያዎችንም ቀጥሮ ቢያሰራ፣

3. በወረዳው የሚደረገው ፉከራና ቀረርቶ ክዋኔ ከጽድቅና ከኩነኔ ጋር ተያይዞ በካህናቱ፣ ከሰላምና ጸጥታ ጋር ተያይዞ በአካባቢው የመንግስት አካላት፣ ከሚተኮሰው ጥይት ዋጋ መጨመር ጋር ተያይዞ ተጽእኖ እየተደረገበት ነው። የልማዱ ለውጥ የግድ ቢሆንም አሁን ባለበት ግጥሙ ቢሰበሰብ፣ ቢጠና እና፣ ቢቀረስ ለአሁኑ ትውልድም ይሁን ለመጭው ትውልድ ለታሪክ መመርምሪያነት ሊጠቅም ይችላልና አሁን ባለበት መጠናቱ ቢቀጥል፣

4. ቀረርቶና ፉከራ ሲከወን በባህርይው ወኔ ቀስቃሽ በመሆኑ አንዳንዱን ሰው በስሜት ብዙ ሊያስተኩሰው ይችላል። ተኩሱ በኢኮኖሚ መበደሉ፣ ጥይት ባርቆ አደጋ ሊያደርስ መቻሉ እንዳለ ሆኖ፣ የመንግስት አካላት አትተኩሱ በማለት ከማወጅና ከመቅጣት በተሻለ መተኮስ የሚያደርሰውን ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማህበረሰቡ በማስተማርና የግንዛቤ ለውጥ እንዲያመጣ ቢጥሩ መልካም ነው ። ምክንያቱም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ለዘመናት አብሮ የቆየን ወግና ልማድ በአንድ ጊዜ በአዋጅ አታድርግ ብሎ መከልከል ድርጊቱ ወዲያውኑ እንዲቆም አያስችልምና ነው።

# ዋቢ ጽሑፎች


ሐረገወይን ድፋባቸው፥ «የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፥ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1974 ዓ.ም።

መዓዛ ተስፋይ፥ «በዓጋመ አውራጃ የቀብር ሥርዓት አፈጻጸምና የለቅሶ ግጥሞች የይዘት ትንተና»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፥ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1982 ዓ.ም።

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፥ <u>ባለን እንወቅበት</u>፥ አዲስ አበባ፥አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥1961 ዓ.ም።

_______፥ <u>ዝክረ ነገር</u> ፥አዲስ አበባ፥አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥1962 ዓ.ም።

ሽመልስ አክሊሉ፥ «የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓትና የግጥሞች ይዘት ትንተና»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፥ ለአርትስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1997 ዓ.ም።

በየነ ለገሠ፥ «በምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ አርጆ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሠብ «ጌረርሳ» (ቀረርቶ) ዓይነቶችና አጫጭር ትንታኔ»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ትምህርት፥ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥1992 ዓ.ም።

ባዩ ቦጋለ (ተርጓሚ)፥ <u>ቅማንት አረማዊ ኦሪታዊ ኢትዮጵያዊ ገበሬ (ፕሮፌሰር ፍሬደሪክ ሲ.ጋምስት እንደፃፈው)</u>፥ አዲስ አበባ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፥ 1993 ዓ.ም።

ታዬ ገብረ ማርያም (አለቃ)፥ <u>የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ</u>፥ አዲስ አበባ፥ ንግድ ማተሚያ ቤት፥ 1955 ዓ.ም።

ነጋ ጌጤ፥ <u>የቅማንት ህዝብ ታሪክ</u>፥ ጎንደር፥ ዳሸን ማተሚያ ቤት፥ 1993 ዓ.ም።

ንጉሴ አክሊሉ፥ «ለጀግኖች ለቅሶ የሚደረደሩ ግጥሞች (ምንጃርና ሸንኮራ) አካባቢ»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ትምህርት፥ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1974 ዓ.ም።

አስመላሽ ወልደ ማርያምና ጽጌረዳ ተክሌ፥ «በትግርኛ የለቅሶ አጋጣሚ የሚተላለፉ መልእክቶች»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓመታዊ ሴሚናር የቀረበ ፥1980 ዓ.ም።

አየለ መሎሬ፥ «የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ሥርዓት»፥አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፥ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1986 ዓ.ም።

ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፥ <u>የዐማርኛ መዝገበ ቃላት</u> ፥አዲስ አበባ፥አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ 1951 ዓ.ም።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ <u>መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ</u>፥ አዲስ አበባ፥አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ 1948 ዓ.ም።

ወርቁ ማንደፍሮ፥ «በሊቦከምከም ወረዳ የለቅሶ ሥነ ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ፥ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1987ዓ.ም።

ወርቁ ደቻሳ፥ «በወለጋ ክፍለ ሃገር፣ በሆሮ ጉድሩ አውራጃ የኦሮሞ ብሔረሠብ ቀረርቶ ግጥሞች ትንተና»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፥ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1978 ዓ.ም።

ወርቃየሁ አረጋ፥ «የአዊ ህብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርዓት) እና የአውኚ ዚንዚምኚ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና»፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፥ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፥ 1995 ዓ.ም።

ዓለማሁ ሞገስ፥ «ከሰፊው ሕዝብ አጫጭር ግጥሞች» ፥ለትውፊት ሴሚናር የቀረበ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፥ 1973 ዓ.ም (ያልታተመ)።

ዘላለም ኢዮብ÷ «በጎፋ ብሔረሰብ ባህላዊ ለቅሶ (ዬሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነ ግጥማዊ ገጽታ»÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት÷ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ÷ 1995 ዓ.ም።

የላይ አርማጭሆ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ቢሮ÷ "የ2002 ዓ.ም የ2ኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት»÷ ትክል ድንጋይ÷2002 ዓ.ም (ያልታተመ)።

የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ÷ "የ2000 በጀት ዓመት ዓመታዊ ስታትስቲካዊ መፅሄት"÷ ጎንደር÷ጎንደር ማተሚያ ድርጅት÷ ጥር 2001 ዓ.ም።

የኪነቃልና ስነ ጽሑፍ ጥናት ቡድን÷ <u>አጭር የኪነቃል አጠናን መመሪያ መነሻ ሀሳብ</u> ÷አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር÷ 1973 ዓ.ም (ያልታተመ)።

ያቆብ ገብረ ኪዳን÷ «የጎንደር ቀረርቶና ፉከራ ይዘትና ክፍለ ሃገራዊ አሻራ»÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት÷ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ÷ 1979 ዓ.ም።

ደስታ ተክለ ወልድ÷ <u>ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት</u>÷ አዲስ አበባ÷ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት÷1962 ዓ.ም።

ድጋፌ ፈይሳ÷ «የሲዳማ ብሔረሠብ የለቅሶ ስነ ስርዓት»÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት÷ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ÷ 1975 ዓ.ም።

ጌጡ ታደሠ÷ «ክዋኔ በጎንደር ከተማ የለቅሶ ስነ ስርዓት»÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት÷ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ÷ 1986 ዓ.ም።

ጥላሁን ኢቢዶ÷ «የጌዴኦ ኅብረተሰብ የልቅሶ ሥርዓት»÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት÷ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ÷ 1982 ዓ.ም።

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፦ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች ስብስብ

### 1.1 የቀረርቶ ግጥሞች

1. እንግዲህ ጠመንጃ ጌታሽን ንገሪኝ
   እንግዲህ መሳሪያ ጌታሽን ንገሪኝ
   ተሸካሚሽ ሁሉ እያንገራገረኝ

2. ማይረባ ጌታና የሙጀሌ ቁስል
   እሹኝ እሹኝ ይላል ሚጠቅምይመስል

3. ደህና ጐበዝና ነብር አንድ ናቸው
   ደርሰው ሰው አይነኩም ካልደረሱባቸው

4. ኧረ ጀግናው ታጠቅ ለሁሉም ይበጃል
   ከዋለ ካደረ ጠላት ይደራጃል

5. ላሞችን ንዳቸው ሳር ወዳለው
   <u>በሮችን</u> ንዳቸው እርሻ ወዳለው (በሬዎች ለማለት)
   ማልደህ ጥመድና በጊዜ ፍታቸው
   የሰው አገር በሮች እራትም የላቸው

6. ንዳው ሳሙን አቧራው ይነሳ
   ይመጣ የለም ወይ አውራው እያገሳ

7. ወይፈኑን ቢጠምዱት አይዝም <u>ጥጉን</u> (ዳገቱን)
   <u>ዳብሩን</u> ቢጠምዱት አይዝም ጥጉን (የተንኮላሸ ትልቅ በሬ)
   ከመንጋው ግባና ምረጥ አውራውን

8. መገኔ መገኔ ትላለች ጋጋኔ
   የቸገረ ነገር ቢያገኛት እንደእኔ

9. ደመና ሲደምን ይወረዛል ገደል
   ይዘገያል እንጂ መች ይረሳል በደል

10. ዋርካው ዘሞ ጤፉ ተቆላሞ

ወንድ ልጅ አይቀርም እንዲህ ታሞ ታሞ

11.ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደአባቱ

ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደ እናቱ

12.አገሬ አርማጭሆ ወልቃይት ጠገዴ

ማረሻው ምንሽር መጕልጐያው ጓንዴ

13. በሬዬን ጠመንጃ ላሚቱን ጥይት

ጊደሬንም ቋንጣ ደሮዬን ክብሪት

እንግዲህስ በቃኝ ልውጣ ልሸፍት

14. ኧረ ጥራኝ ጫካው ኧረ ጥራኝ ዱሩ

ለአንተም ይሻልሃል ብቻ ከማደሩ

15. አንተ ያገሬ ዋርካ ያገሬ ውልክፋ

አታስጠጋኝም ወይ አንድ ዓመት ብከፋ

16.ገዳይ ገዳይ ሲል ነው የወንድ ወንድነቱ

ሴትም ትገድላለች ከረጋ መሬቱ

17. ጓሮንቻ አፋፉ ላይ ነብር አስሬያለሁ

አርማጭሆ አፋፍ ላይ ነብር አስሬያለሁ

ቆርጦ ከሄደማ እንዴት አደርጋለሁ

18.ምኑ ሞኝ ነው ምኑ ጅል ነው

ሲሰድቡት ዝም ያለ ሲመቱትም ያው ነው

19. አይ አወላውሌ እያወላወለ

ጠላቱን ሰደደው ዛሬ ነገ እያለ

1·2 የፉከራ ግጥሞች

1.2·1 የሚችን ዘማችነትና የዘመቻ ቦታ የሚገልጹ የፉከራ ግጥሞች

1. አየ ጉድየ አየ ጉድየ

ያ ጀግና ጉበዝ ከዓለም ተለየ

2. ጀግናው አርበኛ

ጠላቱን ሳይጥል እንቅልፍ አይተኛ

3. ማን ለማን ፈርቶ ማን ለማን አንሶ

ጉድብ አስነቃይ ደገላ ጥሶ (ጥሻ፣ ዳዋ)

ሳለ ለኩራት ሲሞት ለልቅሶ

4. አንቺ ክላሽ ለእግዜር ኑረሻል

ያ ጀግና ጎበዝ አገልግሎሻል

ውሃ ሲጠማሽ ደም ያጠጣሻል

5. በላይ ቢመጡ በላይ ቆያቸው

በታች ቢመጡ በታች ቆያቸው

እንደ ደመራው ባንድ አቆማቸው

እንደ ብርሌ ከሰከሳቸው

እንደ ሸክላ ሰባበራቸው

6. ወንዙ ወዲያ ማዶ ከፈፋው ላይ (ትንሽ ወንዝ)

ጠላት ያሸካካል አትሠማም ወይ

7. አይጠረጠርም እነሱ ናቸው

ሽንጥህን ገትር ቁሙ በላቸው

8. ጠላት አይወድም ጀርባ ሲያሳዩት

ግንባር ግንባሩን ዓይን ዓይኑን በሉት

9. ጦር ክተት ብሎ ሲጮህ ጥሩንባ

ጀግና ሲገጥም ፈሪ ሲገባ

አንበሳው ወንዱ መሃሉን ገባ

10. መሀሉን ገብቶ አረገው ወና (ኦና ለማለት)

ምስጥ እንደበላው እንደብሳና

11. እናንተ ሆየ እስኪ ሰው ጥሩ

ልበ ደንዳና ሃሞተ ኩሩ

12. ይተኩስ ነበር በጣም አጊጦ
ሱፍ የመሠለ ደም ተረግጦ

13. ተመልከት ብሎ ቢተኩሰው
ጅብ የገመጠው አስመስለው

14. ገዳይ ሰኞ ማለዳ
ጥጃው ተራክቦ ላሙ ሲነዳ (ላም ታልቦ እንደተጠናቀቀ ለማለት)

15. ገዳይ ማክሰኞ ደግሞም ሮብ
አየር በሰማይ ሲያረበርብ

16. ሮብ ተጉዞ ገዳይ ሃሙስ
ሲያጭደው ዋለ እንደ አውራ ገብስ

17. አርብ ተጉዞ ገዳይ ቅዳሜ
ወትሮም ጀግና ሰው የለው እድሜ

18. በሰማይ አየር ሲበርበት
በመሬት ታንክ ሲሮጥበት
መድፍና አዳፍኔ ሲነድበት
ጀግናውን ሁሉ በላው መሬት

19. ጀግናው አጅሬ የጥቃት መውጫ
አይታወቅም የጠላት መምጫ

20. የሰውዬ ልጅ ባለጎፈሬ
ጠምዶ ይነዳል ሰው እንደበሬ

21. ያን አድሃሪ ያን ኩፍኝ ፊት
ስቦ ያቀርባል ከመስሪያ ቤት

22. ወረዳ አይፈራ አውራጃ አይፈራ (የወረዳና የአውራጃ አስተዳዳሪዎችን ለማለት ነው)
እንደ አባይ ባህር ልቡ የሞላ

23. ዘራፍ አጅሬ በዚያ ወረደ
ክላሹ እንደ እሳት እየነደደ

24. ከክላሹ ጋር የተማከረው
ሰርክ በደም ሽማ የተነከረው

25. ዘራፍ አጅሬ ይህ ነው እኮ
ይገባለታል ወንድ ተሳቆ

26. ወንድ እንደ ፍየል የሮጠለት
መሬት እንደሰው የሳቀለት
ይህ ነው ጀግና የወንድ አባት

27. ኧረ አርማጭሆ ይምጣ ጠገዴ
ሰዎች ቀጫጭን ልባቸው ዳንዴ (ጠንካራ፣ ልበ ሙሉ፣ ደፋር)

28. ኧረ ጠገዴ ይምጣ ጠለምት
እንኳንስ ሰምቶ የጥይት ድምጥ
ቡና ይሸታል እንኳንስ ባሩድ

29. ጀግናው ለወኔው ጠመንጃ ገዝቶ
ባምስት በስድስት በሰባት መቶ

30. ለምን አኖረው ቤቱ ቆልፎ
ያስተዛዝበናል ይኽ ቀን አልፎ

31. ታች አርማጭሆ ላይ አርማጭሆ
ይደባልቃል ጀግና እንደ ቡሆ (ሊጥ)

32. ዘራፍ የኢትዮጵያ ጀግና
ጦር ሲጥመለመል እንደደመና
መሃሉን ገብቶ አረገው ወና

33. ውረድ እንውረድ በቁልቁለቱ
የሞተው ይሙት ታልቅስ እናቱ

34. በርሃ ወርዶ ጥይት ዘርዛሪ
የሰው ኮርቻ ጦም አሳዳሪ

35. ታምባ ላይ ወጥተው ጸሐይ ሲሞቁ
ደረሰባቸው ወንዱ መብረቁ

36. ወንዱ ነውጠኛ
የማያስቀምጥ የማያስተኛ
የሚወዘውዝ እንደ ቁመኛ

37. ጀግና ነው ማለት ይሸ ነው ለካ
ባለ<u>ጓንዴ</u> ነው ባለ <u>አማሪካ</u> (የጠመንጃ ስሞች)

38. አይ ዘራፍ ጀግናው ወታደር
ለመብል ቀርቶ ለሞት ሲታደል

39. ጀግና ነው ማለት እንዴት ያለ ነው
ከጠባብ ቦታ የተፈተነ ነው

40. የተፈተነው የታየው ጉዱ
<u>ብረት</u> ማራኪ ከነ ጉድጓዱ (ጠመንጃ ከነ ጥይቱ ለማለት ነው)

41. እንጉድ እንጉድ ባይ እንደ <u>ጨው</u> ደቋሽ (በጐንደሬ ዘዬ ጨው በርበሬ ማለት ነው)
ተመልከት ብሎ በግራው ተኳሽ

42. ውጣ በግራ ውረድ በስተቀኝ
ገድሎ መፈከር እንዴት ናፈቀኝ

43. ገዳይ አሁንም ገዳይ
የፈረሰ ጦር ዙሮ አደላዳይ

44. ዘማች በልጅነቱ
ጥጃ ጠብቋል ስትል እናቱ

45. ውረድ እንውረድ ይለይልነ
እንዲያው <u>ተጃነን</u> ሙያም የለነ (ተፈራርተን፣ ተጠባብቀን)

46. አየር በሰማይ ሲያንዣብብበት
ታንኩ በመሬት ሲሮጥበት
አይ ያለው ደስታ ያለው ኩራት

47. የኮራ ጐበዝ የተንጠራራ
በአባቱ ጋሻ ልጁ ሚጠራ

48. ጀግና ነው ማለት እንዴት ያለ ነው
ከአደባባይ ወጥቶ የዋለ ሰው ነው

49. ውጣ አደባባይ አገር ይወቅህ
ጀግናው ይኸ ነው ብሎ ያድንቅህ

50. ዘራፍ አጅሬ ሆዬ
እንደአራስ ነብር ጠቡ የለዬ

51. ገዳይ አዜከው ገዳይ ካምፈንታ
በሃይማኖቱ ማተብ ሳይፈታ

52. ጠላት ቢመጣ ወሰን ሊጥስ
ገስግሶ ደራሽ እንደ አውራሪስ

53. ታማኝ ለአገሩ ለሚወዳት
እንኳንስ ገፍቶ ለሚደፍራት

54. ሃያል ነው ቁጣው ለሚመኛት
ለጠላት ምጥ ነው ለወገን ኩራት
አፈጣጠኑ እንደ ጭልፊት

55. በሰላም ጊዜ አርሶ እየበላ
በመከራም ጊዜ ለአገሩ ጥላ

56. የጭቃ እሾህ ነው የማይታይ
ድንገት መትቶ ሲሠጥ ለስቃይ

57. ሌሊት ተጉዞ እግሩ እስቲነቃ
ለጠላት ሆነ የእሳት ላንቃ

58. ወንዱ አባጭላት ወንዱ አባ ነሽር

እንደ አያል ደብተራ ጥፈት የሚሽር (ድግምት)

59. ________ እለፍ በበሩ

እኒያ ጠላቶች እንዳይወበሩ (እንዳይጠነክሩ፣ ማናለብኝ እንዳይሉ)

60. አንክተውና በዚያው ይመለስ

አይቀርምና ተሰርቶ መፍረስ

61. ዘራፍ ተቀምጦ ዘራፍ ሲነሳ

የሌሊት አውሬ የቀን ጃውሳ

62. ወንድ ነበረ ወንድ ጋሞራ

እየገደለ ሰጠው ላሞራ

63. አልገዛም ባይ ሰውየው ለሰው

በደረቅ እርሳስ ጉኑን ሳላርሰው

ፈርሱን ከመሬት ሳልነሰንሰው

64. አየር በሰማይ ያንዣበበ ዕለት

በአጋሜ ጥይት ሲታጠር መሬት

65. ምን ይችል ሰማይ ምን ትችል መሬት

አለነ ብለው ሚኮሩበት

የ--- ልጅ መጣ ትዕቢት

66. ልቡ ድፍን ነው እንደ ፈጣሪ

ዘራፍ አጅሬን ማናለው ፈሪ

67. ሜጀር ጀኔራል ኮከብ ማራኪ

መድፍ ታከኛ ከአፈር ዘናቂ

68. አንበሳው ጋሻ ጀግናው ጋላገር

የታጠረ ነው በብረት ማገር

69. ከች ዓይነት ውሀ ከርከር ዋላጅ
ተጠቅቶ አያውቅም ማጥቃት ነው እንጂ

70. እሳቱን እሳት እሳት ሲወልደው
እፍ እፍ እያለ እያናደደው

71. ካላጋጋሙት እንደግራር ፍም
የአባቱ ዘራፍ ለልጅ አይተርፍም

72. ከቤቱ በታች ከአባቱ ክልክል (ለግጦሽ የማይውል፣ የተጠበቀ መሬት)
በጥቁር ብረት የሚያንቀለቅል

73. እጥፍጥፍ ያለው እንደ ኩታ ልብስ
አተኳኮሱ አንጀት የሚያርስ

74. አይ አተኳኮስ አይ አገዳደል
እንደ ወስከምቢያ መሃሉን መንደል (ከአክርማ የሚሰራ ስፌት)

75. ለዝና ብሎ ለመሞናደል
እየገደለ ሰደደው ገደል

76. ገዳይ በጓንዴ በአፈ ድምድሙ
የእመጫት አልጋ ሲመስል ደሙ

77. ተመልከት ብሎ ቢለው ደረቱን
አዝለከለከው አንጀት ጉበቱን

78. ለፉከራማ ለውስዋሶው
መቸ ያሳፍራል ሱሪ ያለው ሰው

79. ሱሪ ቢኳችሁ ጨርቅ ነው ወይ
ሱሪ ቢኳችሁ ሳልባጅ ነው ወይ

80. የታጠቀ ነው ከልቡ ላይ
ደራርቦ ጣይ ነው ሰው በሰው ላይ

81. የ-- ልጅ የቀትር እሳት
የአባቱን አገር አያስቀምሳት

82. አጥባቂ አራቂ እንደ ሰንሰለት
ተጠምጣሚ ነው እንደ ቀለበት

83. ወንድ ጋሞራ የደንጊያ መዝጊያ
የማይከፈት የማይዘጋ

84. ማነው ሲሏችሁ --- ነው በሉ
እንደ ጊዮርጊስ እጀ ፈጣኑ

85. እንደ ጊዮርጊስ እንደ አምላክ ቁጣ
አምስት አምስቱ በግንባር ይምጣ

86. ከላይ ደረቱን ከታች ጉልበቱን
አንክቶ አንክቶ ሰደደው ቤቱን

87. አልተመለስም አልዞረም ፊቱን
እንደ ዘረጋው ቀረ ጉልበቱን
አይ ባልወለድሽኝ አላት እናቱን

88. እንኳን እናቱን ቢጣራ ሌላ
ነፍስ ከሄደች አትመጣም ገና

89. ነፍስ ከሄደች ከገሠገሠች
እናቴ ቢሏት አልተመለሠች

90. ወንድ ነበር የወንዶች ወንድ
ቆርጠው ካልሄዱ ፍራት አይገድ

91. ካልዳፉት እንደ ውሀ ሙላት
ትክ ብለው ቢያዩት አይሞትም ጠላት

92. ክላሽ ሲንፈቀፈቅ መትረየስ ሲያጓራ
ልብ አይታመንም እንኳን ባልንጀራ

93. ጥይት ሲሹለከለክ በሰውየው ገላ
ቀዩ ሰው ሲጠቁር ጥቁሩ ሲቀላ

94. ባልንጀራው ወድቆ ደገላ ሲያለብሰው (ጥሻ)
ተራምዶት አለፈ እንደ ማያውቀው ሰው

95. ዱብዱብ ባይ እንደ በረዶ
የሚተናነቅ ጉድብ ተራምዶ

96. አትናገሩት ---- ይናገር
ቆደበኛ ነው አይችልም ነገር (አመጸኛ፣ ትዕቢተኛ)

97. ጀግናው የ-- ልጅ መጣ መሰለኝ
የእህል ሰውና ጀግና ሰው ተለይ

98. ሲያባርረው ውሎ ሲያንከለክለው
እንደ ጉማሬ ከባህር ዶለው

99. ወንዱ የባህር አዞ
መቸ ይወቀሳል እጁን ተይዞ

100. የማደር ወንድም የማደር ገፊ
ቀኝ እጁን ይዞ ይላል የጥፊ

101. አይመጣም ሲሉ የመጣ እንደሆን
አለመደንገጥ ከልብ መሆን

102. ኧረ ጓሮንቻ እነማን ነበሩ
ነበረ ______ የጦር አጋሩ
ሄዶ ይዋጋል ለእናት አገሩ

103. ኮልኩል በፈረስ ውረድ በእግር (ትዕቢተኛ አመጸኛ)
የነፍጥ ጌታ የአባ ደክር

104. በወጣው ወጥቶ በገባው ገብቶ
ይዞት ይመጣል እጁን ጕ ትቶ

105. ይምጣ ጃኒፈንቀራ

ይከራከራል ከጠላት ጋራ

106. ዘማች ጐንደር

ለዚህ ቀን ብሎ ለማስፈከር

107. ዘማች በለሳ

እህል ሳይቀምስ ሳይበላ ምሳ

108. ገዳይ ጐንደር ዘማች ወለቃ

ብዙ ገደለ ብዙ ሻለቃ

109. ባለክላሽ ነው ባለጅምስሪ (ጂ ኤም ስሪ ለማለት)

በልጅነቱ የልቡን ሰሪ

110. በረጅም ሲል ባጭር አስቀሪ

ለሃይማኖቱ ተከራካሪ

111. ገዳይ ዘራጌ ከቤቱ በታች

እናቱ እያየች ሚስቱ እያቦካች

መጫኛ ሚያህል አንጀት አስጐታች

112. ጥጃ ጠብቋል ስትል እናቱ

መብረቅ ሆነበት ለሠራዊቱ

113. አየ ጉድዬ

ሰው አያምንም ዘልቆ ካላየ

114. ከተነካኩማ ከተጫጫሩ

የጠፋ ይጥፋ ይቅር አገሩ

1.2.2 የሚችን አዳኝነት የሚገልጹ የፉከራ ግጥሞች

115. ሲሄድ ነበረ ጋራ ለጋራ

የተማከረው ከክላሹ ጋራ

116. ሁል ጊዜ ስጋ ዱለት ሚበላ
አውራ ሚዳቋ አውራ ድኩላ

117. ገዳይ ድኩላ አለዚያ ሰላ
ማልዶ ሚያደርሰው ለቁርስ ለምሳ

118. የዚያች አሽከር ባል ያንገተ ቅጥል (ያ ባለረጅም አንገት)
ሳይገድል አይመጣም ሳያንጠለጥል

119. የዚያች አሽከር ባል የቀመጢና (ወጣት፣ ልጅ)
ሀምሳውን ገድሎ መጣ በጤና

## 1.2.3 የሚችን የዘር የበላይነት የሚገልጹ የፉከራ ግጥሞች

120. የወንዶች ወንድም የባለ ሱሪ
እንግት አስመላሽ ወንዝ አሳፋሪ (ትጥቅ)

121. የወንዶች ወንድም የተኳሾች
ተመልከት ብሎ ይመታል ወርች

122. ጥርሱ እንደሚዶ ያለው ዘርዘር
የ--- ልጅ የደህና ሰው ዘር

123. የ--- ልጅ አገር ያወቀው
ሌባ ነው ተብሎ ያልተጠየቀው

124. የሴትዮ ልጅ የሴት ወይዘሮ
ከጠላቱ ፊት ይተፋል ዙሮ

125. የሴትዮ ልጅ የእመቤቲቱ
አባርሮ ደፊ በጭንቅላቱ

126. የሴትዮ ባል የመሠናዶ (ሁሌም ዝግጁ)
በልጅነቱ ተዋግቶ ለምዶ

127. በአራቱ ማዕዘን የሚወለደው
እንደስላሴ የሚታደገው

128. ሰው ያለዘሩ አይወለድም
ሾፌር ከሞተ መኪና አይሄድም

129. የ_____ ልጅ የባለ ጠጁ
አይበለጥም ታለ ወዳጁ

130. የ_____ወንድም የዚያ ወታደር
የልቡን ሠርቶ ኖሯል በዚህ አገር

131. የ_____ ወንድም የዚያ ደፈርሻ ("ፈ" አይጠብቅም። አጭር፣ ወፍራምና ደረታም)
ጠብ ከመጣማ እንዴት ነሽ ፍርሻ (ብጥብጥ፣ ግጭት፣ ግርግር)

132. ወንዱ የወንዶች ወገን
መስሎ ዘለቀ የእሳት ፈገገን (ፍም)

133. የጀግና ዘር ነው የእሳት አለሎ
ፍቅሩን እንጂ ጠቡን ማንችሎ

134. በእናቱ እመቤት በአባቱ ጌታ
እልፍኝ ያደገው ሳይንገላታ

135. በሰባት ቤቱ የለው ደንቆሮ
ብረቱ ክላሽ ቤቱ ቆርቆሮ

136. የወንዶች ወገን የወንዶች ልጅ
ሚበላው ጮማ ሚጠጣው ጠጅ

137. የ_____ን እናት ማን ይነካታል
ትንሽ ትልቁ አንቱ ይላታል

1.2.4 የሟችን ሙያ፣ ንብረትና ልግስና የሚገልጹ የፉከራ ግጥሞች

138. የአርማጭሆ ልጅ የተደራጀው
መኖሪያ ቤቱ መቶ የፈጀው (ቤቱ የተሠራበት የቆርቆሮ ብዛት)

139. ይፈከርለት በዓይነት በዓይነቱ
በላም በበሬው በርስት በጉልቱ

140. ላሙ ነጫጭ ነው ጊደሩ እምብርታም
የሰውዬ ልጅ ጥንት ነው ሃብታም

141. የሰውዬ ልጅ የባለጸጋ
ቤቱ አይጐድልበት ክረምት ተበጋ

142. ሳቅ ሳቅ የሚለው ዘመድ ሲያወጋ
የሚተኛውም ከመልካም አልጋ

143. እንዴት ዋላችሁ ከአጅሬ ቤት
ጠላ በበርሜል ሚሾምበት

144. ጋኑ በማቶት ማወርድበት (ጋን ከነጠላው ሞልቶ ወደሚጠጣበት ቦታ መውሰጃ ገመድ፣ የእጅ መያዣ)
እንጀራው በእርጐ ሚበላበት

145. እንኳን ሲቆጣ ሲናገር ገና
በሬው ክንፍ አለው እንደ ርቡላ (አይሮፕላን ለማለት)

146. ታረሱም ወዲያ ተርሻው ተዋሉ
ማርያም መቀነት ሲመስል ሾሩ (ቀስተ ደመና)

147. ጎሹን በቀኝ ዘውዴን በግራ (የበሬ ስሞች)
ሰርዶ አራጋፊ አንደጨንራ

148. ጀግናው ገበሬ
ያመርት ነበር ልምና ጥሬ

149. እያለ ምሽቱን ፍጭ ጋግሪ
ሲመጣ ዘመድ እንድትኮሪ

150. ይህን ይመስላል ያጅሬ መላ
አይሠርቅ አይቀጥፍ ሰርቶ ሚበላ

151. እናትና ልጅ የታለበለት
አባትና ልጅ የታረሰለት

152. እንግዳው በልቶ የጠገበለት
በቅሎው ከጓዳ የሚያሽካካለት

153. ዘራፍ አጅሬ የአጅሬ ልጅ
ይህ ነው ገበሬ የእግዜር ወዳጅ

154. ባለ በቅሎ ነው ባለ ፈረስ
መቶ ጫን እህል ጉንደር ሚያደርስ (የእህል መስፈሪያ፣ አምስት ኩንታል አንድ ጫን ይባላል)

155. በአስር አህያ ቢጀረጉደው
አባ ሽኳርን ብድር ሰደደው (ነጋዴ)

156. መሃል ጋላገር ጌሾ ተከለ
ኧረ አርማጭሆ ቡና ተከለ

157. ሽቃጩ ሁሉ እጁ ቆሠለ (ነጋዴ)
እየመዘነ እየሰቀለ

158. አራሽ ነበረ እልም ታለው ጭንጫ (ዓለት የተነጠፈበት መሬት)
እህልና መሬት ሲማታ ማጫ (አዲስ ተጋቢዎች ከየ ቤተሠቦቻቸው ያመጧቸውን ከብቶች በመቀላቀል ንብረትህ ንብረቴ ነው የሚባባሉበት ልማድ ነው)

159. ቤቱ ተመንገድ ተዲቡ በታች (ቃሉ ዲብ ነው፤ ከዳገት በታች ማለት ነው)
ብሉ ጠጡ ባይ እንግዳ ጉታች (ገላጋይ፣ ብሉ ጠጡ በሞቴ ባይ)

160. እረሱ በእርሻ አትመለሱ
ቡና ሲፈላ ችግር ነው ቁርሱ

161. ያረሰ ጉበዝ እርፍ የነቀነቀ
ወፍጮው እንዳጉራ መስከረም ዘለቀ

162. አርሳለሁ ለእርሻ አልማረርም
ችግር በወንጭፍ አይባረርም

163. ጀግናው ባረሰው
አይራመድም ሙጀሌያሙ ሰው

164. የወንዶች ወገን የባለ ሱሪ
ባለ መሰላል ጉተራ ሰሪ
ለተቸገረው ዝቆ አበዳሪ

165. ከገበሬው ቤት ከወለላው
ጠላና እርጎ ነው የሚገኘው

166. ማጀቱም ሰፊ የጠላው መምጫ
መቅጃው <u>በራድ</u> ነው መጠጫው ዋንጫ (ማንቆርቆርያ)

167. ከገበሬው ቤት እንዴት ዋላችሁ
የእግዜር እንግዶች መጣንላችሁ
አንቺ ውጭና ግቡ በያቸው

168. አንጥፈሽ ግዜ አስቀምጫቸው
ወጥተው ሲሄዱ ዝም አትበያቸው
ብድርም እንደሁ ዝቀሽ ስጫቸው
ብድሩንም አትጠይቂያቸው
የሞትን ለታ ሚያለቅሱ ናቸው

169. አወይ ሙያችን አወይ እርሻችን
ጉተራው ቁሟል ከደጃፋችን
ብድር አይሄዱም እህቶቻችን
ጅል <u>አይሠራም</u> ከመሶባችን (ቃሉ ይጠብቃል፣ ከጅል ጋር ማዕድ አንቀርብም)

170. በዚህ ዘማች ነው በዚህ ገበሬ
በሁለት እጁ ሰሪ እንደ ሸማኔ

171. በሁለት ወፍጮ ነው ቡና ሚያስከካ
ያለው አይመስልም <u>አራት ፈረንካ</u> (አስር ሳንቲም)

172. ጀግናው ገበሬ የስደድ እሳት
የእባብ ልብ እንጂ የለውም አንጀት

1.2.5 የሚችን መልክና ጸባይ የሚገልጹ የፉከራ ግጥሞች

173. ይኼ ነው ጀግና የወንዶች አባት
የወንዶች ወገን የወንዶች ልጅ
ሚበላው ጮማ ሚጠጣው ጠጅ
ስራው ያመረ መልኩ ፈረንጅ

174. ከጅል ሰው ጋራ የማይስማማው
በልቡ ኩራት እየተሰማው

175. አጭር ቁመቱ ሰፊ ደረቱ
አባርሮ ደፋው በቁልቁለቱ

176. ግጥምጥም ያለው እንደ ካንዱራ
እንደ መስኪቶ ዓይኑ የጠራ (የጠመንጃ ስም)

177. አጭር ነው ብለው ሰውን አይንቁም
የቆመ ድንጋይ አይነቀንቁም

178. ጅማተ ብርቱ እንደ አውስቴራ
በአፉ ተናግሮ በእጁ ሚሠራ

1.2.6 በማህበረሰቡ ዘንድ የሚወገዙ ተግባራትን (እንደ ውሸት፣ ስንፍና፣ ፍርሃትና ስርቆት የመሳሰለውን) የሚገስጹ የፉከራ ግጥሞች

179. ያልገደለውን ገደልኩ እያለ
ያልተኮሰውን ተኮስኩ እያለ
ያልዘመተውን ዘመትኩ እያለ
ዋንጫ ጨብጦ የሚውል አለ

180. የጠላ ጨላጭ የመንደር አውራ
ከቁም ነገር ላይ አንድም ላይሠራ

181. ገዳይ እምትሉ እነማናችሁ
ዘራፍ እምትሉ እነማናችሁ
ጀግና ሲሸበር መቼ ነበራችሁ

182. ኧረ እጀ ጠባብን ሁሉ ለበሳት
ኧረ ሱሪን ሁሉ አጠለቃት
ኧረ ክላሽን ሁሉ አነገታት
ኧረ ጥይትን ሁሉ ታጠቃት
ቀውጢ ቀን አለ የሚያስወልቃት

183. የደጋው ጉበዝ ቆላ ሲዘምት
የቆላው ጉበዝ ደጋ ሲዘምት

184. ቆላና ደጋ ሲደባለቅ
አለ አንዳንድ ጅል ስሙን ማያውቅ

185. ጉም ጉም ሲል ቦንብ እንደ መብረቅ
ግማሹ ሲፈክር ግማሹ ሲወድቅ
ብዙ ፈሪ አለ ስሙን የማያውቅ

186. ፈሪና ደፋር ቢመዛዘኑ
ፈሪ በለጠ ከነ ቅዘኑ

187. የክላሽ ቁንጮ ጭራ ሲመስል
ፈሪ ተጨንቆ ጉንበስ ቀና ሲል
አሻግሮ መታው ከጉድቡ ስር

188. አለ ጩርጩር የዛርጢ ሆዱ (ፈሪ)
በገምቦ ጠላ እንደሚቀዱ

189. እምቢ አሻፈረኝ ጅል አይውደደኝ
ሲሳሳቁበት እየነደደኝ

190. ከጅል ሰው ወገን እንዳትዋለዱ
እንኳን ጭራሮው አይሞቅም ግንዱ

191. አህያ ጭነው ደጋ ቢወጡ
አህያ ጭነው ቆላ ቢወርዱ
ለሙቅ አይበቃም እንኳን ለሆዱ (አጥሚት)

192. ሲያርሙ አያርም ሲዘሩ አይዘራ

ይገመግማል የሰው አዝመራ

193. መቼ ያኮራል የሌባ ጋሻ

አስፈቱኝ ይላል ታስሮ እንደ ውሻ

194. ታስሮ እንደውሻ ከመወቀስ

መሞት ይሻላል አፈር መልበስ

195. ከሌባውማ ከዚያ ቆማጣ

በየጉሽጉሻው ይገኛል ቋንጣ

196· ከሌባ ጋራ ፍንጥር የጠጣ (የገበያ ውል አዋዋዮች የሚከፈላቸው ዋጋ፤ ብዙ ጊዜ የተለመደው መጠጥ ነው)

ዓመት ታሠረ ሺህ ብር ተቀጣ

ሺህ ብር ተቀጥቶ ጐንደር ላይ ወጣ

196. ጐንደር ላይ ወጥቶ ባታ ወረደ (ጐንደር ከተማ ውስጥ የሚገኝ ወህኒ ቤት)

ሰባት ትውልዱን እያዋረደ

197. የሌባን እናት ማን ይወዳታል

ፖሊስ በጫማ ይረገጣታል

## 1.2·7 በክዋኔ ወቅት ለገበሬ ገዳይ እያሉ ሲፎክሩ "የለም ገበሬ እንጂ ገዳይ አይደለም" ብለው የሚገጥሟቸው የፉከራ ግጥሞች

198. ያልገደለውን ገደለ አትበሉ

ያልዘመተውን ዘመተ አትበሉ

የሚጠድቅ ነፍስ አታስኮንኑ

ይልቅስ በሉ

የላሞች ጌታ የነድንቡሉ

199. ገዳይ አትበው ያልገደለውን

ዘራፍ አትበለው ያልዘረፈውን

ስጠው ጅራፉን የለመደውን

200. ያልገደለውን ገደለ ምነው

ያልዘረፈውን ዘረፈ ምነው

እኔ ምፈክር በበሬዎቼ ነው

# አባሪ ሁለት፦ የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

## 2.1 የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | የአቀባይ ስም | እድሜ | ፆታ | ሙያ | ቀበሌ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ | ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ተሰራ አምባው | 68 | ወንድ | ነጋዴ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 7/2002 | ቤታቸው | 10:27-12:55 |
| 2 | አቶ ደርበው ፈረደ | 70 | ወንድ | አርሶ አደር | ክርክር ባለእግዚአብሔር | መጋቢት 5/2002 | ቤተ ክርስቲያን የሰንበቴ ማህበር ሲጠጡ | 3:23-4:31 |
| 3 | ወይዘሮ አሰለፍ ገበየ | 60 | ሴት | የቤት እመቤት | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 5/2002 | ቤተ ክርስቲያን የሰንበቴ ማህበር ሲጠጡ | 4:35-5:42 |
| 4 | አቶ ብርሃን አዱኛ | 58 | ወንድ | አርሶ አደር | ገምበጅ | መጋቢት 5/2002 | ቤተ ክርስቲያን የሰንበቴ ማህበር ሲጠጡ | 5:45-6:57 |
| 5 | ሊቀ ካህናት መልአከ ገነት አበበ | 46 | ወንድ | የወረዳው ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሐላፊ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 19/2002 | ቢሮዋቸው | 3:25-5:20 |
| 6 | እማሆይ ጥሩ ዓይነት ሺበሺ | 92 | ሴት | መነኩሲት | ጅሣ | መጋቢት 19/2002 | ጸበል መጠመቂያ ቦታ | 1:47-2:32 ማታ |
| 7 | መሪጌታ አራጌ ባዩ | 49 | ወንድ | የወረዳው ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጸሐፊ | አንኮድብ ይኖሩ የነበሩና ከ1999 ዓ.ም ወዲህ ትክል ድንጋይ የሚኖሩ | መጋቢት 3/2002 | ቢሮዋቸው | 10:13-11:47 |
| 8 | አቶ ብርቁ ሚካኤል | 28 | ወንድ | አርሶ አደር | አዲስጌ | መጋቢት 3/2002 | ቤታቸው | 7:20-8:43 |
| 9 | አቶ ጌታ ጣፈጠ | 38 | ወንድ | የሂሳብ ሰራተኛ (ፎካሪም ናቸው) | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 11 እና 19/2002 | ሆቴል | 10:45-12:14 እና 5:57-6:41 |
| 10 | አቶ ሙሌ አውላቸው | 44 | ወንድ | አርሶ አደር (ፎካሪም ናቸው) | አዲስጌ | መጋቢት 19/2002 | ሆቴል | 6:45-7:42 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | አቶ አወቀ ታከለ | 52 | ወንድ | አርሶ አደር (ፎካሪም ናቸው) | ጋላገር | መጋቢት 19/2002 | ሆቴል | 7:50-8:34 |
| 12 | አቶ ሞላ መኮንን | 62 | ወንድ | አርሶ አደር (ፎካሪም ናቸው) | አዲስጌ | መጋቢት 20/2002 | ጠላ ቤት | 11:20-12:11 |
| 13 | ረዳት ኢንስፔክተር ሞላ እንየው | 43 | ወንድ | ፖሊስ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 10/2002 | ቢሮዋቸው | 4:27-5:10 |
| 14 | ቄስ ዓለሙ ጎዶ | 29 | ወንድ | አርሶ አደር | ሹማገራ ሎምዬ | መጋቢት 6/2002 | መኪና ውስጥ | 8:22-9:50 |
| 15 | ወይዘሮ አሠፉ በለጠ | 35 | ሴት | የቤት እመቤት | ክርክር ባለ እግዚአብሔር | መጋቢት 16/2002 | ቤታቸው | 11:30-12:44 |

## 2·2 የንዑሳን መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | የአቀባይ ስም | እድሜ | ፆታ | ሙያ | ቀበሌ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወይዘሮ የመንግስት ከፍአለ | 28 | ሴት | በወረዳው ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሔር ዳኛ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 7/2002 | ቢሮዋቸው |
| 2 | አቶ ደግፍ መኮንን | 60 | ወንድ | ዘበኛ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 19/2002 | ጠላ ቤት |
| 3 | ወይዘሮ የሽ ዓለም ብጫ | 55 | ሴት | ባላቸው የሞተባቸው | ከች ዓይነት ውሃ | መጋቢት 8/2002 | ትክል ድንጋይ በእንግድነት ዘመድ ቤት መጥተው |
| 4 | ሳጅን ክንዴ ይግዛው | 37 | ወንድ | ፖሊስ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት 17/2002 | ቢሮዋቸው |
| 5 | ተማሪ አንዳርጋቸው እንየው | 25 | ወንድ | ተማሪ | ክርክር ባለ እግዚአብሔር | መጋቢት 19/2002 | ሌሎች መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ስሄድ መንገድ ላይ |
| 6 | ቄስ ታዬ በለጠ | 61 | ወንድ | አርሶ አደር | ክርክር መድሃኒዓለም | መጋቢት 4/2002 | ቤታቸው |
| 7 | አቶ ዋሲሁን አቡሃይ | 37 | ወንድ | ወዛደር | ትክል ድንጋይ | መጋቢት12/2002 | ጠላ ቤት |
| 8 | አቶ ብርሃን አውደው | 41 | ወንድ | ነጋዴ | ሹማገራና ሎምዬ | መጋቢት 12/2002 | ጠላ ቤት |
| 9 | ወይዘሮ ስስት ውብነህ | 46 | ሴት | የቤት እመቤት | ሹማገራና ሎምዬ | መጋቢት 12/2002 | ቤተ ክርስቲያን ማህበር ሲጠጡ |
| 10 | አቶ ጎዶ ጌጤ | 72 | ወንድ | አርሶ አደር | ሹማገራና ሎምዬ | መጋቢት 12 እና 21/2002 | ጠላ ቤት እና ቤተ ክርስቲያን ማህበር ሲጠጡ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ሲጠጡ |
| 12 | አቶ ዘመነ ተሻገር | 49 | ወንድ | አርሶ አደር | ሹማራና ሎምዬ | መጋቢት 12/2002 | ቤተ ክርስቲያን ማህበር ሲጠጡ |
| 13 | አቶ ይደሰት በለጠ | 38 | ወንድ | አርሶ አደር | ከርከር ባለ እግዚአብሔር | መጋቢት 7/2002 | ጠላ ቤት |
| 14 | ወይዘሮ ታንጉት ምትኩ | 48 | ሴት | የቤት እመቤት | ሹማራና ሎምዬ | መጋቢት 7/2002 | ቤተ ክርስቲያን ማህበር ሲጠጡ |
| 15 | ወይዘሮ ሙሉ ተረፈ | 46 | ሴት | የቤት እመቤት | ጅሃ | መጋቢት7 /2002 | ቤተ ክርስቲያን ማህበር ሲጠጡ |
| 16 | አቶ አበበ መርሻ | 28 | ወንድ | አርሶ አደር | ማሒን | መጋቢት 13/2002 | ጠላ ቤት |
| 17 | አቶ ሞገስ ደርሶ | 32 | ወንድ | አርሶ አደር | አዲስጌ | መጋቢት 13/2002 | ጠላ ቤት |
| 18 | አቶ ማዘንጊያው ጌጡ | 47 | ወንድ | ዘበኛ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት11 /2002 | ሆቴል |
| 19 | አቶ አለበል ባዬ | 49 | ወንድ | የወረዳው ማስታወቂያና መረጃ ቢሮ ሐላፊ | ትክል ድንጋይ | የካቲት30/2002 | ቢሮዋቸው |
| 20 | አቶ ይርዳው አባይ | 32 | ወንድ | አርሶ አደር | ካምፊንታ | መጋቢት 13/2002 | ጠላ ቤት |
| 21 | አቶ ሰለሞን አገኘሁ | 28 | ወንድ | በወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ሠራተኛ | ትክል ድንጋይ | መጋቢት /2002 | ቢሮዋቸው |
| 22 | አቶ ሞላ እንየው | 48 | ወንድ | አርሶ አደር | ሹማራና ሎምዬ | መጋቢት 7 እና 12/2002 | ቤተ ክርስቲያን ማበር ሲጠጡ |
| 23 | አቶ አለበል በላይ | 29 | ወንድ | መምህር | እንድቢና ያደጉና አሁን ትክል ድንጋይ የሚኖሩ | መጋቢት18/2002 | ትምህርት ቤት |

## አባሪ ሶስት፦ ኢንተርቪው ለተደረገ አካላት የተደረጉ መንደርደሪያ ጥያቄዎች

### 3.1 ለካህናት የቀረቡ

1. ስለየቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ቤተ ክርስቲያን የጽሑፍ መረጃ ይኖራት ይሆን? ካለ ምን ይላል?
2. ግንዘት ምንድነው? የጉዞ ፍታትስ?
3. አስከሬን ዑደት ያደርጋል፤ ወደ ምስራቅም ሶስት ጊዜ እንዲሰግድ ይደረጋል። ሲቀበርም ራሱ ወደ ምእራብ እግሮቹ ደግሞ ወደ ምስራቅ ተደርገው ነው። ይህ የሚሆነው ለምንድነው?
4. መጽሐፈ ግንዘት የሚነበበው ለምንድነው?

### 3.2 ለአዛውንቶች የቀረቡ

1. በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ፉከራና ቀረርቶ የሚደረግላቸው ሰዎች ምን ምን ተግባራትን የፈጸሙ ናቸው? ፉከራውና ቀረርቶው የድሮው ይሻላል ወይስ የአሁኑ?
2. ፉከራና ቀረርቶ ምን ይጠቅማል? ምን ዓይነት ስሜትስ ይፈጥርብዎታል?
3. ጥሩ ፎካሪ የሚባለው ምን ዓይነት ሰው ነው?
4. በየጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት የሟች አልባሳት፣ ጋሻ፣ ጎራዴ፣ ጠመንጃ፣ ወዘተ የሚወጡት ለምንድነው?
5. ለጀግና ገበሬም ይፎከራል። ታዲያ ገበሬው ጀግንነቱ አርሶ ብዙ ማምረቱ ሆኖ ሳለ፣ በቀብሩ እለት ለማድመቂያነት የሚወጡት ደግሞ ሞፈሩ፣ ቀንበሩ፣ በሬዎቹ ሳይሆኑ ጠመንጃ፣ ጋሻ፣ በቅሎ፣ ወዘተ ናቸው። ይህ ለምን ይሆናል?
6. ለቅሶ ደራሽ አፉን በጋቢ ወይም በነጠላ የሚሸፍነው፣የሃዘንተኞችን ትከሻም የሚነካው ለምንድነው?
7. የቀብር ሥነ ሥርዓት እንደተጠናቀቀ የሟች የህይወት ታሪክ ይነበባል፤ የእዝን ምግብ ይቀርባል፤ የደመር ለቅሶም ይቀጠራል። ለምን?

## 3.3 ለፎካሪዎች የቀረቡ

1. ከቀብር ሥነ ሥርዓት ውጭ በምን በምን አጋጣሚዎች ፎክረው ያውቃሉ? የት ሲፎክሩ ነው ጥሩ ስሜት የሚሰማዎትስ? ፉከራስ ለምን ይጠቅማል ይላሉ?

2. እርስዎ ፎክረው እንደጨረሱ ሌላው ፎካሪ ከእርስዎ ተቀብሎ እንዲፎክር የሚያደርጉበት መንገድ ምንድነው?

3. በፉከራ ጊዜ የአድማጭዎን ትኩረት ለመሳብ ምን ምን ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

4. በፎካሪነትዎ ምን ተሸልመው ያውቃሉ?

5. የፉከራ ግጥሞችን እንዴት ነው የምትገጥሙት? በፊት የሚያውቋቸውን ነው ወይስ እዛው እየፎከሩ ባሉበት ሁኔታ ነው የምትገጥሟቸው?

6. በፉከራ ጊዜ እንደ ጠመንጃ፣ ጋሻ፣ ጎራዴ፣ ጦር፣ ወዘተ ያሉን መሳሪያዎች ይዘው ሲፎክሩ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማዎታል?

## 3.4 ለፖሊሶችና ለመንግስታዊ አካላት የቀረቡ

1. አንድ የቀብር ሥነ ሥርዓት ህጋዊ ነው የሚባለው መቼ ነው?

2. በጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ወቅት ከሚደረገው ፉከራና ቀረርቶ ምን ምን ነገሮችን ያደንቃሉ? የሚጠሉትስ ይኖራል?

3. በጀግኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ጥይት መተኮስ የሚከለከለው ለምንድነው? የተኮሰስ ቅጣቱ ምንድነው?

4. ማህበረሰቡ ከፉከራ ጋር ጥይት እንዳይተኩስ የምትቆጣጠሩበት መንገድ ምንድነው?

# የአማራ ክልል ካርታ
# Map of Amhara Region by Zone



የሰሜን ጎንደር ዞን ካርታ በወረዳ

# MAP OF NORTH GONDAR BY WOREDA




Source: NG DOFED, DPP



N
Map of Lay Amachiho Woreda by kebele
Work Midir
Merena
Aykua Chakir
Mahin
Kamfenta
Janikew Kunjiba
Atsie Midir
Dazihon
Kech Ayinet Wuha
Jiha
Alege Muna
Adisgie
Shumara Lomiye
Giramita
Tikil Dingay Town
Genbera Anigereba
Ledaho
Chira Anibezo
Kerker B/Egziabiher
Abela Sayina
Bir Lebeho Enchinako
Chila Dewa
Kerker Endibine
Sata Midraro
Jinkira
Banblo
Werangib
Kerewa Mezewa
Mawra
Chankiya
Woinoche Gizana
Zeraige
Begamigie
Gonderoch Mariam
Chachikuna
6,300 3,150 0 6,300 12,600
Km
Source: NGDoFED. Development Planning Process

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የእኔ (original work) ወጥ ስራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም፡-______________________________

ፊርማ፡- ______________________________

የማስረከቢያ ቀን፡-__________________________